# ክፍል ፩

# የታኅሣሡ ግርግር

# ምዕራፍ ፩

# የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪዎች

## ወርቅነህ ገበየሁ ( ? - ፲፱፻፶፫ ዓ.ም.)

ወርቅነህ ገበየሁ እንደ ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ለንጉሠ ነገሥቱ ቅርብ፣ ተወዳጅ፣ ተሰሚና ብርቱ አገልጋይ በመሆን ከ፲፱፻፵፯ እስከ ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. አገልግሏል፡፡ በነዚህ ዓመታትም፣ ለአገሩ ዕድገትና ለሕዝቡ ኑሮ መሻሻል የሚረዳ የመንግሥት ሥርዓት ለውጥ እንዲደረግ የሚያሳስቡ ልዩ ልዩ ማስታወሻዎችን ለንጉሠ ነገሥቱ ያለመታከት ያቀርብ ነበር፡፡ እነሱን ከማየታችን በፊት ግን ወርቅነህን ወደዚህ ኃላፊነት ያደረሰውን የሕይወቱን ጉዞ በጥቂቱ እንመልከት፡፡

ወርቅነህ ገበየሁ እንደ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ከገበሬ ቤተሰብ፣ ከአቶ ገበየሁ ገብሬ ሕይወት እና ከወ/ሮ ውዲቱ ብሩ በቀድሞው የቤጌምድርና ስሜን ጠቅላይ ግዛት፣ በደብረ ታቦር አውራጃ፣ ሐሙስ ወንዝ አትክና ጊዮርጊስ ተብሎ በሚጠራው ቀበሌ ተወለደ፡፡ ወርቅነህ ለወላጆቹ በኩር ሲሆን፤ ተከታይ አምስት ወንድሞችና ሦስት እህቶች ነበሩት፡፡

ወርቅነህ ዕድሜው ለትምህርት ሲደርስ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ገብቶ በአካባቢው ይሰጥ የነበረውን ትምህርት ከጊዜው ቀድሞ ዘለቀ፡፡ ቅኔ ለመማር ጐጃም ሔዶ ትምህርቱን በመከታተል ላይ በነበረበት ግዜ በአዲስ አበባ ከተማ የልዩ ልዩ ሙያ ሊቃውንት መኖራቸውን ይሰማ ስለነበር፤ ጊዜ ሳያጠፋ አዲስ አበባ ሔዶ ከነዚህ ሊቃውንት ዘንድ ትምህርቱን ለመቀጠል፣ በዚያውም ክህነት ለመቀበል በ፲፱፻፴፯ ዓ.ም. መጨረሻ በእግሩ አዲስ አበባ ገባ፡፡ ከርሱ ቀደም ብሎ ከዚሁ ከደብረ ታቦር አውራጃ በተለያየ ምክንያት የመጡት፣ ነጋ ተገኝ (በኋላ ሜጀር ጀነራል)፣ መልኬ ታደሰ? ታሁን (በኋላ ብርጋድዬር ጄኔራል)፣ ወርቁ መኮንን (በኋላ ብርጋዴር ጄኔራል)፣ ከበደ? ታምሩ ወንዴ (በኋላ ኮሎኔል)፣ ያሬድ ቢተው (በኋላ የሻለቃ) በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም. መጀመሪያ፣ በአቶ መኮንን ዘውዴ (የትምህርት ሚኒስቴር ኢንስፔክተር) አጋዥነት ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ሦስተኛ ክፍል ሲገቡ ወርቅነህም ዕድል አግኝቶ በዚሁ ትምህርት ቤት እንዲገባ ተደረገ፡፡ ሁሉም ከገጠር የመጡ እንደመሆናቸው እንግሊዝኛ ቋንቋ ከብዷቸው የነበረ ቢሆንም በርትተው በማጥናት ቀደም ብለው በዚያው ትምህርት ቤት ከነበሩት ተማሪዎች በመጀመሪያው ተርም ብልጫ ያገኙ ተማሪዎች ሆኑ፡፡ በተለይ ወርቅነህ ከሁሉም ልቆ አንደኛ ሆነ፡፡ በሁለተኛው ተርምም እንደዚሁ አንደኛ ሆኖ አለፈ፡፡ ወርቅነህን ጨምሮ ሁሉም ሦስተኛ ተርም ከማለቁ በፊት ለክብር ዘበኛ ጦር መኮንኖች ማሠልጠኛ (ካዴት) ትምህርት ቤት ተመልምለው ገቡ፡፡ በዚህ እጩ የጦር መኮንኖች ማሠልጠኛ ት/ቤት ወርቅነህ

ሦስቱንም ዓመት አንደኛ በመውጣት ትምህርቱን ሲያጠናቅቅ፤ በተለይ ለውጊያ ሥልት በሚዘጋጅ የአሸዋ ገበታ አዘገጃጀትና መግለጫ አሰጣጥ በጣም የተደነቀ ነበር።

የወርቅነህ የንግግር፣ የቃላት ፍሰትና አጠቃቀሙ ግሩም የመናገር ተሰጥኦው ማሳያ ነበር። በ፲፱፻፶፩ ዓ.ም. የመኮንንነት ሥልጠናውን ሲጨርስ የመመረቂያውን መግለጫ ንጉሠ ነገሥቱን፣ ንግዶችንና ጓደኞቹን ባስደሰተ ሁኔታ አቅርቦ ከሌሎች



ለወርቅነህ በሜጀር ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ተፈርሞ የተሰጠው

ጓደኞቹ ጋር ከሃምሳ አለቅነት ወደ ምክትል የመቶ አለቅነት ማዕረግ ማደጉ ተገልጾ በስሙ ተጠርቶ ዲፕሎማውን ተቀብሏል። ወርቅነህ በተለይ ሦስቱንም ዓመት አንደኛ በመሆኑ ንጉሠ ነገሥቱ የሹመት የምስክር ወረቀት (ዲኘሎማውን) የሰጡት፤ የመኮንንነት ቀበቶውን እራሳቸው በማስታጠቅ ነበር። ይህንንም ተመራቂ ጓደኞቹና በሥፍራው የነበሩ ሁሉ "ይገባዋል! ይገባዋል!" በማለት አወድሰዋል።

ወርቅነህ ታኅሣሥ ፯ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ.ም. በመኮንንነት ከተመረቀ በኋላ፣ ከሌሎች ጥቂት ጓደኞቹ ጋር በዕጩ መኮንኖች ማሠልጠኛ (ካዴት) ትምህርት ቤት ባሠልጣኝነት ተመድቦ ሠርቷል። እዚያም እያለ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በማታው ክፍለ ጊዜ ተከታትሎ በማጠናቀቅ የቀለም ትምህርቱን አሻሽሏል። ከዚያም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ በማታው መርሃ ግብር ትምህት ቤት ተመዝግቦ በሕዝብ አስተዳደር መማሩን ቀጥሏል። በርካታ ኮርሶችም ወስዶ ጥሩ ውጤት ማስመዝገቡን አብረውት ይማሩና ይሠሩ የነበሩ ጓደኞቹ ይናገራሉ። ከሚጠቀስለት ጉብዝናው አንዱ ብርቱ አንባቢነቱ ነበረ። ይህ መኮንን አማርኛ፣ ግዕዝ፣ እንግሊዘኛና ሲዊዲሽኛን አቀላጥፎ የሚናገር፤ በጣሊያንኛ፣ በፈረንሳይኛና አረብኛ ቋንቋዎችም ለመግባባት የሚያበቃ




ለወርቅነህ በሜጀር ጄኔራል ሙሉጌታ ቡሊ ተፈርሞ የተሰጠው


ችሎታ ነበረው። ይሁን እንጂ በነበረው የሥራ ጠባይ አለመመቸት ትምህርቱን ሙሉ ለሙሉ አጠናቆ ዲግሪውን ለመቀበል አልቻለም።

ሁለተኛው የዓለም ጦርነት እንዳበቃ የተባበሩት መንግሥታት ማኅበር ሲመሠረት ኢትዮጵያም በመሥራች አባል አገርነት ተመዘገበች። በዚህ ጊዜ የተቀበለችቸው የአባል አገር ግዴታዎች ነበሩ። ከእነርሱም አንዱ አንድ የተባበሩት



*ወርቅነህ በምክትል መቶ አለቃ ማዕረግ*

መንግሥታት አባል አገር በግፍ ሲወረር፣ ማኅበሩ ወራሪውን በጋራ ጦር ተከላክሎ ለማስቆም ጥሪ ሲያደርግ፣ ጦር መላክ ነበር። በመሆኑም፣ ደቡብ ኮርያ በሰሜን ኮርያ ሲወረር፣ ኢትዮጵያ ጦር እንድትልክ ተጠይቃ፣ በተከታታይ ላከች። ወርቅነህም



*ወርቅነህ በምክትል መቶ አለቃ ማዕረግ*

ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ደቡብ ኮርያ በተላከው የቃኘው ሻለቃ ጦር በሻምበል ማዕረጉ (መደቡ የሻለቃ ነው) የዘመቻና የትምህርት መኮንን ሆኖ ወደ ደቡብ ኮርያ ዘመተ:: ይህ ኃላፊነት የሻለቃ ጦሩን ለግዳጅና ለማንኛውም እንቅስቃሴ በቂ ሆኖ እንዲገኝ ማዘጋጀት ነበር:: የተሰጠውን ግዳጅ ለመፈፀም ብቃቱን ያሳየባቸው አጋጣሚዎችም ነበሩ:: በወቅቱ የነበሩ ጓደኞቹ እንደገለጹልኝ፤ ባንድ ወቅት በማዕረግ ከሱ ጋር ተመሳሳይ ከሆኑ አሜሪካውያን መኮንኖች ጋር አንድ ዓይነት ከፍተኛ ግዳጅ እንዲፈፅሙ ከፀፀኛው የአሜሪካ ጦር አዛዥ ትእዛዝ ይሰጣቸዋል:: ይህንን ግዳጅ በተቀረጠው ጊዜ በትክክል ፈፅሞ የተገኘ ሻምበል ወርቅነህ ገበየሁ ብቻ በመሆኑ ዋናው አዛዥ አድናቆታቸውን ለሱ ከገለጹ በኋላ ወገኖቻቸው የሆኑትን አሜሪካውያን መኮንኖችን «ታላቅ ከሚባለው የአሜሪካ የጦር አካዳሚ ተመርቃችሁ እንዴት አንድ አፍሪካዊ መኮንን ይብለጣችሁ?» ሲሉ ወቅሰዋቸዋል::

የደቡብ ኮርያ ዘመቻ ሲታወስ ሊነገሩ የሚገባቸው ሁለት ዐቢይ ቁምነገሮች አሉ:: እነርሱም የኢትዮጵያውያን ጀግንነትና የክብር ዘበኛ አባላት በውጪ የተደረሰበትን የዕድገት ደረጃ ለመመልከትና ካገራቸው አንጻር ለመገምገም መብቃታቸው ናቸው:: ከነዚሁ ሁነቶች ጋር በተያያዘ ስለወርቅነህም የሚታሰብ ጉዳይ አለ:: በደቡብ ኮርያ በአንደኛውም ሆነ ሁለተኛው ዙር የተሰለፈው የኢትዮጵያው የቃኘው ሻለቃ ጦር የውጊያ ቦታውን በተቃዋሚ ጦር ኃይል ተገዶ ለቆም ሆነ አንድም የቃኘው ሻለቃ አባል ተማርኮ አያውቅም:: ይህ ግን እንዲህ በቀላሉ የሆነ አይደለም:: እንዲህ ዓይነቱን የኢትዮያ «ሪኮርድ መስበር አለብን» በሚል የቻይናና የሰሜን ኮርያ ጦር ባለ በሌለ ኃይሉ የኢትዮጵያ ጦር የተሰለፈበትን ግምባር አጥቅቶ ለመያዝ ዝቶ እስከመምጣት ደርሷል:: ይህም አጋጣሚ ወርቅነህን ውጤታማ ስልት ለመፈፀም አስችሎታል:: ይኸውም ቀደም ብሎ ያገኘውን መረጃ ለጦሩ አዛዥ በማሳወቁ፤ ተባባሪ የጦር ኃይሎች ከባድ የመድፍና የአዳፍኔ መሣሪያዎች ዒላማቸውን ወደ ኢትዮጵያ ጦር ግንባር እንዲያልሙ ተደርጎ እንዲጠብቁ ማድረግ ተቻለ:: ስለዚህ የጠላት ጦር ወደ ኢትዮጵያ የውጊያ ግምባር እንደተጠጋ ተባባሪ የጦር ኃይሎቹ የመጣውን የጠላት ጦር ሲደበድቡ፤ ምሽግ ውስጥ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር ወደ ምሽጉ በተጠጋው የጠላት ጦር ላይ ተኩስ እንዲከፍት ትእዛዝ ሰጠ:: በዚህ ዓይነት የመጣው የጠላት ጦር ከግራና ቀኝ በሚተኮስ ዐረር መኸል ገብቶ ከፍ ያለ ጉዳት ደርሶበት ተመለሰ:: በውጊያውም ሻምበል ወርቅነህ ገበየሁ በከባድ መሣሪያዎች ማስተኮሻ አቅራቢያ ሆኖ በመምራት፣ የኢትዮጵያን ጦር ከሞትና ከምርኮ ሲያድን፤ እሱ ግን በከባድ መሣሪያ ድምፅ በግራ ጆሮው ላይ ከባድ ጉዳት ደርሶበት «ሴኡልና፣ ቶኪዮ» ሔዶ ታክሟል::

ለግዳጅና ለሕክምና በሔደባቸው አገሮች ወርቅነህ የየአገሮቹን የመንግሥት አስተዳደር የሕዝብ ኑሮ ዕድገትና ብልጽግና ምን ያህል ከራሱ አገር የላቀ እንደሆነ ለማስተዋል ችሏል:: ይኸው ግንዛቤ የሰረጸው በሻምበል ወርቅነህ ብቻ ሳይሆን በዘመቻው በተካፈለው የክብር ዘበኛ ጦር አባል ሁሉ ነበር:: ጦሩ ወደአገሩ ሲመለስ

የአገራቱ ያየውንና የሰማውን የሥልጣኔ ምጥቀት ከአገሩ ጋር እያመዛዘነ አመለካከቱ ተለውጦ፣ ንቃተ ኅሊናው አድጎና የለውጥ ፍላጐቱ አይሎ ነበር። ወርቅነህ በግልም ወደአገሩ ከመመለሱ በፊት በኮርያ ዘመቻ ላይ በነበረው የሥራ መደብ ምክንያት አስተዳደራዊ ልምድ ከፍተኛ ብስለት አግኝቷል። ምክንያቱም ከተለያዩ አገሮች የመጡ የተባበሩት መንግሥታት ጦር አዛዦች ጋር ስብሰባዎችን ለመካፈል ችሏል። ይህ አጋጣሚም በአስተዳደርና በወታደራዊ ሙያ ከበሰሉ ሰዎች የከፍተኛና ቁርጠኛ ትዕዛዝ አስተላለፍና አፈፃፀም ተግባር ለመካን በቅቷል። ወደ አገሩ እንደተመለሰም፣ የክብር ዘበኛ ሠራዊት በትምህርትና ዘመቻ መምሪያ ተመድቦ ጥቂት ጊዜ ሠርቷል። ቀጥሎ ያገኘው ኃላፊነት የዋናው አዛዥ የብርጋዴር ጄኔራል መንግሥቱ ልዩ ረዳት ሆኖ መሥራት ነበር። ይህም የሥራ መደብ የወርቅነህን የወደፊት ዕጣ ፈንታ የሚወስነውን ልዩ አጋጣሚ ፈጥሮለት ጄኔራል መንግሥቱ የወርቅነህን የሥራ አያያዝና ችሎታውን ለመመልከት እንዲችሉና በሥራው ፍፃሜ እንዲረኩ አድርጓል። ይህ ደግሞ በመካከላቸው መቀራረብና የፀና ምተማመን እንዲፈጠር ረድቷል።

ወርቅነህ በመሐሉ የጀርው ሕመም ስላስቸገረው፣ ለሕክምና ወደ ስዊድን ተልኳል። በወቅቱ ተልኮው ‹ለሕክምና› ይባል እንጂ፣ ከፍተኛ የነገረ መረጃ ትምህርት ለመከታተል ነው እየተባለ በሹክሹክታም ይወራ ነበር። እንደተባለውም ይመስላል፤ የንጉሡ ሥልጣን በሕግ በተገደበ ዘውዳዊ አስተዳደር በሚመራው በስዊድን ውስጥ የአገርን ፀጥታና ሉአላዊነት፣ የመንግሥቱን ጥንካሬና ቀጣይነት ለማረጋገጥ፤ የሕዝቡን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ኑሮ አዋኪ ደባዎችን ለማክሸፍ የሚያስችሉትን የሕዝብ ደህንነት ጥበቃ ትምህርትና ሥልጠና ኮርሶች ተከታትሎ ወደ አገሩ ተመልሷል።


የሻምበል ወርቅነህ ሥልጠናውን ጨርሶ ከተመለሰ በኋላ፤ በታኅሣሥ ወር ፲፱፻፵፰ ዓ.ም. በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የክብር ጥሪ የዩጎዝላቪያ መሪ የነበሩት ማርሻል ጆሴፍ ብሮዝ ቲቶ በኢትዮጵያ ለ፲፬ ቀናት ይፋ ጉብኝት እንዲያደርጉ ስለ ተጋበዙ፤ እንግዳውን ለማስተናገድ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት ተሰባስበው ተወያዩ። ዩጎዝላቪያ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት እንዳበቃ ሥርዓተ መንግሥቷን ሶሻሊስት ስታደርግ፣ ይህን ተቃውመው አገራቸውን ትተው ወደ ኢትዮጵያ የተሰደዱ በርካታ የዩጎዝላቪያ ዜጎችና ባላንጣቻው ጣልያኖች አዲስ አበባ ስለነበሩ፤ በእንግዳው ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ልዩ ጠባቂና አጃቢ የሚሆን ከጦሩ መካከል ለመምረጥ የተደረገው ውይይት የስብሰባው ተካፋይ የነበሩ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖችና የጦር አዛዦች ኃላፊነቱ ለክብር ዘበኛ ጦር ይሰጥ ብለው ወሰኑ። ይህ ኃላፊነት የተሰጠው የክብር ዘበኛ ዋና አዛዥና የልዩ ልዩ መምሪያ ኃላፊ መኮንኖች ባደረጉት ስብሰባ ደግሞ ለልዩ ቡድኑ አዛዥ ማን ይሁን በሚለው ጉዳይ ተነጋግረው ሻምበል ወርቅነህን በአንድ ድምፅ መረጡ። ኃላፊነቱን የተቀበለው ሻምበል ወርቅነህ ገበየሁም የመዲናዋ አዲስ አበባ አስፈላጊውን ሁሉ በጥንቃቄ ካዘጋጀ በኋላ የክብር ዕንግዳው

በሚገቡበት አሰብ ወደብ ቀደም ብሎ ደርሶ ኃይሉን በመጠበቂያው ቀጠና አሠማራ። ማርሻሉ ሲደርሱም ባለው ጦር ለክብር እንግዳው የክብር አቀባበል አደረገ።



ወርቅነህ ለክቡር ማርሻል ብሮዝ ቲቶና ለግርማዊ ጃንሆይ የማይጨው ጦርነትን ያሳየበት የአሸዋ ገበታ

ለእንግዳው ጉብኝት ከተያዘው ፕሮግራም አንዱ የማይጨውን የጦርነት ቦታ ማሳየትና ስለጦርነቱ መግለጫ መስጠት ነበር። ይህ አጋጣሚ ደግሞ ወርቅነህን ከንጉሡ ጋር የሚያስተሳስር ሁነትን ፈጥሮለታል። ወርቅነህ በዚህ ወቅት በሻምበል ማዕረግ (የመስመር መኮንን) ይሁን እንጂ፣ የሥራው ደረጃ ከጄኔራል መኮንን አመራር ጋር የሚነጻጸር ነበር። ለእንግዳው በተያዘላቸው መርሐ ግብር መሠረት ሻምበል ወርቅነህ የማይጨውን የውጊያ ቦታ በአሸዋ ገበታ አዘጋጅቶ መግለጫ አቀረበ። አገላለጹ ግን ከታሪክ ባገኘው ሳይሆን በጦርነቱ ወቅት በአካል ተካፋይ የነበረ ያህል ስሜት በሚቀሰቅስና ድርጊቱ ራሱ በገለጸው ወቅት የሆነ ያህል እስኪመስል የአዳማጩን ትኩረት በመሳብ ነበር። ዝርዝሩም እንግዳውንና ንጉሠ ነገሥቱም እጅግ የመሰጠ ሆነ። በተለይ ገለጻው ስለ ጠላት የአየር ጥቃት መከላከል ውጊያ ምዕራፍ ላይ ሲደርስ «ባለሙያው እዚህ በመካከላችን ስላሉ እሳቸው ቢገልጹት የበለጠ ይሆናል» በሚል ጃንሆይን ጋብዞ መድረኩን በመልቀቁ፤ ማርሻል ቲቶ በአቀራረቡ በመደነቅ ከመቀመጫቸው ተነሥተው በመሔድ አቅፈው እንደሳሙት እዚያው የነበሩ ይናገራሉ። ብዙ ጊዜ ለሣቅ ቁጥብ የሆኑት ጃንሆይም እንደማርሻል ቲቶ ፈካ ብለው እየሳቁ በመገረም መድረኩን ተረክበው ገለጻ አድርገዋል።



*ወርቅነህ ለክቡር ማርሻል ብሮዝ ቲቶና ለግርማዊ ጃንሆይ የማይጨው ጦርነትን ያሳየበት የአሸዋ ገበታ*

ከዚህ በተጨማሪ የሻምበል ወርቅነህ በዚሁ ቦታ ሁለት ያልታሰቡ ድርጊቶችን ፈጸሙ በቦታው የነበረውን ሁሉ ሲያስደንቅ ንጉሡንም አስደስቷል። ነገሩ እንዲህ ነው። አንድ ረዘም፣ ጠውለግ፣ አርጀት ያለ ሰው ጉላ ባለ ድምፅ እየጮኸ «እርጥባን» ለመጠየቅ ወደ እንግዶቹ ሲመጣ፤ ጃንሆይ ቀደም ብሎ የነበረውን ደስታ ሊያጠላበት ነው ብለው ቅሬታ ተሰማቸው። ማርሻል ቲቶም «ምንድነው የሚለው?» ብለው ወርቅነህን ሲጠይቁት፤ ቀልጠፍ ብሎ «የፋሺስት ኢጣሊያ ደመኛና አርበኛ፣ አገራችንን ከጠላት ወረራ ለመከላከል የተጋደልንበትን ቦታ ለማየት በመምጣትዎ የአካባቢው ኅብረተሰብ ከፍ ያለ ደስታና ክብር ተሰምቶናል። እጄን የዘረጋሁት ይህንን ምስጋና ይቀበሉኝ ስል ነው» የሚለው ብሎ ነገራቸው። ማርሻል ቲቶም ራሳቸውን ደጋግመው ነቃነቅና በማጨብጨብ ለምስጋናው አጸፋውን መልሰዋል። ልክ እንዲሁ ደግሞ እንግዳው የሚያልፉበትን መንገድ ያወቁ የአገሩ ሰዎች እርጥባን ለመጠየቅ ከፊሉ ነጠላቸውን እያነጠፉ፣ ከፊሉ ደግሞ ቅጠልና ለምለም ሣር በመንገዱ ላይ እየነሰነሱ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ሲጮኹ፤ አሁንም በድጋሚ ማርሻል ቲቶ «ምንድነው የሚሉት?» ብለው ይጠይቃሉ። ሁኔታው ጃንሆይን ክፉኛ አሰቅቆ ነበር። የአገር ገመና ነውና ዘዴኛው ወርቅነህ አሁንም ቀበል አድርጎ «በኢትዮጵያ ባህል ትልቅ ሰው ወደ አገሩ ሲመጣ ወይም ከአገሩ ሲወጣ፤ የአካባቢው ሕዝብ አሁን እንዳዩት ያለውን ሁሉ እያደረገ ከራሱ ዝቅ ብሎ የኛ ወዳጅ፣ የኛ እንግዳ እንኳን ደህና መጡ። በዚህ ላይ ይሒዱ በማለት ነው የሚቀበለውም፣ የሚሸኘውም» ብሎ ይመልሳል። ይህ መልሱ አጥልቶ የነበረውን የቅሬታ ድባብ ከንጉሡ ላይ ገፎ ደስታን አጐናፀፏል። የዚህ ወጣት ቅንን ፈጣንና አስተዋይነት በእንዲህ ዓይነቶቹ በርካታ አጋጣሚዎች በመገለጻቸው፤ ንጉሡ ከእንግዳቸው ጋር ይህን ሁሉ አልፈው ማረፊያቸው ሲደርሱ፣ «ያን ወጣት ቅንን ጥሩት! ራቱን ከዚህ ይብላ። ከዚህም እንዳይለይ።» በማለት ለልፍኝ አስከልካዩ ትዕዛዝ ሰጡለት። ይህች ዕለት ንጉሡንና ወርቅነህን አቀራረበች። ዘለቄታው ግን ከበደ ሚካኤል በ***የዕውቀት ብልጭታ*** መጽሐፋቸው

*ዕድል አጋጣሚ ለሰው ልጅ ስትመጣ*
*መልካምና ክፉ አላት ሁለት ጣጣ*

እንዳሉት ሆነ እንጂ።

ይህ ወቅት በመንግሥቱ መዋቅር የፀጥታ ጥበቃ መሥሪያ ቤት ተቋም በአገር ግዛት ሚኒስቴር ሥር ሆኖ፣ በሥሩ ወህኒ ቤቶችን፣ የፖሊስ ሠራዊትንና የወሰን ጉዳይ መሥሪያ ቤትን ይዞ፣ በኮሎኔል (በኋላ ደጃዝማች) ክፍሌ ዕርገቱ ሲተዳደር የነበረበት ጊዜ ነበር። መዋቅሩ ለይስሙላ ነው እንጂ የዕዝ መሥመሩ ምንጊዜም ተጠብቆ አያውቅም። ግንኙነቱን ሁሉም በየፊናው ከንጉሡ ጋር (በከፋፍለህ ግዛው ሥልት) ስላደረገ፤ ሥራው በልዩ ልዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በግለሰብና በቡድን ተከፋፍሎ ባመዛኙ ጥገር የፖለቲካ የኤኮኖሚና ማኅበራዊ ጥቅም ጥበቃ ላይ ሳይሆን፤ በአስተዳደሩ ላይ በሚነሡ ቅሬታዎች፣ ትችቶችና ነቀፋዎች፣ እንዲሁም፣ በንጉሡ

ስምና ክብር (ክብረ ነክ) ጥበቃ ላይ ያተኮረ፣ ብሎም አንዱ በሌላው ውድቀት ለማደግ በሚደረግ የርስበርስ ጠለፋና ሽኩቻ ላይ ያተኮረ ነበር።

በሌላ በኩል ደግሞ ያለው የፀጥታ መሥሪያ ቤት ተቋም ከ፲፱፻፵፩ ዓ.ም. ጀምሮ እያደገ የመጣውን የውጭ ዜጎች ዓይነትና ብዛት መጨመር፣ የተማሪዎች እንቅስቃሴ መስፋፋት፣ የዘውዳዊ አስተዳደር ፀር የሆነው ኮሚኒዝም ወደ አገሪቱ መሥረግ መጀመር፣ የኮሎኔል ጀማል አብደል ናስር በመፈንቅለ መንግሥት ወደ ግብፅ ፕሬዚዳንትነት ሥልጣን መምጣት በኢትዮጵያ ወጣቶች ላይ ያሳደረው ስሜትና ተነሣሽነት፣ በልዩ ልዩ ዘርፍ እየተከፋፈለ የገባው የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት እንቅስቃሴንና ሌሎች ሁኔታዎችን ተከታትሎና ተቆጣጠሮ ለከፍተኛ ደረጃ ውሳኔ አሰጣጥ ማዘጋጀት የሚያስችለው ብቃት እንደሚጐድለው ግልጽ ሆኖ ታየ። እንዲህ በመሆኑ የሥራ ክፍሉ ኃላፊነቱን በሚገባ ሊወጣ በሚችልበት ሁኔታ መደራጀት እንዳለበት ታመነ። የሚደራጀው ክፍል ፈጣን፣ ብልህ፣ ንቁና ወሳኝ በሆነ አንድ ኃላፊ መመራት እንዳለበትም ግንዛቤ ተወሰደ። ስለዚህ ሁሉም በየበኩሉ ይመጥናል የሚለውን የራሱን ሰው ማፈላለግ ሲይዝ፤ ጃንሆይ ግን ምርጫቸውን ቀደም ብለው ብልህነቱን፣ ፍጥነቱንና ጥንቃቄውን ባዩት ወጣት የክብር ዘበኛ መኮንን በሻምበል ወርቅነህ ገበየሁ ላይ አሳረፉ። በዚህ መሠረት በ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. የፀጥታ መሥሪያ ቤቱን በዘመናዊ መንገድ አዋቅሮ እንዲመራ ወርቅነህን ሾሙት።

ወርቅነህ አዲሱን ሹመት እንደተቀበለ በቀጥታ ወደ ተሾመበት መሥሪያ ቤት ከመሔድ ይልቅ የሥራ መዋቅሩን፣ ይዘቱንና አመራሩን እየቀየሰ በመኖሪያ ቤቱ ለጥቂት ወራት መቆየትን መረጠ። አስቀድሞ ካሰበባቸው ነገሮች መኸል አንዱ የሠራተኞች ምልመላን ሲሆን፤ ለዚህም የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድ አወጣ። ሥራውን በይፋ ሲጀምርም ከነባሮቹ የመረጣቸውንና ከፖሊስ፣ ከክብር ዘበኛ፣ ከጦር ሠራዊትና ከሲቪሉ ክፍል አዲስ የመለመላቸውን ሰዎች ጨምሮ መጀመሪያ ካዛንቺስ ከነበረው የፀጥታ መሥሪያቤት፤ በኋላ ሦስተኛ ተብሎ ከሚታወቀው አካባቢ ያለው መሥሪያ ቤቱ ገባ።

ወርቅነህ የዕቅዱ አፈፃፀምን የመጀመሪያ ተግባር ሥራና ሠራተኛን ማገናኘት አድርጎ፤ ሠራተኞቹ ሊከተሉ የሚገባቸው በዴሞክራሳዊ ሥርዓት አገራዊ፣ ኤኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ጉዳዮችን (ፖሊስ ከሚሠራቸው ጉዳዮች) ለይተውና ጠንቅቀው እንዲያውቁና እንዲጠብቁ፤ ዋና ተግባራቸውም በሕዝብና በመንግሥት መካከል አገናኝ ድልድይ እንዲሆኑ መሆኑን አስረድቶ እንደየዝንባሌያቸው ወደ ሥራ አሰማራቸው። በመጀመሪያው ዙር ከመረጣቸው ሠራተኞች መካከል አንዱ ስዊድናዊ አማካሪ ነበር። በፀጥታ መሥሪያ ቤት የውጭ አገር ሰው ቢሮ ይዞ ሥራ መጀመሩ ለነባር ሠራተኞች አስደንጋጭ አጀማመር ሆነ። ከብዙ አቅጣጫም ተቃውሞ አስከተለ። ይሁን እንጂ፣ ወርቅነህ ለሥራው ይጠቅሙኛል ያላቸውን ሌሎች ባለሙያዎችንም በመጨመር የውጭ አገር አማካሪዎችን ሚና ስፋትና ጥልቀት እየሰጠ

እስከ መጨረሻው ቀጠለ።[1] እንዲህ በማድረጉም መሥሪያ ቤቱን ዘመናዊ የአሠራር ሥልት ለማስያዝ ያስቻለውና ከስኬት ሊቆጠር የሚችል ውጤት ያገኘበት ነበር።

የሻለቃ ወርቅነህ አሁን (የሻለቃ ሆኗል) በፀጥታ መሥሪያ ቤት ሥራ የጀመረው ለሥራው የሰምሪት ክልል ሳይደረግ ነው። በአስተዳደር፣ በፍትሕ፣ በትምህርት፣ ጤና፣ በኢኮኖሚና ...ወዘተ. ሥራዎች ሁሉ ይገባ ነበር። ይህም የሥራ ይዞታ ንጉሡ ትዕዛዝና ፍቃድ እንደነበር ወደፊት በሚነሡ ጉዳዮች ላይ ሲንፀባረቅ ይታያል። ይህ ዓይነቱን አሠራርም እስከ መጨረሻው ተግብሮታል። የተሰጠውን ሰገብ ኃላፊነትም ሻለቃ ወርቅነህ የብዙዎችን ድጋፍ በሚያስገኝ መልኩ በማድረጉ ውጤማነቱን የጨመረለት ሆኗል። ይኸውም ቀደም ብሎ በክብረ ነክና በአስተዳደሩ ላይ ባሰሙት ትችትና ነቀፋ ክስ ተመሥርቶባቸው ተይዘው የነበሩትን ሰዎች በአካል ተገናኝቶ በማነጋገር፣ ዳኞችንና ዐቃቤ ሕጎችንም በማማከር፣ ክሳቸው ተዘግቶ ሥራቸውን በሰላምና በተረጋጋ መንፈስ እንዲያከናውኑ መክሮ ከእሥር አስፈትቷቸዋል። እንዲህ ዓይነቱ ዕርምጃው የፀጥታ መሥሪያ ቤቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለሕዝባዊና አገራዊ ደህንነት የሚሠራ መሆኑ እንዲታወቅና ብዙ ሰው በዜግነቱ የሚሳተፍበት እንዲሆን መተማመን አስገኝቶለታል።

ወርቅህ የተከተለው አስተዳደር ከሕዝቡ በአገር ኤኮኖሚ ላይ በደል የሚያደርሱ ሰዎችን እየጠቆሙ ማጋለጥ የጀመሩ ሰዎችም እንዲገኙ አድርጓል። ለማስረጃም ጥቂት ነጋዴዎች የመንግሥት ባለሥልጣኖችንና የጉምሩክ ሠራተኞችን በመተያያና በስጦታ ደልለው፣ ቀረጥ ሳይከፍሉ የጦር መሣሪያ እና ሸቀጣ ሸቀጥ ወደ ሱቃቸው ለማስገባታቸው ባገር ተቆርቋሪዎች መጠቆሙን መጥቀስ ይቻላል። የሕዝብ ጥቆማ መረጃ ክፍሉ ደርሶ ማስረጃው ተጣርቶና ተቀነባብሮ ሕግ ተላላፊዎቹ ፍርድ ቤት ቀርበው ጉዳያቸው በዳኝነት ከታዩ በኋላ መክፈል የነበረባቸውን ብር ፻፷ ሺህ (አንድስት መቶ ስልሳ ሺህ ብር) የመንግሥት የቀረጥ ሒሳብ ገቢ እንዲያደርጉ ተበየነ። ፈፀሙት ወንጀል ይሰጥ የነበረው የእሥራት ቅጣት ምሕረት ተደርጐላቸው ሥራቸውን ቀጠሉ።

ልክ እንዲሁ አንድ የቡና ላኪ ድርጅት ባለቤት ከጉምሩክ ሠራተኞችና አንዳንድ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ጋር በመሻረክ፣ ቡናውን ባቄላ ነው እያለ ባቄላው ቀረጥ ከቡናው ቀረጥ ስለሚያንስ) ወደውጭ ይልክ ነበር። በዚህም መንግሥት መግባት የነበረበትን ቀረጥ አይከፍልም ነበር። ይህም ለሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ መሥሪያ ቤት ተጠቁሞ ስውየው ይከሰስና ፍርድ ቤት ብር ፪፻ ሺህ (ሁለት መቶ ሺህ ብር) እንዲከፍል ይበይንበታል። ወንጀለኛው ብሩን ገቢ እንዲያደርግ ሲደረግ ሥታሠሩ ድርጅቱን መዘጋት ስለሚያስከትል ይህን ተከትሎ ሊመጣ የሚችለውን የሠራተኛውን መበተንና የቡና ነጋዴዎችን የወደፊት ገበያ መጥበብ ግምት ውስጥ ለማስገባት ግለሰቡ እንዳይታሠር ተደረገ። እንዲህ ዓይነቱ ውሳኔ ሕዝብን እና

[1] የዚህ ታሪክ ጸሐፊም በዚሁ መሥሪያ ቤት ተቀጥሬ ስሠራ አማካሪዬ የውጭ አገር ዜጋ ነበር።

መንግሥትን ማቀራረብ እንጂ ማራራቅ አይገባም ከሚለው የወርቅነህ የአመራር ስልት የመነጨ ነበር። በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት የመንግሥት ገቢዎች ሊሰበሰቡ የቻሉት፣ የመረጃ አሰባሰቡና አቀነባበሩ የተሠራው ጥንቁቅ፣ ቅን፣ ጠንካራና ታማኝ በሆኑ ሠራተኞች በመያዙ ነበር። ይህም፣ የሕዝብ አመኔታንና ግንዛቤን ከፍ ለማድረግ ረድቷል።

የሻለቃ ወርቅነህ የሕዝብ ፀጥታ መሥሪያ ቤት ሠራተኞች ከሠለጠኑት አገሮች፣ ከእንግሊዝ ኤም አይ ፮ (MI-6) እና ከእሥራኤል ሞሳድ (MOSAD) የፀጥታ ሠራተኞች ጋር የሚነጻጸር ችሎታና ብቃት እንዲኖራቸው ለማድረግ የተለያዩ እርጃምዎችን ወስዷል። ከዚህ መካከል አንዱ የአባዲና ፖሊስ ካዴት (ትምህርት ቤት) በኮሌጅ ደረጃ እንዲያድግ ለማድረግ የወሰደው እርምጃ ነበር። ይህንን ዕቅዱን ተግባር ላይ ለማዋል ከላይ የተጠቀሰውን ከነጋዴዎች የተገኘ ገንዘብና የአዲስ አበባ ወህኒ ቤት ከያዘው ሠፊ ቦታ በከፊል ለኮሌጁ ሕንፃ ማሠሪያ እንዲሆን የጃንሆይን ፈቃድ ጠይቆ ጃንሆይም በሐሳቡ ተስማምተው ገንዘቡና ቦታው ለታቀደው ኮሌጅ ሕንፃ ማሠሪያ እንዲውል ፈቃዳቸውን አግኝቷል። የፈቃዱ መገኘት መልካም ቢሆንም፣ ገንዘቡ ቶሎ በሥራ ላይ ሳይውል ቢቆይ ለሌላ ተግባር ሊታዘዝ ይችላል ብሎ በመሥጋት አፋጣኝ እርምጃ ወስዷል። እሱም አዛዡን በማነጋገር[2] እኔ ወደ አዲስ አባባ ወህኒ ቤት ሔጄ የወህኒ ቤቱን ኃላፊ የሻለቃ ብርሃኔ ወልደ የሱስን (በኋላ ሌ/ኮሎኔል)ን አነጋግሬ አጥሩን በሦስት ቀናት ውስጥ እንዳስፈርስ አዘዘኝ። ወደ አዲስ አበባ ወህኒ ቤት ሔጄ አዛዡን አግኝቼ ራሴን ከአስተዋወቅሁ በኋላ "ከሻለቃ ወርቅነህ ጋር በተነጋገሩት መሠረት አጥሩ ቶሎ እንዲነሣ ለማሳሰብ ተልኬ ስለመምጣቴ ስነግራቸው፤ እሳቸውም «በሚለቀቀው ቦታ ላይ ያሉ ሁለት የውሃ ጉድጓዶች በዚያው ስለሚቀሩ፣ በነሱ ምትክ የውሃ ጉድጓዶች ማስቆፈሪያና አጥር ማስነሻ የሚሆን ብር ፫ሺህ ፭፻ (ሦስት ሺህ አምስት መቶ) አስቀድሞ ካልተከፈለ፣ አጥሩን አላስነሣም» አሉ። ስለዚህ ወደ ሻለቃ ወርቅነህ ቢሮ ተመልሼ የተሰጠኝን መልስ ነገርኩ። ይሄን የሰማው የሻለቃ ወርቅነህ በመሥሪያ ቤቱ ገንዘብ ያዥና የምስጢር ጸሐፊው (በኋላ ምክትል ሚኒስትር) አቶ ትኩ አዳነን አስጠርቶ የተጠየቀው ገንዘብ ወጭ ሆኖ እንዲከፈል አደረገ። እኔም አጥሩን በማልስቱ ማስፈረስ እንዲጀምሩ አሳስቤአቸው ተመለስኩ።

በተነጋገርነው መሠረት በማልስቱ ጧት በአራት ሰዓት ስሔድ እቦታው ላይ አፍራሽ እሥረኞች ቢሰባሰቡም አጥሩ አልተነሣም። ሁኔታው አሳዝኖኝ «ለምን እስካሁን ሥራው አልተጀመረም?» በማለት የወህኒ ቤቱን «ጠቅላይ ካቦ»[3] ስጠይቅ ያገኘሁት ምላሽ የሚገርም ነበር። ጠቅላይ ካቦ የእሥረኞች የየሥራ ምድብ ኃላፊዎች (ካቦዎች) የበላይ የሆነው «የካቦዎች ካቦ» ነው። ይህ ጠቅላይ ካቦ እኔ የመንግሥት


---

[2] ከእኔ ጋር ቀደም ብለን የተነጋገርነው ያልነበረና ሥራውም ከፍሌን የማይመለከት ቢሆንም ትዕዛዙን ፈፀምኩ።


[3] ካቦ የሚለው ቃል ከጣሊያንኛ የተወረሰ በወህኒ ቤት የሚጠቀሙበት አለቃ ወይም ኃላፊ ማለት ነው።

ሠራተኛ ሆኜ፤ እሱ ደሞ እሥረኛ የነበረ ቢሆንም ሲያነጋግረኝ ግን ተጀንኖ ከንፈሩን ሸርመም አድርጐ በንቀት እያየኝ ነበር። ለጥያቄዬ ወዲያው መልስ ባለመስጠቱ ጥያቄዬን በድጋሚ ሳቀረብም አሁንም በትዕቢት ራሱን እየነቀነቀ መልስ አልሰጠኝ አለ። በመጨረሻም ቆጣ ብዬ «ምን ማለትህ ነው እራስህን እየነቀነቅህ መልስ የማትሰጠው» ብዬ ሳፈጥ፣ «ለራሳችሁ እኮ ነው የምታጠቡት» አለኝ። ምን ማለቱ ነው? እኔ ወህኒ ቤት ስገባ እንዳይጠበኝ ማለቱ ነው? ብዬ ግርም ብሎኝ መልስ ሳልሰጠው አጠገቡ ለነበሩት እሥረኞች ነግሬ ተመለስኩ። ይህን በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. በግንቦት ወር ብሎኝ በ፲፱፻፶፫ ዓ. ም. ታኅሣሥ ወር በተካሔደው በተለምዶ የታኅሣሡ ግርግር በሚባለው መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ሰበብ ተይዤ ታሥሬ ከሱ ጋር በመገናኘቴ ትንቢቱ ሲገርመኝ ይኖራል። ወደ መሠረተ ጉዳዬ ስመለስ የተጀመረው ሥራ የተሠራበትን ዐላማ ይዞ በመካሔድ ላይ እንዳለ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲቋቋም፤ ሕንፃው ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት ጽሕፈት ቤትነት እንዲውል መንግሥት በመሠጠቱ የፖሊስ መኮንኖች ኮሌጅ ከዚያ ወደሌላ ቦታ ተዛወረ።

ሕንፃው ለአፍሪካ አንድነት ደርጅት የተሰጠው ቀስ በቀስ ነፃ የወጡት አገሮች ቁጥር ሠላሳ በመድረሱ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መቋቋም አስፈላጊ እየሆነ በመምጣቱ ነበር። አፍሪካ ዓለም አቀፍ መሰብሰቢያ ሁና ለመመረጥ ዕድል አልነበራትም። በአፍሪካ ያሉት አገሮች የፖለቲካ ሁኔታ አመች ባለመሆኑ ነፃ የሆኑ አገሮች ከመበራከታቸው ጋር እርስ በርስ እየተገናኙ ስለጋራ ችግሮቻቸው በአፍሪካ ምድር መወያየት ግድ እየሆነ መጣ። ይሁን እንጂ የመሰብሰቢያ መቀመጫቸው የት ይሁን? በሚለው ጉዳይ ከእኔ አገር ይሁን፣ ከእኔ አገር ይሁን በማለት በአባላት መካከል ከፍተኛ ፉክክር ተፈጥሮ ነበር። አብዛኛዎቹ መሪዎች የዐፄ ኃይለ ሥላሴን የዕድሜ ባለፀጋነት፣ የቀዳሚ ብቸኛ ነፃ አገር መሪነት፣ በባል ሐሳብ አቅራቢነት በማሰብ፤ የሳቸውን ሐሳብ ተቀባይና ደጋፊ ነበሩ። ንጉሠ ነገሥቱ የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽንን አዳራሽ ሕንፃ አሠርተው ስለሰጡም መቀመጫው አዲስ አበባ እንዲሆን ድጋፍ ሰጡ። እንደዚያም ሆኖ ግን ከእኔ አገር ይሁን ከእኔ አገር ይሁን የሚለው የተቃዋሚው ቁጥር ቀላል አልነበረም። ይህ መሰናክል የታለፈው አቶ ከተማ ይፍሩ (የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር) እና ዶ/ር ተስፋዬ ገብረእግዚ (የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ) ሌት ተቀን ጥረትት ተፎካካሪዎችን የማግባባት ብርቱ ጥረትና ዘዴ ነው።



ከተማ ይፍሩ (የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር)




ዶ/ር ተስፋዬ ገብረ እግዚ (የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ደኤታ)

የኢትዮጵያውያኑ ጥረት ተሳክቶ በመጨረሻ የጽሕፈት ቤቱ መቀመጫ አዲስ አበባ እንዲሆን በድምፅ ብልጫ ሲወሰንም፤ የጽሕፈት ቤቱ ሕንፃ ጉዳይ ደግሞ ሌላ ደንቃራ ሆኖ ቀረበ። ሆኖም፣ ዕድሉ ከእጅ እንዳይወጣ ሲባል «ለአባዲና ፖሊስ ኮሌጅ ተብሎ የተሠራው ሕንፃና ግቢው ውስጥ ያሉት ቤቶች ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት ጽሕፈት ቤትነት እንዲውሉ መንግሥታችን ሰጥቷል» በማለት ጃንሆይ ስላበረከቱ ችግሩ በዚህ ተፈቶ፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ጽሕፈት ቤት በኢትዮጵያ ተቋቋመ።[4]

---

[4] በዚህ አጋጣሚ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በኢትዮጵያ ስለመቋቋሙ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ በነበርኩበት ጊዜ ኢትዮጵያ በዓለም የነበራትን ቦታ የሚለውጥ ከፍኛ ክስተት በመሆኑ ከጉዳዩ ጋር የተያያዘ ትውስታዬን ማንሣት እፈልጋለሁ። መቼም የድርጅቱ መቋቋም ታላቅ ዜና ሆኖ በዓለም በሰፊው በመሰራጨቱ ምክንያት ኢትዮጵያ በዓለም ካርታ የት ላይ እንደምትገኝ ለመፈለግ ከነመኖሯም እስቦ የማያውቀው ከፊሉ የዓለም ሕዝብ አሁን በካርታ ላይ ለይቶ ሊመለከታት ግድ ብሎታል። ይህ አስተያየት በተለይ አሜሪካኖቹን አስመልክቶ አግባብነት እንዳለው ራሴ ምስክር እሆናለሁ። ጐንደር ከተማ የስድስተኛ ክፍል ተማሪ ሳለሁ ከአማርኛና ከሒሳብ፣ ትምህርት በቀር ሌላውን ትምህርት ሁሉ አጠቃሎ የሚያስተምረን አንድ አሜሪካዊ መምህር ነበር። በክረምት ትምህርት ቤቱ ሲዘጋ ለሁለተ ወራት የዕረፍት ጊዜው ወደ አገሩ አሜሪካ ደረሶ ይመለሳል። ታዲያ ሁለት ወራት ቆይቶ ሲመለስ በዕረፍት ጊዜው ስላደረገው ስለሆነው ከነገረን የሚከተለው ላነሳሁት ጉዳይ ጥሩ ማሳያ ይሆናል።
«ከጐንደር አዲስ አበባ ሔድኩ። ከአዲስ አበባ ካይሮ፣ ከካይሮ ለንደን፣ ከዚያ ደግሞ ወደ ኒውዮርክ ሔጄ ከአውሮፕላን እንደወረድኩ ታክሲ ይዤ ወዳንድ ቦታ ለመሔድ ስነሣ ታክሲ ነጂው በጭውውታችን መኻል "ከወዴት ነው የመጣኸው?" አለኝ። "ከኢትዮጵያ" አልኩት። ከኢትዮጵያ? ኢትዮጵያ? አለና "ኦ! ኦ! አዎ ገባኝ ከኒውዮርክ እንደዚህ ካለው መንደር ወደ ውስጥ ገባ ብሎ ነው! ገባኝ ገባኝ" አለኝ። አያችሁ ኢትዮጵያ የት እንዳለች አትታወቅም።›› ሲል ከመካከላችን ብርሃኑ ሐሚድ የተባለ ተማሪ እጁን አውጥቶ መምህር አሁን ያልከው እኮ ትክክል አይደለም። እዚህ ላይ ለኔ የሚታየኝ የኢትዮጵያ ያለመታወቅ ሳይሆን የአሜሪካኖችን ጂኦግራፊ ያለማወቅን ነው አለው።



*ከተማ ይፍሩ (የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር)*



*ዶ/ር ተስፋዬ ገብረ እግዚ (የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ደኤታ)*



*የአፍሪካ አንድነት ድርጅት*

የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ሕንፃ አሠራርም ከወርቅነህ ጋር የተያያዘ ታሪክ ያለው እዚህ ላይ ማንሳት ያስፈልጋል። በ፲፱፻፶ዎቹ ዓመታት መጀመሪያ ነፃ የነበሩት አገሮች አንደኛ ኢትዮጵያ፣ ሁለተኛ ግብፅ፣ ሦስተኛ ላይበሪያ ነበሩ። ስለዚህም እነዚህ አገራት በአፍሪካ ካርታ እንደአልማዝ ፈርጥ፣ ብልጭ ብልጭ እያሉ የሚታዩ ነበሩ። የአፍሪካ ነፃነት ታጋይ አባቶች እነ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ኩዋሚ ንክሩማን (ከጋና)፣ ዶር ታፌዋ ባሌዋ (ከናጄሪያ)፣ አህመድ ሴኩቱሬ (ከጊኒ)፣ ጁሊየስ ኔሬሬ (ከታንጋኒካ ዛሬ ታንዛኒያ)፣ ኬኔዝ ካውንዳ (ከዛንቢያ) ወደ አዲስ አበባ እየመጡ በቅኝ አገዛዝ እጅ ያሉት የአፍሪካ አገሮች ነፃ መውጣት ጉዳይ ውይይት ማድረግና ለጋራ ትግል በጋራ

---

*እንግዲህ ይህ ታክሲ ነጂ ኢትዮጵያ በዓለም ካርታ የት እንዳለች እንዳላወቀው ሁሉ፤ ስለኢትዮጵያ የአፍሪካ መንግሥታት መቀመጫነት ሲነገር የማያውቋት ብዙ የዓለም ሕዝቦች አገሪቱ በዓለም ካርታ የት ላይ እንደምትገኝ እንዲፈልጉ ማነሳሳቱ አልቀረም።*



የአፍሪካ አንድነት ድርጅት

በመቆም "የጨለማው አህጉር" ይባል የነበረው የአፍሪካ አህጉር በጋራ ትግላቸው ጨለማው እየተገፈፈና የንጋት ብርሃን እየታየበት እንዲመጣ አደረጉት።[5]

በዚህ የነፃነት ትግል መሥራች አባቶች በአዲስ አበባ ተደጋግሞ መገናኘት በመካከላቸው መቀራረብና መተማመንን ፈጠረ። ይህ ግንኙነት መቀራረብና በአንድነት መቆም ቋሚና ዘላቂ እንዲሆን ለጋራ ጥቅም የሚሠራ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ጽሕፈት ቤት እንዲቋቋም፤ መሥሪያ ቤቱም የነፃነት ሰንደቅ በሆነችው በኢትዮጵያ ዋና ከተማ በአዲስ አበባ እንዲሆን የተባበሩት መንግሥታት የኤኮኖሚክና የሶሻል ኮሚቴ ወሰነ። አስተናጋጇ አገር ለዚህ የሚሆነውን ሕንፃ ቶሎ አሠርታ ትስጥ በመባሉም የኢትዮጵያ መንግሥት ሕንፃውን በፍጥነት አሠርቶ በማድረስ በተወሰነለት ቀን ተመርቆ ሥራውን ጀመረ። ኮሎኔል ወርቅነህ ይህ ሕንፃ በተያዘለት ቀን እንዲደርስ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ክትትል ሁሉ እንዲያደርግ ኃላፊነት ስለተሰጠው ሕንፃው የተጠናቀቀው እርሱ በምሽት ጭምር በቦታው እየተገኘ በማሾ መብራት እያሠራ ነበር።



*የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ሕንፃ*

ወደ ቀደመ ነገሬ ልመለስና፣ የተጠቀሰው የነጋዴዎች ጉዳይ እንዳለቀ፣ ፀጥታ መሥሪያ ቤቱ የተከታተለው ጉዳይ የኮሚኒዝም ሥርዓት ስለመስረጉና ለጃንሆይ ለምን ይህን ያህል ገንዘብ ይሰጣል? ተብሎ ስለተወራው ሀሜት ነበር። ስለጉዳዩ የፀጥታ

---

5 *ከአፍሪካ አንድነት ድርጅት መሥራች አባቶች ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቀደምት መሆናቸው እንዲህ ግልጽ ሆኖ እያለ ለእሳቸው መታሰቢያ አለመቆሙ ውለታ ቢስ ያደርገናል።*



*የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ሕንፃ*

ወደ ቀደመ ነገሬ ልመለስና፣ የተጠቀሰው የነጋዴዎች ጉዳይ እንዳለቀ፣ ፀጥታ

መሥሪያ ቤቱ የመረጃ ሠራተኞች የመጀመሪያውን ጉዳይ አጣርተው ያገኙት ደጐል አደባባይ አጠገብ ያለው የንግድ ባንክ አንድ ሠራተኛ በጊዜው ጥቂት የንግድ ባንክ ሠራተኞችን «ዕቁብ እንጠጣ» ብሎ አግባብቶ «የዕቁብ መተዳደሪያ ደንብ ነው» በማለት በሥራ ገበታቸው ላይ እንዳሉ ደንቡን የሚያነብ አስመስሎ በቃሉ ከገለጸ በኋላ ሲስማሙ ‹ፈርሙ› እያለ ያስፈረመበትን ሰነድ ነው:: ሰነዱ ላይ የተጻፈው ግን ይህን «ሪአክሽነሪ የመሬት ከበርቴ መንግሥት አስተዳደር ወጣቱ አጥብቆ ይቃወመዋል:: ሥሩም ፈንቅሎ ለመጣል ይፈልጋልና፤ የመስኮብ (የሩሲያ) መንግሥት መሣሪያ ለመስጠት እንዲተባበረው ይጠይቃል» የሚል ነበር ይህን ደብዳቤም እራሱ ለኤምባሲው ያስገባና ቅጂውን ለአሜሪካን ኤምባሲ ወስዶ ሲሰጥ በኢትዮጵያ የኮሚኒስት እንቅስቃሴ መሥረግ ጀምሯል፤ ፍንጩ ይኸውላችሁ:: ክትትሉን ለማስፋት ገንዘብ ያስፈልጋል" ብሎ ያስረዳል:: በዚህ መሠረት ለተባለው ጉዳይ ሥራ ማስኬጂያ የሚሆን ገንዘብ በአሜሪካ ኤምባሲ በሬዲዮ ቴክኒሻንነት ይሠራ በነበረ አንድ የግሪክ ተወላጅ በኩል እንደሚላክለትና የሚቀበልበት ቀንና ቦታ ተነግሮት ይመጣል:: ተላኪው የግሪክ ተወላጅ ግን ጉዳዩን አስቀድሞ ለሕዝብ ፀጥታ ጥበቃ መሥሪያ ቤት ስላሳወቀ፤ ገንዘብ ተቀባዩ በተቀጠረው ቀን ከግሪኩ ቤት ተገኝቶ ገንዘቡን ሲቀበል እጅ ከፍንጅ በፀጥታ አባሎች ተያዘ:: በሱ መሪነትም ደብዳቤውን የጻፈውና በሰነዱ ላይ የፈረሙት ዕቁብተኞቹም ጭምር በቁጥጥር ሥር ዋሉ:: ሆኖም ጉዳያቸው በአስቸኳይ ተጣርቶ ተንኮሉን የጠነሰሱትና ሰነዱን ያዘጋጀው ጸሐፊው ፍርድ ቤት ቀርበው የእሥራት ቅጣት ሲፈረድባቸው፤ ሌሎቹ ደግሞ በአጭር ጊዜ ቆይታ ነገሩ ተጣርቶ ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ ተደረገ::

የሁለተኛው ጉዳይ መነሻ ደግሞ በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም. በተደረገው የሕዝብ እንደራሴዎች ምርጫ ተመርጠው ምክር ቤት ከገቡት መካከል ጥቂት ሰዎች "ንጉሡ ለልዩ ልዩ ጉዳይ የሚያውሉት ተብሎ ስለቀረበ ስድስት መቶ ሺህ ብር ያሥነሱት ጥያቄ ነው:: ጥያቄው ንጉሡ ይህን ያህል ገንዘብ የሚወስዱት ለምን ሊያውሉት ነው? አይበዛም ወይ? የሚል ሲሆን፤ ጉዳዩን ለውይይት (ለክርክር) ፓርላማ ሊያቀርቡት እንደሆነ ለሻለቃ ወርቅነህ መረጃ ይደርሰዋል:: በዚህ ጊዜ የተጠቆሙትን የሕዝብ እንደራሴዎች አስጠርቶ «ለምን ይህን ያህል ገንዘብ ለጃንሆይ ይሰጣል ብላችሁ የያዛችሁት ጉዳይ በከተማው በሠፊው እየተወራ ነው:: ጊዜው አሁን አይደለም፤ የቸኮላችሁ መሰለኝ፤ ባንድ ጊዜ አናት ላይ ወጣችሁ:: ንጉሡ፣ 'ሕገ መንግሥቱን የሰጠናችሁ በፈቃዳችን ነው:: ምክር ቤት እንዲቋቋም ፈቅደን የሰጠነው እኛ ነን' እያሉ የእናንተ እርምጃ ቢያስቆጣቸውና ‹ምክር ቤቱን ዘግተነዋል!› ቢሉና ይህችን የመብት ብልጭታ ብታስጠፉአት ማንን ምን ትጠቅማላችሁ? አገር እኮ ነው የምትጎዱት» ብሎ በጥሞና አስረዳቸው:: የሕዝብ እንደራሴ አባላቱም በአቀራረቡና በምክሩ ተደስተውና አመስግነው ጉዳዩንም ደግመው ላያነሡ ቃል ገብተው ተመለሱ:: ይህም ሻለቃ ወርቅነህ የዲሞክራሲ ዐላማን ወደ ሕዝብ ለማስረጽ የነበረውን ፍላጎት ያሣየበት አንዱ አጋጣሚ ነበር::

ወርቅነህ የፀጥታ መምሪያ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ሆኖ ሥራ ከጀመረበት ፲፱፻፴፰ ዓ.ም. ጀምሮ፣ በሁኔታዎች አስገዳጅነት ሥራውን እስካቋረጠበት ጊዜ ድረስ፣ አንድም ሰው "በክብረ ነክ ወይም አስተዳደሩን ነቅፈሃል ወይም ባለሥልጣን አምተሃል" ተብሎ የተያዘ፣ የተጋዘ፣ በአደባባይ በጅራፍ የተገረፈ ወይንም የታሠረ ሰው ስለመኖሩ አልታየም፤ አልተሰማም። የሱ ሥራ ተቃዋሚ የሆኑ ግን ቀደም ብሎ ይሠራ እንደነበረው ባለማሠራቱ አድራጐቱን ይነቅፉ ነበር። እንደውም የመንግሥት ተቃዋሚ የሆኑትን ሁሉ ሕጋዊ እርምጃ እንዳይወሰድባቸው ይሸፍንላቸዋል፤ ይጋርድላቸዋል። ይህ አድራጎቱና ቀድሞ ነገር "ባህሪውም የኮሚኒስት ነው" እያሉ ያስወሩበት ነበር።


ሐሜቱ ሌላው ቀርቶ በግል ሕይወቱም ትዳር ያልመሰረተውና ልጅ ያልወለደውም "በሥርዓቱ ላይ ሥር የሰደደ ጥላቻ ስላለው ነው" አስብሎታል። ከልዑላን ቤተሰብ እንዲያገባ (በታጭታ ቀራቢ ዘመዶች ወርቅነህን ለማግባባት ሙከራ እየተደረገ ስለነበረ) የሁለት ታጭታ ልዕልቶች ቀራቢ ዘመዶች "እኔ አሳጭሻለሁ፣ እኔ አሳጭሻለሁ" በማለት በህታማቾች መካከል ፉክክር ይደረግ ነበር። ወርቅነህ ደግሞ እዚህ ውስጥ ላለመግባት ይጥር ነበር። ለዚህ ጥሩ ማሣያ የሚሆን እኔ ራሴ የነበርኩበትን አንድ ክስተት ልግለጽ። አንድ ቀን እሱና እኔ በሰዓት ከሥራ ወጥተን ምሳ ለመብላት መኖሪያ ቤቱ ስንሔድ፤ የቤት ሠራተኛው ወደ በሩ መጥቶ "እንግዶች አሉ" አለን። ወርቅነህ «የምን እንግዳ? እኔ የቀጠርኩት እንግዳ የለም። እነማን ናቸው?» ብሎ ጠየቀ። ሠራተኛውም «ልዕልት ዙሪያሽ ወርቅና ልዕልት ጊሩት ናቸው» አለ።[6] ይህን እንደሰማ ወርቅነህ «አስወጣልኝ! አስወጣልኝ! አስወጣ ነው የምልህ!» ብሎ ሠራተኛውም አዘዘ። ሠራተኛው ደንግጦ እንዴት አድርጐ እነዚያን ሰዎች ውጡ እንደሚል ተቸገረ። እኔም ነገሩን ሳላውቅ የመዳፈር ነገር መሰለኝና ደነገጥኩ። ቁጣውን ለማብረድም ሞከርኩ። «በምን መጡ? መኪናቸው የት አለ?» ብሎ እንደገና ሠራተኛውን ሲጠይቀው፤ «አድርሷቸው ሔደ» አለው። ከዚያም እኔን «በል፣ ያዝና ውሰድልኝ! ውሰድልኝ! ውሰድና አድርስልኝ!» ብሎ ሁለቱን ልዕልቶች ታጭታና አሳጭታዋን ይዤ ወደ ግርማዊት እቴጌ መነን ትምህርት ቤት (አሁን የካቲት ፲፪ ግቢ) አደረስኩ። ከዚያ ተመልሼ ወርቅነህን ወደ መሥሪያ ቤቱ ወሰድኩ። እንደዚህ ያለ ሁኔታ መፈጠሩን እኔ መልካም ዕድልና ከበሬታ ነው ብዬ በደህና ዓይን ዓየው ነበር። እሱ ግን «ከእሳቸው ቤተሰብ ጋር ልጋባ?» በማለት የከረረ ጥላቻን የሚገልጽ የቁጣ ቃል አሰማ። ሁኔታውም ገረመኝ።

እንዲህ ዓይነቱ ቀረቤታ በወርቅነህ በኩል የማይፈለግ ነበር። ነገር ግን አንድ ቀን ከንጉሡ «ልዕልት እገሊት እጮኛህ እንድትሆን ሰጥተንሃል» የሚል ትእዛዝ እንደሚመጣ በመገመት ሳይቀድሙኝ ልቅደም ብሎ፤ በጊዜው የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ የነበሩት ብላቴን ጌታ ዘውዴ በላይነህ ያሳደጓት የእህታቸው ልጅና የኮሌጅ ተማሪ

---

[6] ሌሎቹ ተወዳዳሪዎች ደግሞ ልዕልት ሶፊያ በልዕልት የሻሽ ወርቅ ይልማ በኩል እንደነበር ይሰማ ነበር።

የሆነችውን ወይዘሪት ፅፀገነት ዘውዴን ቶሎ ብሎ ዐጨ:: ንጉሡ ለጉብኝት ከኢትዮጵያ ውጭ ስለነበሩ እንደተመለሱ ስለሻለቃ ወርቅነህ ማጨት ሲሰሙ ቆጣ ብለው፣ «እኮ እንዴት? እኛን ሳታሳውቅ እንዲህ ያለ ነገር ታደርጋለህ?» ብለው ተቆጡ:: ስለዚህ ሁኔታ አንስቶ በነገረኝ ዕለት እግረ መንገዱን ሳይጠለፍ በማምለጡና ንጉሡን በማስቆጣቱ መደሰቱን ከሁኔታው መረዳት ቻልኩ::



*ወይዘሪት ፅፀገነት*

በቀለበቱ ሥነ ሥርዓት ላይ ከክብር ዘበኛ የመጡትን የ፲፮ ሚ.ሚ. የሲኒማ ፊልም ፎቶግራፍ አንሽዎችና ድምፅ ቀራጮችን እንዳስተባብር ተነግሮኝ ከመሥሪያ ቤቱ ሰዎች በሥነ ሥርዓቱ ላይ የተገኘሁ እኔ ብቻ ነበርኩ:: የቀለበት ማድረጉ ሥነ ሥርዓት ቀላልና ግርግር በሌለበት ሁኔታ ተፈጸመ:: ከዚያ ታጭታዋ እየመጣች ቤት ስታስተካክል ወሬው በከተማው ተዛመተ:: የወርቅነህ ሥጋትም በዚህ ቆመ::

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወይዘሪት ፅፀገነት ዘውዴ፣ ሚስተር ማጊ በተባሉ በአሜሪካ ኤምባሲ የፖለቲካ ክፍል ኃላፊ ተባባሪነት በነፃ ትምህርት (Scholarship) ወደ አሜሪካ እንድትሔድ ተደረገ::[7] አንድ ቀን ከውጭ የመጡትን ፖስታዎች እየከፈትኩ እንዳነብለት ስጥቶኝ ሳነብለት፤ ወይዘሪት ፅፀገነት አሜሪካ ከደረሰች በኋላ የጻፈችውን ደብዳቤ አገኘሁና የሱ የግል ደብዳቤ ስለሆነ ፖስታውን ሳልከፍት ስሰጠው ከፍቶ አነበበውና እኔ ሳላነበውና ምን እንደሚል ሳላውቅ «መልስ ጻፍላት» አለኝ:: «ምን ብዬ ልጻፍ?» ብዬ ብጠይቀው «ሰላምታ አድርገህ ስታበቃ በሐሳብሽ ወደዚህ አታተኩሪ፤ በዚህ ብዙ ተስፋ የለምና በትምህርትሽ መጠናከሩ ነው የሚበጅ፤ በሱ በርቺ:: ያገኘሽውን ዕድል ተጠቀሚበት» በላት አለኝ:: እኔም እንዳለኝ ጽፌ ረቂቁን ስጠሁትና ዓይቶት እንደገና ተጽፎ ተላከ:: ከዚያ በኋላ የሁለቱ ግንኙነት ተቋረጠ:: ወ/ሮ ፅፀገነት ስለግንኙነቱ ስትናገር:-

> *መጀመሪያ የተገናኘነው ከፊታውራሪ ኃይለ ሚካኤል ዘውዴ ቤት በሻሂ ግብዣ ላይ ሲሆን፤ መተጫጨቱ ውስጥ የገባነው ወዲያውኑ ነበር:: ብዙም ሳንቆይ ቀለበት አሠርን:: ከዚያ በኋላ አልፎ አልፎ ወደሱ ቤት እሔድ ነበር:: ይሁን እንጂ፣ የሱ በሥራ መወጠር፣ ከቤት ሲመጣም የእንግዳው ብዛትና የስልክ ጥሪው አለመቋረጥ፤ ከኔ ጋር ተረጋግቶ*

[7] *እሷ ግን በራሷ ጥረት ነው ያገኘሁት ትላለች::*



ወይዘሪት ፅፀገነት

ለመጫወት ይቅርና የቀረበለትን ምግብ እንኳን አጣጥሞ ለመብላት ፋታ አልነበረውም:: ባጭሩ፣ በተፈጥሮው አእምሮው ለሥራ እንጂ ለመዝናናት የታደለ አልነበረም:: በዚህ ምክንያትም ተዝናንቶ የሚያዝናናው ጓደኛና ወዳጅ አልነበረውም::

ከኔ ጋር ለብቻችን ሆነን የተጫወትንበት ጊዜ ቢኖር፣ ለኮሎኔል እምሩ ወንዴ ሠርግ ሆለታ አብረን የሔድን ጊዜ ብቻ ነው:: ያን ዕለትም ቢሆን ጨዋታችን ዘና የሚያደርግ ዓይነት አልነበረም:: እስታውሳለሁ ከቤቱ (አሁን ጦር ኃይሎች ሆስፒታል ከሆነው አጠገብ) ምሳ በልተን፣ እሱ እየነዳ እኔ ከጐኑ ተቀምጬ ፫ኛ ፖሊስ ጣቢያ አጠገብ ወደነበረው ቢሮ ደርሶ ለመሔድ፤ መናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ስንደርስ ሁለት ጎስቆል ያሉ አርበኞች ሲያይ መንፈሱ ደፈረሰ:: ራሱን እየነቀነቀ ካዘነ በኋላ፤ እኔ በኃላፊነት ተጠያቂ እንደሆንኩ ሁሉ ወደኔ መለስ ብሎ፤ ቫምን እንደዚህ ይሆናል? ለምን እንዲህ ይደረጋል?" በማለት አዘነ:: ከዚህ በኋላ፥ ሆለታ እስከምንደርስ ድረስ ጭውውታችን እንደ መጀመሪያው የለሰለሰ አልነበረም:: አሁን መለስ ብዬ ሳስበው ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ የወገን ፍቅር የሚያንገበግበው እንደነበርና ከግል ሕይወቱ ይልቅ የአገር ጉዳይ ይበልጥ ያሰጨንቀው እንደነበር ለመረዳት ችያለሁ:: በዚህ ልዩ ባህሪውም ባጭር ሊቀጭ በቃ::[8]

በማለት ታስታውሰዋለች::

[8] ከብዙ ዓመታት በኋላ በ፲፱፻፹፯ ዓ.ም. ከወይዘሮ ዕፀገነት ዘውዴ ጋር ሎስአንጀለስ ካሊፎርኒያ ቅድስት ልደታ ማርያም ቤተክርስቲያን ተገናኝተን ስለኮሎኔል ወርቅነህ የነገረችኝ

## የአስተዳደር ሥርዓት የመለወጥ ጥረት

በዓለም ላይ በብዙ አገሮች ከሁለተኛው ጦርነት በኋላ የፍጹም ዘውዳዊ መንግሥት ሥልጣን (በሕግ ያልተገደበ አስተዳደር ሥርዓት) የመቀየር እንቅስቃሴ እየተጠናከረ መጣ:: በፍጹም ዘውዳዊ አገዛዝ ይተዳደሩ ከነበሩት አገሮች ስፔይንና ጃፓን ወዘተ የመሳሰሉት የጊዜውን የዓለም የፖለቲካ ሒደትና ሕዝቡ ለዲሞክራሳዊ ለውጥ ያለውን መነሣሣት እያዩ የአስተዳደር ሥርዓታቸውን ቀስ በቀስ ወደ ዴሞክራሲያዊ (ፓርላሜንታሪያን) ዘውዳዊ አስተዳደር ለወጡ:: በአንጻሩ ኢትዮጵያ፣ ሳውዲ አረቢያ፣ ኢራንና የመሳሰሉት ደግሞ በፍፁም ዘውዳዊ አገዛዝ ሥርዓት ቀጠሉበት:: እንዲህ ዓይነቱ ሥርዓት ይዋል ይደር እንጂ ጊዜውን ጠብቆ በውድም ይሁን በግድ ወደ ሕገ መንግሥታዊ አስተዳደር ሥርዓት መለወጡ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በቀር አይቀሬ መሆኑ ይገመት ጀምረ:: በተለይ በአገራችን በወቅቱ በመንግሥት ሥልጣን ዙሪያ የነበሩ ልዑላን መሳፍንት፣ መኳንንት፣ ሚኒስትሮችና የጦር አዛዦች የአገር አለኝታ ክብርና ኩራት የሆኑትን ያህል፤ ከባድ በሆኑ አራትና አምስት በሚሆኑ የተለያዩ ቡድኖች ተከፋፍለው የዕለት ተዕለቱን የአስተዳደር ሥራ የተወሳሰበና አቅጣጫውን ያጣ (ኮምፓስ የሌለው መርከብ) እስኪመስል ይንጡት ነበር:: ይህም የሥርዓት ለውጡ አይቀሬነት ማሣያ ነበር:: የየቡድኑ አባላት አብዛኞቹ ፀሐይ በተፈጥሮ ሕግ ጠዋት ወጥታ ማታ እንደምትገባ ሁሉ እነሱም ከዕለት ተዕለት ውሎና አዳር ያለፈ ስለአገር ዕድገትና ስለሕዝብ ብልፅግና አርቀው የማያዩና የማይጨነቁ፤ ከዓለም ወቅታዊ ሁኔታ ጋር የተገናዘበ የዕድገት ራዕይ ያልነበራቸው ነበሩ:: ንቃተ ኅሊናቸው ከፍ ያለውና የዓለም ወቅታዊ ሁኔታን ተንትነው ያወቁት ደግሞ አገሪቱ እየተመራች ያለችበት ሥርዓት ወደፊት ሊያደርስ የሚችለው ችግር ያሳስባቸውና ያስጨነቃቸው ነበር:: የችግር መፍቻ ብልሃቱም ዕውቀቱም በጣታቸው ጫፍ እያለ፣ የሚያምኑበትን የለውጥ ሐሳብ ለንጉሡ አቅርቦ ለማስወሰን ድፍረትን በማጣት ይዘውት ኖሩ::

ሻለቃ ወርቅነህንም ለለውጥና መሻሻል የሚያነሳሱት በርካታ ምክንያቶች ነበሩት:: እነርሱም

፩. በኮርያ ዘመቻ ጊዜ ከተባበሩት መንግሥታት ከፍተኛ የጦር አዛዦች ጋር ባደረጋቸው ብዙ ስብሰባዎች የቀሰመው ቆራጥ የውሳኔ አሰጣጥና ክትትል፣

፪. ለሕክምናና ለዕረፍት "ሴኡልና ቶኪዮ" በሔደበት ጊዜ የየአገሮቹን የሥልጣኔ ዕድገት፣ የመንግሥት አስተዳደር ሥርዓት፣ የሕዝብ ብልጽግና እንዲሁም ለዘመቻው ከተለያዩ አገሮች ከመጡ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች ጋር ስለየአገራቸው በግል ካደረገው የሐሳብ

ልውውጥ ስለደረሱበት የሥልጣኔ ዕድገት የተረዳውን ከአገሩ ዕድገትና ሥልጣኔ ጋር እያወዳደረ ያገኘው ልዩ ልዩ ግንዛቤ፣
፫. በስዊድን ከፍተኛ የነገረመረጃ ትምህርትና ሥልጠና ይከታተል በነበረበት ጊዜ፣ ትምህርቱ ያካተታቸውን የአገር ኤኮኖሚ ፖለቲካና ማኅበራዊ ተቋም ላይ ሊሠራ የታሰበን ደባ ከመድረሱ በፊት ቀድሞ ደርሶ ማክሸፍና እየደረሰ ከሆነም ጉዳቱ የቀለለ እንዲሆን አስፈላጊውን መከላከል በማድረግ የደህንነት ሥራ ጉዳዮች ያስጨበጡት ግንዛቤዎች፣
፬. በስዊድን የሕዝብ ሰላም፣ ፀጥታና ብልፅግና፣ መድሎ የለሽ አስተዳደር ሒደት ያሳደረበት የአገርና የወገን ፍቅር፣
፭. ከግርማዊ ጃንሆይ ጋር ወደ ተለያዩ ብዙ አገሮች ለጉብኝት ስለሔደ ባያቸው አገሮች ሁሉ የታዘበውን የመንግሥት አስተዳደር ሥርዓት፣ የፀጥታ ጥበቃ መሥሪያ ቤት አቋምና ተግባር፣ የሕዝብ የሥልጣኔ ዕድገት ብልፅግና፣ መንግሥት ከሕዝቡ ጋር ተግባብቶ የሚተዳድርበት ሥርዓትና ሥልት ያስጨበጠው ከፍተኛ ዕውቀት ሁሉ ለለውጥ እንዲነሣሣ ገፋፍቶታል ማለት ይቻላል::

በአጠቃላይ ወርቅነህ ይህን ሁሉ ያካተተ ሠፊና በሳል አመለካከትና አስተሳሰብ በመጨበጡና ከንጉሡ ጋር በነበረው ቅርበት፣ ፍቅርና ተሰሚነት ተማምኖ የአገሩ የመንግሥት ሥርዓት በውጪ እንዳያቸው አንዳንድ መልካም አስተዳደር እንዳላቸው አገሮች በተሟላ መልኩ እንኳ ባይሆን በሚቀራረብ ደረጃ የሕዝቡን ኑሮና አስተዳደር ያሻሽላል ብሎ በሚያምንበት የመንግሥት አስተዳደር ሥርዓት እንድትመራ ከፍተኛ ጥረት ያደርግ ነበር:: በዚህ መሠረት የፍጹም ዘውዳዊውን ሥርዓት ወደ ሕገ መንግሥታዊ ዘውዳዊ አስተዳደር ሥርዓት ለማስለወጥ የተለያዩ ማስታወሻዎችን አቅርቧል:: ወርቅነህ አቅርቧቸው የነበሩትን ማስታወሻዎች ቀጥሎ እናያለን::

## የመንግሥት ሥርዓት ለውጥ ሙከራ

ወርቅነህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ካስቆጠራቸው ረጅም የታሪክ ዘመናት አንጻር ሲመዘን የሚገኝበት የኑሮ ደረጃ ዝቅተኛ መሆኑ ያሳስበው ነበር። ለዚህ ነው ከዚህ ችግር ለመውጣትና በአጭር ጊዜ ለማሳደግ የውጭ ባለሀብቶችን መዋዕለ ንዋይና ቴክኖሎጂ ወደ አገር አስገብቶ ከአገሪቱ ሕዝብ ሀብትና ጉልበት እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብት ጋር አቀናጅቶ በሥራ ላይ ማዋል የኢትዮፊያ መንግሥት የትኩረት አቅጣጫ ሊሆን እንደሚገባ ለንጉሡ ነገሥቱ አጥብቆ ያስረዳው:: ለዚህም ፈጣን የዕድገት ፍለጋ እንቅስቃሴ

ጃፓን የተመራችበትና በአፋጣኝ የዕድገት እመርታ ያገኘችበት ስልት የተሻለ አማራጭ ስለሆነ፤ የእርሷን ፈለግ ብንከተል ከተመኘነው ግብ እንደርሳለን:: ብሎ ለንጉሠ ነገሥቱ ማስታወሻ አቅርቦ ይሁንታን አግኝቷል::

ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ወርቅነህ በምሥጢር ወደ ጃፓን ሒዶ ከመንግሥት ባለሥልጣኖች ጋር በልዩ ልዩ አርዕስተ ጉዳዮች ላይ ተነጋግሯል:: በውይይቱ ራሳቸውን ጠቅመው አገሪቱንም ለመጥቀም ፈቃደኛ ለሆኑ የጃፓን ባለሀብቶች ኢትዮጵያ በሯ ክፍት መሆኑንም ለባለሥልጣኖች ገልጾአል:: የጃፓን መንግሥት ባለሥልጣኖችም በበኩላቸው የአገሪቱ ሕጐች ለውጭ ባለሀብቶች አመቺ እንዲሆኑ ከተደረገ የጃፓን ባለሀብቶች ገንዘባቸውንና ቴክኖሎጂያቸውን በኢትዮጵያ በሥራ ላይ እንዲያውሉ ማድረግ የሚቻል መሆኑን አረጋግጠውለታል። በማያያዝም የኢትዮጵያ መንግሥት ላዕላይ መዋቅር ከጃፓን እና ከእንግሊዝ ሕገ-መንግሥታዊ የዘውድ አስተዳደር መዋቅር ጋር የተመሳሰለ አደረጃጀት እንዲኖረው ቢደረግ ለአገሪቱ የዕድገት እርምጃ መፋጠን አመቺና አጋዥ ሊሆን እንደሚችልም ገለጸውለታል:: ቀጥለውም ሐሳቡ ተቀባይነት ካገኘ እንዴት ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል ለማጥናትና የጥናቱን ውጤት በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልገውን የገንዘብ ወጪ ለመሸፈንም የጃፓን መንግሥት ፈቃደኛ እንደሆነ አረጋግጠውለታል::

ወርቅነህ በጃፓን መንግሥት ባለሥልጣኖች የቀረበው ሐሳብና የትብብር ዝግጁነት ስላስደሰተው፣ ከዚያ እንደተመለሰ የሥርዓት ለውጥ ሽግግሩን ከጃፓኖች ሊገኝ ከሚችለው ከፍተኛ የኢኮኖሚ ትብብርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ጋር በማያያዝ የውይይቱን ፍሬ ሐሳብ ለንጉሠ ነገሥቱ አቅርቦ ጉዳዩ ይጠና ዘንድ የይሁንታ ውሳኔ አገኘ:: ይህንኑ መልካም ውሳኔ ለጃፓን መንግሥት ባለሥልጣኖች ስላስታወቀ፤ የጃፓን መንግሥትም የኢትዮጵያ ፍፁማዊው ዘውዳዊ ሥርዓት፣ ደረጃ በደረጃ እየተለወጠ ወደ ሕገ መንግሥታዊ ዘውዳዊ አስተዳደር ሥርዓት ሊገባ የሚችልበትን መንገድ ለመቀየስ ጥናት የሚያደርግ፣ ሌሎች ነገሮችንም በማከል ባለ ሀብቶች ሊሳተፉ የሚችሉበትን መንገድ የሚያመቻች በጄኔራል ሲሙትሱ ኢኬዳ የሚመራ ስድስት አባላት የሚገኙበት አጥኚ ቡድን በ፲፱፻፵ ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ ላከ:: አጥኚው ቡድኑ ኢትዮፊያ እንደገባ የጥናት መነሻ ነጥቦችን አንሥቶ የአጥኚው ቡድን ተግባር እንዴት መሆን እንዳለበት ከንጉሡ ጋር ተወያየ:: በውይይቱም በመጀመሪያ የአገሪቱን አጠቃላይ ሁኔታ ማየትና በዚያ ላይ የተመሠረተ ሪፖርት ማቅረብ፣ አለዚያም በቅድሚያ አስቸኳይ በሆኑ ልዩ ልዩ የመንግሥት የሥራ መዋቅሮች ላይ የማሻሻያ ጥናት አድርጎ ሪፖርት ማቅረብ የሚሉ አማራጭ ሐሳቦች አቀረበ:: በዚህ መሠረት ንጉሡ "በመንግሥቱ ልዩ

ልዩ የሥራ ዘርፎች ላይ ቅድሚያ ጥናት ይደረግ" የሚለውን መርጠው ሥራውም በአፋጣኝ እንዲጀምር አዘዙ፡፡ አጥኝው ቡድን ቅድሚያ ሰጥቶ ያተኮረባቸው የመንግሥት የሥራ መዋቅሮችም መከላከያ፣ አማካሪ ቦርድ (ልዩ ካቢኔ)፣ ማዕከላዊ የመረጃ ተቋም፣ የዋና ኦዲተር፣ መሠረታዊ ትምህርት፣ ጡረታና ዕቃ ግዥ ነበሩ፡፡

የአገር መከላከያን በሚመለከት፤ መሥሪያ ቤቱ ቀልጣፋ ስለሚሆንበት፣ የመከላከያ ሚኒስትሩና የኤታ ማዦር ሹሙ የሥራ ድርሻ ተለይቶ ስለሚታወቅበት፣ የጦር መኮንኖች ጡረታ መውጫ ዕድሜ ተወስኖ፣ በዕድሜ የገፉትን መኮንኖች በጡረታ በማውጣት በወቅቱ የነበረውን የተዳከመ የሚሊቴሪ መንፈስ ማነቃቃት፣ በጡረታ የሚወጡት መኮንኖች ኑሮአቸውን የሚደግፉበት አርሰው የሚተዳደሩበት መሬት ቢሰጣቸው ለጦሩ ሞራል መነቃቃት በእጅጉ ስለሚረዳ በዚህ መሠረት መፈጸም ጠቃሚ ስለመሆኑ፣ በመከላከያ ኃይሉ ውስጥ በተለይ በምድር ጦሩ እንዲያገለግሉ እየተመረቁ የሚወጡት መኮንኖች ሁለት የተለያየ ደረጃ ካላቸው ተቋማት መሆኑ ለአንድ ዐላማ በኅብረት ለመቆም እንቅፋት ስለሚሆን የጦር መኮንን ማሠልጠኛዎች ተመሳሳይ ደረጃ ያላቸው እንዲሆኑ፣ ኢትዮጵያ በኢኮኖሚዋ አለመጠንከር ምክንያት በየጊዜው የሚያስፈልጋትን ያህል ሙሉና ብቁ የሆነ የመከላከያ ሠራዊት ቀጥራ ለማስተዳደር ስለማትችል ኑሮው በግብርና ላይ የተመሠረተ ሆኖ ሲፈለግ ብቻ የሚጠራ የገበሬ ጦር ሊኖራት እንደሚያስፈልግ የሚገልጽ ጥናት አቀረበ፡፡

የአማካሪ ቦርድ (ልዩ ካቢኔን) በሚመለከትም፣ ንጉሠ ነገሥቱን እጅ ለመንሣትና አንዳንድ ጉዳዮችን ለማስፈፀም ቤተ መንግሥት ቆመው የሚያረፍዱትን ከፍተኛ ባለሥልጣናት የሥራ ጊዜ በተቻለ መጠን ለማካካስ ከልዩ ልዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ከአቤት ባይ ግለሰብ የሚመጣውን ጉዳይ በሚገባ እያጣሩና የራሳቸውን አስተያየት እያከሉ የውሳኔ ሐሳብ የሚያቀርቡ፣ በልዩ ልዩ ሙያ የሠለጠኑና በንጉሠ ነገሥቱ ብቻ የሚታዘዙ አባላትን የያዘ አንድ ልዩ የንጉሠ ነገሥቱ አማካሪ ቦርድ (ልዩ ካቢኔ) ማቋቋም፣ ለሥራ ቅልጥፍናና ለውሳኔ ጥራት የሚጠቅም መሆኑን አመለከተ፡፡ ልክ እንዲሁ ማዕከላዊ የመረጃ ተቋምን በሚመለከት ደግሞ፣ የአገሪቱን የፀጥታ ሁኔታ አጠቃልሎ የሚመራና ስለማናቸውም ችግር እያጠና የመፍትሔ ሐሳብ የሚያቀርብና አጣዳፊ ነገር ቢያጋጥም ተገቢ እርምጃም የሚወስድ ራሱን የቻለ መሥሪያ ቤት የመኖሩን አስፈላጊነት፤ እንዲሁም ይህ መሥሪያ ቤት ቀጥታ ተጠሪነቱ ለንጉሠ ነገሥቱ የሆነ ኃላፊ እንዲኖረው ሆኖ በተጠናከረ ሁኔታ እንዲቋቋም ማስፈለጉን አሳሰበ፡፡

ሌላው ጥናቱ አፅንኦት የሰጠው ጉዳይ የሕዝባዊ መሠረተ ትምህርትን ለዕድገት አስፈላጊነት አስመልክቶ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘጠና አራት በመቶው ማንበብና መጻፍ የማይችል መሐይም መሆኑ፤ መንግሥት ለአገሪቱ ዕድገት በሚቀይሰው ፕሮግራም የተሳታፊነቱን መጠን ስለሚቀንሰውና ለዕቅዶችም አፈጻጸም

መሰናክል ስለሚሆን፤ ሕዝቡ ከዚህ ሁኔታ ሊላቀቅ የሚችልበት የመሠረተ ትምህርት ፕሮግራም ተቀይሶ፣ በራዲዮ፣ በሲኒማና በመሳሰሉት የብዙኃን መገናኛዎች አማካኝነት ጭምር ሕዝቡን በማስተማር አብዛኛው ሕዝብ በአጭር ጊዜ ውስጥ ማንበብና መጻፍ ችሎ በማናቸውም የዕድገት ፕሮግራም ቀየሳና አፈፃፀም የበለጠ ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ ጠቃሚና አስፈላጊ መሆኑን ነው።

ጥናቱ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን የሥራ አመራር፣ የሀብትና የንብረት ሁኔታ እየተቆጣጠረ ውጤቱን ለንጉሠ ነገሥቱና ለፓርላማው ብቻ የማቅረብ ኃላፊነት የሚኖረው፣ እራሱን የቻለ የጠቅላይ ኦዲተር ተቋም የመኖሩን አስፈላጊነትም አመልክቷል። የጡረታና የመንግሥት ዕቃ ግዢ ድርጅቶችን በሚመለከትም፣ በወቅቱ በአገሪቱ የጡረታ አገልግሎት አለመኖሩን በመረዳት በአስቸኳይ የጡረታ ሕግ ማውጣትና ዕድሜአቸው ለጡረታ ብቁ የሆኑ የሲቪልና የሚሊተሪ አባላት በጡረታ እንዲገለሉ እየተደረገ፣ ሥራው ትኩስ ኃይል በሆነው ምሑር በወጣቱ እንዲካሔድ ማድረግ ከፍተኛ የዕድገት እመርታ ሊያስገኝ ስለሚችል፣ ጊዜ ሳይሰጠው ተግባራዊ እንዲሆን ሐሳብ አቀረበ። ከዚህ በቀር፣ ልዩ ልዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከአገር ውስጥና ከውጭም የሚገዟቸውን ዕቃዎችና መገልገያዎች፤ በጅምላ በማዕከላዊነት እየገዛ በማደራጀትና በማከፋፈል የጊዜ፣ የጉልበትና የገንዘብ ብክነትን የሚያስወግድ፣ አንድ ማዕከላዊ የመንግሥት ዕቃ ግዥና ማከፋፈያ ተቋም ማደራጀት እንደሚጠቅም በማመልከት፤ ቡድኑ ጥናቱን አጠናቆ በእንግሊዝኛ የተጻፈ ፲፫ ገጽ ዘገባ ለሻለቃ ወርቅነህ አቀረበ።

ሻለቃ ወርቅነህም የቀረበለትን ዘገባ ለንጉሠ ነገሥቱ ውሳኔ በሚያመች ቅጽ (ፎርም) በአማርኛ ቋንቋ በ፸፮ ገጽ አሳጥሮ አቀረበ። ይሁን እንጂ ንጉሠ ነገሥቱ ይህን ጉልበትና ገንዘብ የፈሰሰበትን የምሑራን አዕምሮ ጭማቂ ጥናት በተለመደው በጉዳይ መግደያ ዘዴአቸው ውሳኔ ሳይሰጡ በዝምታ ዘጉት። ብዙ ታላላቅ ጉዳዮችን የሚመለከት ጥናት ያካሒዳሉ ተብለው ተስፋ የተጣለባቸው የጃፓን አጥኚዎች ቡድንም ወደፊት ይደረጋል ተብሎ የታሰበው ፍፁም ዘውዳዊውን መንግሥት፤ ወደ ሥልጣኑ በሕግ የተገደበ የመንግሥት ሥርዓት ለውጥ መቀጠሉ ይቅርና በነዚህ መለስተኛ የሥራ የማሻሻያ ሐሣቦች ላይ እንኳ ውሳኔ ሳይሰጥ ረጅም ጊዜ መውሰዱ ተስፋ ስላስቆረጣቸው "በከንቱ የምናባክነው ጊዜ የለንም፤ አገራችን ትፈልገናለች" ብለው ፕሮግራማቸውን አቋርጠው ወደ አገራቸው ለመመለስ ተገደዱ።

የጃፓኖቹ ምሑራን ጉዳይ እንዲህ ሆኖ ከተፈፀመ በኋላ ሻለቃ ወርቅነህ ከአልጋ ወራሽ ጋር ግንኙነት ለማድረግ ሞከሯል።[9] በመቀጠልም የፈረንሣይን አብዮት ታሪክ አስተርጉሞና የራሱንም አስተያየት ጨምሮ ለንጉሡ ማስታወሻ አቀረበ። ይህንንም ለእኔ ከነገረኝ የታሪክ መጽሐፍ ውስጥ ቁምነገሩን እንደሚከተለው

[9] ወደፊት የሔድንበትን ምክንያት የምዘረዝረው ሆኖ ደብረ ዘይት ሔደን ስንመለስ ለእኔ እንደነገረኝ ለጄኔራል መኮንንም ከነገራቸው

አስታውሳለሁ:: ታሪኩም እንዲህ ነበር:: ፈረንሳይ እስከ ሉዊ ፲፩ኛው መንግሥት ፍጻሜ ድረስ በአውሮፓ ገናᎈ ተከብራና ተፈርታ የኖረች አገር ነበረች:: ከሉዊ ፲፩ኛ መንግሥት በኋላ ግን የነበራትን ክብር እያጣች እየደከመች ሔደች:: በሉዊ ፲፩ኛና ከዚያም ቀጥሎ ፈረንሣይ ባካባቢዋ ብዙ ጦርነቶች አካሒዳ ስለነበር፤ ለጦርነት ማስኬጃ መንግሥት ከባለሃብቶች ብዙ ገንዘብ ተበድሮ ነበር:: ስለዚህ አበዳሪዎች ከሉዊ ፲፮ኛ መንግሥት ዘመን በፊት ጀምሮ መንግሥት የተበደረውን ገንዘብ እንዲከፍል ሲጠየቅ አገሪቱ በሁሉም ዘርፍ ተዳክማ የመንግሥት ካዝና ተራቁቶ ስለነበር እዳውን ለመክፈል በመቸገሩ በሕዝብ ላይ ተጨማሪ ግብር ለመጣል ዐዋጅ ዐወጀ::

ከዚህ በኋላ ነው የዋናው ከተማ አካባቢ ሕዝብ ከቤተ መንግሥቱ አጠገብ ተሰብስቦ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባሎች ጉዳዩን ዐውቀው ተነጋግረው ያላሳለፉትን ውሳኔ "ንጉሡ በራሱ ፍቃድ ተነሣስቶ ዐዋጅ ሊያውጅና በሕዝብ ላይ ግዴታ ሊጥል አይችልም" በማለት ተቃውሞ ያነሣው:: የተሰበሰበው ሕዝብ ወደ ቤተ መንግሥት ተጠግቶ ስለችግሩ «አቤት!» «አቤት!» ሲል ወሬው በሥፋት ተዳርሶ፤ በየአገሩ ያለው ሕዝብ ግልብጥ ብሎ በመምጣት ከአቤት ባዩ ሕዝብ ጋር ተቀላቅሎ ያቤት ባዩን ኃይል አገዘፈው:: የተማረውና መሀል ሠፋሪው ደግሞ ከዚሁ አቤቱታ ከሚያሰማው ሕዝብ ጎን ወግኖ በመቆም የፈረንሣይ መሬት ከአምስት እጅ ሁለቱ በመኳንንትና በካህናት ይዞታ ሥር ስለሆነ፤ ካህናቱና መኳንንቱ እንደማንኛውም ሕዝብ ግብር መክፈል አለባቸው፤ ኢንዱስትሪውም በተወሰኑ ሰዎች እጅ ብቻ መያዙ ቀርቶ ለሕዝብ መለቀቅ አለበት በሚል መወትወት ያዘ:: ባገሪቱ የፍትሕ መጓደልᎈ የአስተዳደር በደልᎈ የመኳንንቱና የቤተክህነት ኃላፊዎችም ጭምር ለግል ጥቅም ከመሯሯጥ ሌላ የሕዝብን ኑሮ በሚመለከት የመከሩትና ያሻሻሉት ይህ ነው የሚባል የተሠራ ሥራ ስላልነበር፤ የድሃው ሕዝብ ንዴት እየጋለ ሔደ::

መጀመሪያ ላይ ተቃውሞው "ተጨማሪው ግብር ይነሳልን" ለማለት ነበር:: ቀስ እያለ ግን በቁጥር ከበዛንና እየተጠናከርን ጉልበትም ካገኘን ዘንዳ ብሎ ሌላ ወደማሰብ ተሸጋገረ:: እውነትም የዘውድ አስተዳደር ከራሱ ጥቅም ውጭ ለሕዝብ ምንም አላደረገም:: ንጉሡ ጊዜውን ለአደን ከማዋልᎈ ንግሥቲቱም ለውበትና ለደስታ ከመጣር የዘለለ የሕዝቡን ችግር የሚያዩና የሚፈቱ ሆነው አልተገኙም:: ስለዚህ "የመንግሥቱን ሥርዓት መለወጥ አለብን:: ከእንግዲህ በዘውድ ሥርዓት መተዳደር የለብንም" የሚል አቋም ያዘ:: በዚህ መኻል ሕዝቡ በብዛትና በአንድ ቦታ በመሰንበቱ ረሃብ ጸንቶበት «ዳቦ!» «ዳቦ!» እያለ ጮኸ:: ንግሥቲቱም ይህን እንደሰማች በቤተ መንግሥቱ ሰገነት ብቅ በማለት «ሕዝቡ ምን ብሎ ነው የሚጮኸው» ብላ ጠየቀች:: «ዳቦ!» «ዳቦ!» እያለ ነው የሚጮኸው አሏት:: «ታዲያ ዳቦ ለምን አይበላም» አለች:: «ዳቦ የለም» አሏት:: «ታዲያ ዳቦ ከሌለ ለምን ኬክ አይበላም» አለች ተባለ:: ንግሥቲቱ ይህን ያለችው እጦትን ባለማወቋ ነው:: ሕዝቡ ግን ይሄን አነጋገሯን

እንደማባጨት[10] ተመለከተው። ስለዚህ ሲብሰለሰል ከቆየ የተጠራቀመ ብሶቱ ላይ ይህን ማለቷ ሲጨመር የሕዝቡ ቁጣ ገንፍሎ ሆ! ብሎ ለዐመፅ ተነስቶ ወደ ቤተ መንግሥቱ ውስጥ በማምራት ንጉሡን ሉዊ ፲፮ኛን ከቤተ መንግሥቱ ጎትቶ አውጥቶ አንገቱን በጊሎቲን ቀላው። ቀጥሎም ንግሥቲቱን፣ መሳፍንቱን፣ መኳንንቱንና የችግሩ ምንጮች ናቸው ያላቸውን ሁሉ ከያሉበት ለቅሞ በመያዝ ለፍርድ እያቀረበ በተመሳሳይ ሁኔታ ከጨረሰ በኋላ የፈለገውን የፈረንሳይ ሪፓብሊክ ሕዝብ መንግሥት ሥርዓት መሠረተ ሲል ታሪኩን ከዘረዘረ በኂላ ሁኔታው ከጊዜው የኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር የሚመሳሰል መሆኑን በመግለጽ በኢትዮጵያም እንደዚያ ያለ የሕዝብ የተቃርኖ እንቅስቃሴ ሳይነሳና በአገር ላይ ጉዳት በሕዝብ ላይ እልቂት ሳይደርስ የመንግሥቱን አስተዳደር መለወጥ ትልቅና እርቆ አስተዋይነት እንደሆነ የሚገልጽ ማስታወሻ ለንጉሠ ነገሥቱ አቀረበ።

ንጉሠ ነገሥቱ ይኸን ዓይተው በቀይና ሰማያዊ ኮፒ እርሳስ «ሕዝባችን ከኛ ጋር ነው። ለዚህ አልደረሰም» ብለው ጽፈው ማስታወሻውን መለሱለት። ይህን ማስታወሻ ወርቅነህ ለመሥሪያ ቤቱ ባልደረቦች፣ ለሻምበል ፀጋዬ ደፈርሻ (በኋላ ኮሎኔል) እና ለሻምበል ከበደ ተሰማ አስተያየታቸውን እንዲሰጡት ሰጥቷቸው ነበር። ማስታወሻውን ካነበቡት ኮሎኔል ፀጋዬ ደፈርሻ «ሕዝቡ ንጉሠ ነገሥቱን በጣም ስለሚወድና ስለሚያከብር እንዲህ ያለ ችግር ይደርሳል ብዬ አልገምትም» ሲል የሻምበል ከበደ ተሰማ ደግሞ «ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ እንደሚደርስ ጥርጥር የለውም። እስከአሁን መቆየቱም የሚገርም ነው» የሚል አስተያየት ይሰጣል።[11] እንግዲህ በዚህ መሠረት ፍፁማዊውን ዘውዳዊ አገዛዝ ወደ ሕገ መንግሥታዊ የዘውድ አስተዳደር በማሸጋገር ለኢትዮጵያ የወደፊት ዕድገት ፋና ወጊ ይሆናል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበት የነበረው የጃፓኖች ቡድን ጥናት በንጉሡ የሥልጣን ንፍገት መልስ በማጣቱ አገሪቱና ሕዝቡ በችግር እንደተዋጡ ቀሩ።

የጥናቱ ሰነድም ከቤተ መንግሥት ወደ ብሔራዊ ቤተ መዛግብትና መጻሕፍት ማደራጃ ተልኮ JAG በሚል አርዕስት በምሥጢር ሰነድ ማከማቻ ክፍል ይገኛል። ልዩ ካቢኔ መቋቋሚያ ተብሎ የተጠናው ጥናት ግን ዘግይቶም ቢሆን ተቀባይነት አግኝቶ ተቋቋመና ሥራውን ለማስጀመር የሚከተሉት ሰዎች ተመርጠው ተሾሙ።[12]

[10] እንደማሽፍ፣ አናንቆና አጣጥሎ መናገር ነገር ነው።
[11] በ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. የገለጸልኝ የሥራ ባልደረባዬና ወዳጄ ኮሎኔል ፀጋዬ ደፈርሻ ነው። ኮሎኔል ፀጋዬ አሁን ወደ ብረዘይት መንገድ ከስብስቴ ነጋሢ ት/ቤት ወረድ ብሎ በጡረታ ይኖራል። የሻምበል ከበደ ተሰማ ግን ሉዳን ውስጥ በስልሳዎቹ ገደማ ተገድሏል።
[12] አዲስ ዘመን ታኅሣሥ ፲፪ ቀን ፲፱፻፶፱ ዓ.ም.፤

## ሹ መ ት

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ ታኅሣሥ ፲፪ ቀን ፲፱፻፶፪ ዓ ም ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ሹመት ሰጥተዋል ።

፩/ ክቡር አቶ አማኑኤል አብርሃም በሚኒስትር ማዕርግ በግርማዊነታቸው ካቢኔ የፖሊቲካ ክፍል ዋና ሹም ፤

፪/ ክቡር አቶ ጋሻው ዘለቀ በውጭ አገር የግርማዊነታቸው ባለሙሉ ሥልጣን ን ባሳደርና ልዩ መልእክተኛ ፤

፫/ ክቡር ልጅ ሚካኤል እምሩ በውጭ አገር የግርማዊነታቸው ባለሙሉ ሥል ጣን አምባሳደርና ልዩ መልእክተኛ ፤

፬/ ብርጋዴር ጄኔራል ኢሳይያስ ገብረ ሥላሴ በግርማዊነታቸው ካቢኔ ልዩ የኢታ ማዦር ሹም ፤

፭/ ክቡር አቶ ከበደ ሚካኤል በም ክትል ሚኒስትር ማዕርግ በግርማዊነታ ቸው ካቢኔ የንጉሣዊ ዜና ማደራጃና የሕ ዝብ ቤተ መጻሕፍት ክፍል ዋና ሹም፤

፮/ ክቡር አቶ ግርማ ተክለ ሐዋርያት በውጭ አገር የግርማዊነታቸው ባለ ሙ ሥልጣን አምባሳደርና ልዩ መል ክተኛ ሁነው ተዛውረው ተሹመዋል ።

፯/ ክቡር አቶ ብርሃኑ ድንቄ የጉባ ኤና የቴሌፎን ፣ የቴሌግራፍ ሚኒስቴር ም/ሚኒስትር ።

[illegible]

ከንቲባ ።

፱/ አቶ ታከለ [illegible] መኩሪያ በሚ ኒስትር ደረጃ [illegible] ቆንስል ጄኔራል ።

፲/ ሻለቃ ወርቅነህ ገበየሁ ሊፍተና ኮሎኔል ተብለው በግርማዊነታቸው ካቢኔ ምክትል ልዩ የኢታ ማዦር ሹም ።

፲፩/ ሻለቃ አሰፋ በቀለ በወሎ ጠቅላይ ግዛት የወረይሉ አውራጃ ገዥ ።

፲፪/ ሊፍተና ኮሎኔል ስለሺ ድፋባ ቸው በሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት የደራሳ አውራጃ ገዥ ፤

፲፫/ ልጅ ሙሉጌታ ገብሬ እግዚአ ብሔር ኮማንደር ተብለው በወሎ ጠቅላይ ግዛት የአምባሰል አውራጃ ገዥ ፤

፲፬/ ሻለቃ ሰሎሞን ከድር ሊፍተና ኮሎኔል ተብለው በግርማዊነታቸው ካቢኔ ምክትል ልዩ የኢታ ማዦር ሹም፤

፲፭/አቶ ዮሐንስ ኪዳኔ ማርያም በግ ርማዊነታቸው ካቢኔ ዋና ዲሬክተር ፤

፲፮/አቶ ወርቁ ሀብተ ወልድ በግርማ ዊነታቸው ካቢኔ ዋና ዲሬክተር ፤

፲፯/አቶ ሙሉ እሸት ድልነሣሁ በግር ማዊነታቸው ካቢኔ ዋና ዲሬክተር ፤

፲፰/አቶ አየለ ሞልቶታል በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ፤

፲፱/ ቀኛዝማች ዘውዴ ታደሰ የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት ዋና ዲሬክተር ፤

፳/አቶ አሰፋ ተምትም በሞስኮው የግርማዊነታቸው ኤምባሲ ፩ኛ ጸሐፊ ፤

፳፩/አቶ አያሌው ዘለቀ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ፤

፳፪/አቶ [illegible] በግር ማዊነታቸው ካቢኔ ዋና ዲሬክተር ፤

፳፫/አቶ በፈቃዱ ታደሰ በግርማዊነታ ቸው ካቢኔ ዋና ዲሬክተር ፤

፳፬/ አቶ ነቢዩ ልዑል ከፍሌ በግርማዊነ ታቸው ካቢኔ ረዳት ዋና ዲሬክተር ፤

ከተሿሚዎች መካከልም የሻለቃ ወርቅነህ ገበየሁ በሌፍተናንት ኮሎኔል ማዕረግ የካቢኔው ምክትል ልዩ ኤታማዦር ሹም ሆነ። በርግጥም ጅምሩ ለተወሰኑ ጊዜያት መልካም የሥራ ቅልጥፍና ታይቶበት ይበል ይበል ተብሎ ነበር። ውሎ አድሮ ግን ያው የጓዳ በር ሥራ የቀረባቸው ባለሥልጣኖች ተጠናክረው በመቆም፤ ልዩ ካቢኔው የተቋቋመው ሚኒስትሮቹ የማይታመኑ ሁነው በሚኒስትሮቹ ላይ ሚኒስትር እንደተሾመ፤ ከዚያም አልፎ ተሿሚዎቹ ለየተወከሉበት መሥሪያ ቤት እንደመረጃ ሠራተኛ እየተቆጠሩ ከየመጡበት መሥሪያ ቤት የሚፈልጉትን ትብብር እያጡ እንዲሔዱ ተደረገ። በዚህ ምክንያት የተለመደው የሥራ መጓተትና መነታረክ ቀጠለ። ወርቅነህ ይህ ጥረቱ ሳይሳካ ቢቀርም፤ ጊዜና ሁኔታን ጠብቆ የሚከተለውን የመሬት ይዞታ ማሻሻያ ማስታወሻ ደግሞ ለንጉሡ ነገሥቱ አቀረበ።

## የመሬት ይዞታ ማሻሻያ ደንብ

ቀደም ብዬ በምዕራፍ ሁለት የኢትዮጵያ የመሬት ሥሪትና ግብር ስለነበረበት ችግር ጠቅሼአለሁ:: ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ይህንን የመሬት ሥሪት (በኋላ የመሬት ይዞታ) እና ግብር ችግር ለመፍታትና የመሬት ይዞታን ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ወደ ሕዝብ ለመመለስ አንድ ዘዴ አሰበ:: ይኸውም ልማት ላይ ያልዋለ መሬትን ማስለቀቂያ (የውዴታ ግዴታ) አዲስ የግብር ደንብ ማውጣት ነበር:: ይህን ዘዴ በሥራ ላይ ለማዋል አተገባበሩን በባለሙያዎች አስጠንቶ፣ የዘገባውን ማስታወሻ ለግርማዊ ጃንሆይ ውሳኔ አቀረበ:: ዓላማውም በጥናት ሰነዱ ላይ የሠፈረው የጋሻ መሬት የግብር አመዳደብ ከጃንሆይ መልካም ፈቃድ ተገኝቶ በዐዋጅ ወጥቶ በሥራ እንዲውል ሲሆን፣ የዕቅዱ የጥናት ይዘትም በወቅቱ የነበረውንና ወደፊት እንዲሆን የታሰበውን የመሬት ግብር ባጭርና በጥቅል በንጽጽር የሚያቀርብ ነበር:: በዚህ መሠረት:-

፩. በሰሜን ምዕራብ የአገሪቱ ክፍል በነበረው የመሬት ሥሪት ተወላጁ ሁሉ የራሱ የሆነ የርስት መሬት ያለው ሆኖ፣ መሬት የሚያንሰው እንጅ ከሚጠቀምበት በላይ መሬት የያዘና በይዞታው ግብር የማይከፍል አልነበረም:: በዚህ የመሬት ስሪት ደንብ ይተዳደሩ የነበሩት ገበሬዎች በወቅቱ ይከፍሉ የነበረው የርሻ ግብር፣ (አሥራትን፣ የትምህርት ታክስን፣ የጤና ታክስን ...ወዘተ.) ያካተተ ነበር:: የግብሩ አመዳደብም የማምረቻ መሣሪያውን መሠረት ያደረገ ሲሆን እርሱም፣ በዶማ፣ በቀንጃ በሬ፣ በጥንድ፣ በጥንድ ከቀንጃ፣ በሁለት ጥንድ፣ በሦስት ጥንድና አልፎ አልፎም በአራት ጥንድ የሚያርስ ገበሬ ግብር ሊሆን ይችላል:: ግብሩ ከላይ የታየውን የማምረቻ መሣሪያውን ተራ ተከትሎ ፰ ብር፣ ፲፪ ብር፣ ፳፬ ብር፣ ፴፮ ብር፣ ፵፰ ብር፣ ፷ ብር፣ ፸፪ ብር እና ባለ አራቱ ጥንድ ፻፬ ብር ጣራ ይከፍል ነበር::

፪. በመኻል፣ በደቡብ፣ በምሥራቅ እና በምዕራብ በአገሪቱ ክፍሎች ደግሞ በወቅቱ የነበረውና ወደፊት እንዲሆን ታስቦ የነበረው የጋሻ መሬት ግብር የሚከተለው ነበር:: በሙሉ ለታረሰ ወይም ለለማ አንድ ጋሻ መሬት ግብር ፲ ብር፣ በሙሉ ላልለማ (በከፊል ለታረሰ ወይም ለለማ) አንድ ጋሻ መሬት ግብር ፭ ብር እና ልማት ያልነካው ለግጦሽና ለእንጨት ... ወዘተ. የዋለ አንድ ጋሻ ጠፍ መሬት ግብር ፩ ብር ነበር::

ከላይ በተጠቀሰው የመሬት ግብር አመዳደብ በመቶዎችና በሺህ ጋሻዎች የሚቆጠር መሬት ያላቸው ባለይዞታዎች አነስተኛ የሆነውን ክፍል በጢሰኞች (በተጠማኞች) ሲያስሙ፣ አብዛኛው መሬት እነርሱ ያላለሙት ወይም ለሚያለማ ያልሰጡት ጦም አዳሪ መሬት ነበር:: ችግሩ ይኸ ብቻ አልነበረም:: መልማት የሚችለው መሬት ስላልተሠራበት ጠፍ ተብሎ ይመደባል:: እንዲያ ተብሎ ቢመደብም ባለይዞታዎቹ የጠፍ ግብር እንኳ ለመክፈል ፈቃደኞች አልነበሩም:: ይህን ያልለማ መሬት ራሳቸው

በማልማት ወይም ለሚያለማ በፈለጉት ውል በመስጠት ብዙ የሥራ ዕድል ከፍተው፣ እነርሱ ተጠቅመው የመንግሥት ግብር በመክፈልም ለአገሪቱ የፖለቲካ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ኑሮ መሻሻል ከፍ ያለ አስተዋጽዖ ማድረግ ሲችሉ ሥርዓቱ ስለማያስገድዳቸው እገሌ ይህን ያህል ጋሻ መሬት አለው እየተባለ በሚነሳው ስማቸው ብቻ ተኩራርተው ይኖሩ ነበር። ይህ የወቅቱን ሁኔታ ተከትሎ ያልተሻሻለ ሥርዓት አገሪቱን ከድህነትና ከኋላ ቀርነት አዙሪት ከቷት ኖሯል። ሥርዓቱ መሬት በተገቢው መንገድ ለኢኮኖሚ ዕድገት እንዳይውል በመገደቡ በሚሊዮን የሚቆጠሩ በእርሻ መተዳደር ይችሉ የነበሩ ሥራ አጥ ዜጎችን (ተፈጥሮ በለገሰችው መሬት እንኳ ድርሻቸውን ያላገኙ) ሠርቶ የማደር መብት የነፈገ ነበር።

ስለዚህ የጥናቱ ፍሬ ሐሳብ ይህን ሁኔታ ለመለወጥ እያንዳንዱ ባለጋሻ መሬት ይዞታውን በትክክል አስመዝግቦ እና በተወሰነው የግብር መደብ መሠረት ለእያንዳንዱ ጋሻ መሬት መክፈል የሚኖርበትን ግብር መክፈሉን ማረጋገጥ ነበር። ይህንንም ግብር ለመክፈል ፈቃደኛ ያልሆነን የብዙ ጋሻ መሬት ባለቤት ደግሞ ግብር ያልከፈለበትን መሬት በግብረ ጠልነት መሬቱን ለመንግሥት የመልቀቅ ግዴታ እንዳለበት ማሣወቅ ነበር። በዚህ አኳኋን የሚለቀቀውን መሬት መንግሥት ይዋል ይደር ሳይል መተዳደሪያ ለሌለው በግብርና መተዳደር ለሚፈልግ ለመስጠትና መሬት ተቀብሎ ሠፊ እርሻ ለማልማት ለሚፈልግ ደግሞ ገደብ አውጥቶ ለማከፋፈት የሚያስችል ሕግ አውጥቶ ተግባራዊ ማድረግ ነው።

በአጠቃላይ የዚህ ደንብ ዐላማ ሠፊ የሥራ ዕድል መፍጠር፣ በየጊዜው የሚያጋጥመውን የእህል እጥረትና ድህነትን ማቃለል፣ ለመንግሥት ተጨማሪ ገቢ ማስገኘትና ለመሬት ይዞታ ገደብ ማውጣት ናቸው። ይህም ለመንግሥት ከፍ ያለ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ጠቀሜታ እንደሚያስገኝ ታምኗል። ይህ ጥናት ተግባራዊ ሲሆንም፦

ሀ) ሙሉ በሙሉ ለታረሰና ለም ተብሎ ለተመደበ ለመጀመሪያው አንድ ጋሻ መሬት በወቅቱ ብር ፹ (ሰማንያ የነበረው)፣ ለማበረታቻ (ተሻሽሎ) በዓመት ፴ (ሰላሳ) ብር እንዲሆን፤ ለሁለተኛው ጋሻ መሬት ብር ፹ (ሰማንያ)፤ ለሦስተኛው ጋሻ መሬት ብር ፻ (መቶ) ብር ሆኖ (በእያንዳንዱ ተጨማሪ ጋሻ መሬት) ግብሩ በብር ፩ ፻ሃያ) ጭማሪ እያደገ እንዲሔድ ተደረገ። የጋሻ መሬቱ ቁጥር እየበዛ በሔደ መጠን ግብሩም እያደገ ይመጣና የ፲ኛው አንድ ጋሻ መሬት ግብር ፪፻፵ (ሁለት መቶ አርባ) ብር ይደርሣል። በዚህስሌት ፲ ጋሻ ለም መሬት ያለው የመሬት ባለቤት ቀድሞ ይጠየቅ የነበረው ብር ፰፻ (ስምንት መቶ) በአዲሱ የግብር መደብ ወደ ብር ፩ሺህ ፭፻ (አንድ ሺህ አምስት መቶ) ያድጋል።

ለ) ከፊል ለም ለሆነውና ወይም ለም ከጠፍ ተብሎ ለተመደበ ለእያንዳንዱ ጋሻ መሬት ተወስኖ የነበረው ግብር፤ ብር ፴ (ስልሣ) ባለማልማቱ ብር ፩ ፻ሃያ፣ መቀጫ ተጨምሮበት በመጀመሪያው ጋሻ መሬት ግብር ብር ፹ (ሰማንያ)፤

ለሁለተኛው ጋሻ መሬት ብር ፳ ተጨምሮበት ግብሩ ብር ፻ (መቶ)፤ ለሦስተኛው ጋሻ መሬት የሚከፈለው ብር ፩፻፳ (መቶ ሃያ) ይሆንና ግብሩ በጋሻ ብር ፳ (ሃያ) እየጨመረ ሒዶ የ፲ኛው ጋሻ መሬት ግብር ብር ፪፻፴ (ሁለት መቶ ስልሣ) እንዲከፈልበት ይደረጋል። ስለዚህ ፲ ጋሻ ለም ከጠፍ መሬት የያዘ ባለይዞታ በፊት ይጠየቅ በነበረው ብር ፮፻ (ስድስት መቶ) ፈንታ ብር ፩ ሺህ ፯፻ (አንድ ሺህ ሰባት መቶ) እንዲከፍል ይደረጋል።

ሐ) ለግጦሽ፣ ለእንጨት እና አሸዋ ወይም ድንጋይ የሚውል ጠፍ ተብሎ ለተመደበ መሬት ለመጀመሪያው ለአንድ ጋሻ መሬት ተመድቦ የነበረው ግብር ብር ፵ (አርባ) ላይ ቅጣት ብር ፳ (ሃያ) ተጨምሮበት (ልማት ስላልተሞከረበት) ወደ ልማት እንዲገባ ለመገፋፋት ያንዱ ጋሻ የጠፍ መሬት ግብር ወደ ብር ፷ (ስልሣ) ከፍ እንዲል፤ ለሁለተኛ ጋሻ ብር ፹ (ሰማንያ)፤ ለሦስተኛው ጋሻ መሬት ብር ፻ (መቶ) እንዲሆን ተደርጎ ለ፲ኛው ጋሻ ብር ፩ ሺህ ፭፻ ፲አንድ ሺህ አምስት መቶ) ይከፍልበትና በዚህ ደረጃ የተመደበ አሥር ጋሻ መሬት ይዞታ ያለው ሰው የሚከፍለው በድምሩ በቀድሞው ግብር ሊከፍለው ይገባ በነበረው ብር ፬፻ (አራት መቶ) ፈንታ ብር ፩ ሺህ፭፻ (አንድ ሺህ አምስት መቶ) ይደርሳል ማለት ነው።

ይህ አዲስ የመሬት ግብር ምደባ አሠራር ግብሩን ላልከፈሉ ወይም ለመክፈል ላልፈለጉ ባለይዞታዎች፣ መሬቱን በግብረ ጠል መልቀቅ ግዴታ እንዲሆንባቸው ያስገድዳል። የሚለቀቀው መሬት ደግሞ መተዳደሪያ ለሌላቸውና በግብርና መተዳደር ለሚፈልጉ እንዲሁም ለልማት መሬት ለሚፈልጉ ባለሀብቶች ሊሰጥ የሚችል መሬት ከማስገኘቱም በላይ፤ በአገሪቱ ኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ሕይወት በኩል ከፍ ያለ ጥቅምና ክብርም የሚያስገኝና ድህነትን ለመቀነስ የሚረዳ ሥልት ነው ተብሎ የተቀየሰ ነበር።

ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ለንጉሡ ባቀረበው በዚህ አዲስ የመሬት ግብር ምደባ የጥናት ማስታወሻ፣ ምሳሌ አድርጐ ያቀረበው «ጋንግሪን» በተባለው በሽታ ስለተጠቃ ሰው ነው። ዝርዝሩም በሽታው ሰውየውን ከእግሩ ጣት ላይ ቢይዘው የሰውዬውን ሕይወት ለማትረፍ ጊዜ ሳይሰጡ የታመመውን ጣት መቁረጥ ነው። ይህ ቶሎ ባይደረግ ግን፤ በሽታው (ጋንግሪኑ) ወደ እግሩ ቀጥሎም ወደ ጭኑ እየዘለቀ አሠቃይቶ የታማሚውን ሕይወት ያጠፋል የሚል ነበር። አሁን ያለው ያገሪቱ የመሬት ይዞታ ችግርም ቶሎ ካልተስተካከለ እንደዚህ ሰውዬ የእግር ጣት (ጋንግሪን) ችግሩ እየዘለፈና እየገፋ መጥቶ መንግሥትን የሚያናውጥ ሕዝብንም የሚያፋጅ ቀውስ እንደሚያመጣ አለማጠራጠሩን፤ ለ‹‹ጋንግሪኑ›› መፍትሄው የበሽተኛውን ጣት ቶሎ መቁረጥ እንደሆነ ሁሉ፤ የመሬት ይዞታውን ጋንግሪንም ከመቁረጥ የተሻለ ዘዴ አለመኖሩን፤ ይህ

ባይሆንና አሁን ያለው የመሬት ይዞታ ባለው ይቀጥል ቢባል ግን አገሪቱን ከከባድ ችግር ላይ እንደሚጥላት የማያጠራጥር እንደሆነ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ አስረድቷል::[13]

ሆኖም ንጉሡ ነገሥቱ የራሣቸውን ክብርና ሥልጣን ከአገርና ከወገን ጥቅም በላይ አድርገው የሚያዩ በመሆናቸው፤ ይህን ኢትዮጵያ በኋላ ከደረሰባት ችግር እንዳትወድቅ አርቆ በማየት የቀረበ ሐሣብ መልስ ሣይሰጡበት አዳፍነውት ቆዩ:: ከ፲፱፻፶፫ ዓ.ም. መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በኋላ ግን ንጉሡ ሐሳቡ ከንከናቸው የመሬት ይዞታን የሚመለከት በሚኒስቴር ደረጃ ጽሕፈት ቤት አቋቋሙ::[14] ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ስለ መሬት ይዞታ ባቀረበው ማስታወሻው ውጤት ባያገኝበትም

13 ወርቅነህ በከፍተኛ ስሜት ለግርማዊ ጃንሆይ ሲገልጽ እዚያው የነበሩት የጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት አፈንጉሥ ተሾመ ኃይለ ማርያም በገለጻው ተደንቀውና ተገርመው ለወዳጃቸው ለአቶ ተካልኝ ገዳሙ፣ «ወርቅነህ ብርቱ፣ አርቆ የሚያይና ጥልቅ ግንዛቤ ያለው ሰው ነው:: ሳገሩና ለወገኑ ያለው ፍቅርና ስሜት በጣም የሚደንቅ ነው:: ቆራጥና ደፋርም እንደሆነ ጃንሆይ ፊት ሲናገር ሰማሁ በጣም የሚደንቅ ሰው ነው" በማለት እንደገለጹለት የነገረኝ አቶ ተካልኝ ገዳሙ ነው:: አቶ ተካልኝ የቅርብ ዘመዱና ወዳጁም ሲሆን፤ የፕላን ሚኒስትር፣ የመገናኛና ትራንስፖርት ሚኒስትር፣ የአፍሪካ ልማት ባንክ ምክትል ፕሬዚደንት፣ የአቢሲኒያ ባንክ መሥራችና ፕሬዝደንት እና ከ፲፱፻፺፯ እስከ ታኅሣሥ ፪ ሺህ ዓ.ም. የጐንደር ልማት ማኅበር ፕሬዝዳንት ነበር:: አሁን በአሜሪካ ፊላደልፊያ ይኖራል::

14 የሚኒስቴር ጽ/ቤቱ ሥራ በጣም ከባድና አሳሳቢ ጥንቃቄና ታማኝነትን የሚጠይቅ ስለነበር፤ ሚኒስትር ሆነው የተሾሙት አቶ በለጠ ገብረ ፃድቅ ነበሩ:: አቶ በለጠ ገብረ ፃድቅ አቋዋማቸው ሲገመገም እውነትን ለመናገር የሚደፍሩና ከእውነት ፈቀቅ የማይሉ ነበሩ:: ከትርፍ መሬት ባለቤቶች ጋር ወገናዊነት አለ እንዳይባልም ትርፍ መሬት ቀርቶ የመኖሪያ ቤት እንኳ ያልሠሩ፤ ከወር ደመወዛቸው ሌላ ምንም ገቢ ያልነበራቸው ሆነው በመገኘታቸው ነው ሥራው የተሰጣቸው:: አቶ በለጠ ሥራውን እንደተቀበሉ ብዙ ባለ ሙያዎችን ይዘው ሠፊ የችግር መፍቻ ጥናት አስጠንተው ለንጉሠ ነገሥቱ ይሁንታ አቀረቡ:: ስለዚሁ ተግባራቸው ሲነግሩኝ "ውይ! ውይ!" እያሉ እየተንገፈገፉ (ትዝታው እየመጣባቸው) ነበር:: በጥናቱ ላይ ብዙ ክርክር ተካሂዶ ካሳመኑ በኋላ ደግሞ ‹‹መወሰን ላይ ችግር መጣ›› ይላሉ አቶ በለጠ:: በዚህ የተነሳ ብዙ ሰው ደከሞ፣ ብዙ ገንዘብ ፈሶ ውጤት ሳያስገኙ ተነሱ:: ቀጥሎም የቀረበውን መስፈርት ሁሉ ያሟሉ ሰመጥር ኤኮኖሚስት የሆኑት አቶ በላይ ዐባይ ተተክተው እንደ አቶ በለጠ ብዙ ጥረው የንጉሡን ቁርጠኛ ውሳኔ ሲጠብቁ ችግሩ ሳይፈታ ወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት መጣ:: ለወታደራዊ መንግሥት መምጣት ምክንያት ከሆኑት ችግሮች ዋናና ቀዳሚ የነበረው ይኸው ኢፍትሐዊ የሆነው የመሬት ይዞታ "ሥሪት" ነበር:: ወታደራዊው መንግሥት ይህን ችግር ለመፍታት በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም. የገጠር መሬትንና የከተማ ትርፍ ቤቶችና ቦታ የመንግሥት ሆነዋል ሲል መግለጫ አወጣ:: በወጣው ደንብ ወይም ድንጋጌ የተወሰነው የገበሬው ክፍል ቀጥተኛ የመሬቱ ባለቤት ባይሆንም "ጢሰኛ" ወይም "ተጠማኝ" ከመሆን ነፃ ሆነ የምርቱ ሙሉ ባለቤትም ተደረገ:: በመሬት ይዞታ በኩል ይታይ የነበረው ኢፍትሓዊነት በመወገዱ ትልቁ ብሔራዊ ችግር ከሞላ ጎደል መፍትሄ አገኘ:: ደርግ ይህን አዲስ የመሬት ይዞታና አስተዳደር ደንብ ተግባራዊ እንዲያደርጉና ለሚነሱ ችግሮችም መፍትሔ እንዲሰጡ አቶ ዘገየ አስፋው የተባሉ ምሑር የመሬት ይዞታና አስተዳደር ሚኒስትር እንዲሆኑ ሾመ:: ይሁን እንጂ በውሳኔው መሬታቸውን የተነጠቁ የኅብረተሰቡ ክፍሎች አመጽ በማስነሳታቸው በነሱ በጠ.ብኞችና በለውጡ ደጋፊዎች መካከል የርስ በርስ ውጊያና ፍጅት ተካሄደ:: የብዙ ሰው ደም ፈሰሰ:: የብዙ ሰው ሕይወት ጠፋ:: ብዙዎቹም ተሰደዱ፤ አገር ጥሎ መሔድና መሰደድ የኢትዮፊያ ሕዝብ መታወቂያ እስኪሆን ድረስ:: ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ስለመሬቱ ሥርዓት ከጋንግሪን ጋር አመሳስሎ የሰጠው የቅድመ ሁኔታ ማስጠንቀቂያ ከዚህ ለመዳን ነበር:: "በኢሕአዴግም" የመሬት ይዞታ ችግር ሙሉ በሙሉና አስተማማኝ በሆነ መንገድ መፍትሔ አላገኘም:: መሬት የመንግሥት ብቻ በመሆኑ አሁንም በገጠር ያለው ሕዝብ በሚያርሰው መሬት ላይ ሙሉ የባለቤትነት መብት የለውም:: በከተማም አንድም የከተማ ነዋሪ የመኖሪያ ቤት የሠራበት መሬት የራሱ የግል ንብረቱ ለመሆኑ መተማመኛ የለውም:: በዓለም ርስት የለሽ ሕዝብ ያለባት ብቸኛ አገር (ከኮሚኒስት አገሮች በቀር) ኢትዮጵያ ሳትሆን አትቀርም::

ሳይሰለች ፍትሐዊነትን በተዘዋዋሪ መንገድ ወደ አገር ለማስገባት ሌላ ዘዴ ወጥኖ ለመተግበር ከፍተኛ ጥረት አደርጓል።

## ለገዥዎችና እንደራሴዎች የተዘጋጀ ሥልጠና

ቀደም ብለን እንዳየነው በጃፓኖቹ የተካሔደው የመንግሥት የሥርዓት ማሻሻያ ጥናት በንጉሡ ባለመደገፉ ከሽፏል። አጥኚዎችም አዝነው ወደ አገራቸው እንደ ተመለሱ ዓይተናል። ሆኖም ወርቅነህ ተስፋ ባለመቁረጥ ሌላ መለስ ያለ የሥርዓት ለውጥ ዕቅድ ይዞ ተነሳ። በጠቅላይ ግዛት (ክፍለ አገር) ለገዥነት የሚመደቡት ባለሥልጣኖች ችሎታና አቋም እንዴት ያለ እንደነበር «አስተዳደር» በሚለው አርዕስት በመጠኑ ታይቷል። የገዥዎች ዕድሜ፣ ዕውቀት፣ የአስተዳደር ልምድና አመራር ከፍ ያለ ልዩነት ነበረው። ስለዚህ የሁሉም የአሠራር ሒደት ቢቻል አንድ ዓይነት ባይቻል ተቀራራቢ እንዲሆን፤ ኃላፊነትና ተጠያቂነትን ያካተተ በየጊዜው የሚሻሻል የሥራ መመሪያ ከመንግሥት (ከአገር ግዛት ሚኒስቴር) ስለማይሰጥ ቢሰጥ ደግሞ እንደ ሁኔታው በየጊዜው የማይሻሻል በመሆኑ አመራሩ በገዥዎች የግል አመለካከት ላይ የተጣለ ነበር። የያንዳንዱ ጠቅላይ ግዛት ገዥ ወይም እንደራሴ የልማት ነገር ጨርሶ ሳይነሳ በደል ባለማድረሱ ተቀባይነት ሲያገኝ፤ በጭቆና የሚተዳደረው ሕዝብ ደግሞ ሲማረር ይሰማ ነበር። በዚህ የተነሳ ለኢትዮጵያ ኋላቀርነት ከሚጠቀሱት ምክንያቶች አንዱ የጠቅላይ ግዛት ባለሥልጣኖች ብቃት አለመኖር ያስከተለው ችግር መሆኑ አከራካሪ አልነበረም። ስለዚህ ወርቅነህ ይህን ችግር ቢቻል ጨርሶ ለማጥፋት፣ ባይቻል ለማቃለል፤ የጠቅላይ ግዛት አስተዳደራዊ የሥራ አመራርን ለማሻሻልና ዕድገትን ለማምጣት ለገዥዎችና ለእንደራሴዎች ዴሞክራሲያዊ የአመራር ሥልት የሚያስጨብጥ ሥልጠና መስጠት ብርቱ አቋዋም መሆን አለበት ብሎ ተነሣ። በመሆኑም ችሎታቸውን ለማሻሻል የሚችሉትን ማሠልጠን፣ ማሻሻል የማይችሉትን ደግሞ አንስቶ ችሎታ ባላቸው ወጣት ምሑራን ለመተካት እንዲቻል መንገድ የሚያሲይዝ የዕቅድ ጥናት ለንጉሡ ውሳኔ አቀረበ።

ዕቅዱ ሁሉም ጠቅላይ ገዥዎችና እንደራሴዎች አንድ ወጥ የሆነ የአስተዳደር (የአመራር) ሥልት እንዲከተሉ ትንሽ ወደ ፊት እንዲያዩና፣ ስለልማትም እንዲያስቡ ሊያደርግ የሚያስችል ከሕዝብ ጋር የሚያቀራርብ፣ "ሕዝብ የገዢዎች መገልገያ ነው"፣ የሚለው አስተሳሰብ ተለውጦ "አስተዳዳሪ አገልጋይ ሕዝብ ተገልጋይ ነው" የሚለውን መሠረታዊ የመልካም አስተዳደር (የዲሞክራሲ) መርህ እንዲጨብጡ የሚያደርግ የአጭር ጊዜ ሥልጠና መስጠትን የያዘ ነበር።

ሥልጠናውም በመጀመሪያ ለጠቅላይ ገዥዎችና ለእንደራሴዎች፣ ቀጥሎ ለአውራጃ ገዥዎች፣ በመጨረሻ ለወረዳ ገዥዎች እንዲሰጥና፣ በሕዝብ ላይ የሚደርሰው የአስተዳደር በደልና የፍትሕ መጓደል የሚቀንስበትን መንገድ እንዲፈልጉ ኅሊናቸውን ሊያስገድድ ይችላል ከሚል እምነት የመነጨ ነበር። ይህ ጉዳይ ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበትን ሁኔታ ለማስጠናት ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ከእሥራኤል መንግሥት

ባለሥልጣኖች ጋር ተነጋግሮ አንድ አጥኚ ቡድን አስመጣ። ቡድኑ ወደ ኢትዮጵያ ከመጣ በኋላ በጉዳዩ ላይ ሥልጠና የሚሰጥበትን መንገድ ለመቀየስ በቅድሚያ በወቅቱ በየጠቅላይ ግዛቱ ስላለው የአስተዳደር ሁኔታ አንድ ግንዛቤ መያዝ አስፈላጊ ሆኖ አገኘው። በዚህ መሠረት፣ የሁሉንም ጠቅላይ ግዛቶች አስተዳደር ሁኔታ በዝርዝር ለማየት ቢፈልግ ጊዜ የሚወስድ ስለሆነ፤ አጥኚ ቡድኑ በአገሪቱ ከነበሩት ፲፫ ጠቅላይ ግዛቶች (ኤርትራ በፌዴሬሽን ሥርዓት ትተዳደር ስለነበረች አልተመለከታትም) መካከል ሻል ያለ የአስተዳደር ሥርዓት ተዘርግቶበታል ተብሎ የተገመተውን በደጃዝማች ክፍሌ ዕርገቱ የሚመራውን የሐረርጌን ግዛትና ደካማ ጎኑ ይጐላል ተብሎ ይገመት የነበረውን በደጃዝማች ሰብስቤ ሽብሩ እንደራሴነት ይገዛ የነበረውን የጐጃምን ጠቅላይ ግዛት በመጎብኘትና ሁኔታዎችን በማገናዘብ፤ ለሥልጠና የሚረዳ ፕሮግራም እንዲቀየስ ማድረጉ የተሻለ ነው ተባለና በዚህ መሠረት ጥናቱ ቀጠለ። ለሥልጠና ዝግጅትም ሁለት ቡድኖች ተመደቡ። እነዚህ ቡድኖችና የቡድኖቹ አባላትም በኢትዮጵያ በኩል አቶ ጌታሁን ታፈሰ፣ አቶ ሊሻን ደስታ፣ አቶ ኃይለ ሚካኤል ከበደና አቶ ዘመነ ካሣኘ ሲሆኑ፤ በእሥራኤል በኩል ደግሞ ጄኔራል ዝኤራ፣ ስቶን፣ ኤመሪና ጃክ የተባሉ ነበሩ።

በዚህ ሁኔታ የጉብኝቱ ፕሮግራም ወጥቶና ተፈቅዶ፤ ቡድኖቹ የመጀመሪያ ጉዞአቸውን ወደ ሐረር አድርገው ወደ እንደራሴው ቢሮ ይሔዳሉ[15]። እንደራሴው ቢሮ ገብተው የመተዋወቅ ሥነ ሥርዓት ሲካሔድ የማስተዋወቁ ሥነ ሥርዓት የተከናወነው ለውጭ አገር አማካሪዎቹ የሽፋን ስምና የሽፋን አገር በመስጠት ነበር። ስለዚህ፣ ትውውቁ ለእያንዳንዱ የውጭ አገር አማካሪ አስመሳይ ስምና አስመሳይ አገር በመስጠት አንዱን ከካናዳ አንዱን ከኒውዝላንድ ሌላውን ከአውስትራሊያ … ወዘተ. እየተባለ ነበር። የመተዋወቁ ሥነ ሥርዓት ተከናውኖ ስለመጡበት የጠቅላይ ግዛት አመራር ጉዳይ ጥያቄዎችን የማቅረብና መልስ የመቀበል ሥራ ሲጀመር፤ ጄኔራል ዝኤራ ይጠይቃል፤ ደጃዝማች ክፍሌ ዕርገቱ ይመልሳሉ፤ አቶ ዘመነ ካሣኘ ያስተረጉማል። በዚህ ዓይነት ሦስት ሰዓት ያህል ቆይታ ከተደረገ በኋላ ጥያቄና መልሱ አብቅቶ እንግዶቹ ከቢሮአቸው በመውጣት ላይ እንዳሉ፣ ደጃዝማች ክፍሌ አቶ ዘመነን ወደኋላ እንዲቆይ አዘዙት። ሁሉም ወጥተው ሁለቱ ብቻቸውን እንደቀሩ የሰዎቹን ዜግነት ምን? ምን? ብሎ እንደተናገረ ጠየቁት። መጀመሪያ ያለውን ደገመላቸው። እንደራሴው እሱ ከቢሮአቸው እንደሌለና ብቻቸውን እንዳሉ ዓይነት በቁጣና በብስጭት፣ ራሳቸው ለራሳቸው በመንገር ማጉተምተም ጀመሩ። ፍሬ ነገሩ «እስከ መቼ ነው ጃንሆይ እኛን የማያምኑት?» የሚል ነበር። አቶ ዘመነ የቁጣቸውና የብስጭታቸው ምክንያት በውል ስላልገባው ትንሽ በድንጋጤ ተውጦ ቆይቶ አፍታ እንዳለፈ ደጃዝማች ክፍሌ «ስማህ!» አሉት። «አዲስ አበባ ስትመለስ፣ ለአለቃህ ለወርቅነህ ንገረው! እነዚህ ሰዎች ካናዳዊ

---

[15] *አቶ ዘመነ ካሣኘ (በኋላ አምባሳደር) የቡድኑ አባልና ጸሐፊ ከዚህ ታሪክ ጸሐፊ ጋር የሥራ ባልደረባ የነበረ (አሁን ጐንደር በንግድ ሥራና የጐንደር ልማት ማኅበር ፕሬዝዳንት ሆኖ የሚያገለግል በጽሑፍና በቃል ከገለጸልኝ የተወሰደ ነው።*

ምናምን አይደሉም:: እሥራኤሎች ናቸው:: እኔ መልስ ስሰጥ ሁለቱ ቃል እየተቀበሉ ሲጽፉ አይቻቸዋለሁ:: በዓለም ከቀኝ ወደ ግራ የሚጽፉ ሁለት አገሮች ብቻ ናቸው፤ ዐረቦችና እሥራኤሎች:: ስለዚህ እነዚህ እሥራኤሎች ናቸው:: ያሳዝናል:: ወርቅነህ ከእኛ የበለጠ ለጃንሆይ ታማኝ መሆን ይፈልጋል:: ንገረው! ጥፋቱ የአንተ አይደለም በለው» ብለው ወደ ጠረጴዛቸው ሲሔዱ እጅ ነሥቶ ወጣ:: አቶ ዘመነ ካሣኝ ከቡድኑ ጋር ሲገናኝ ወደኋላ እንዲቆይ የተደረገበትን ምክንያት ለማወቅ በጉጉት ይጠብቁ ለነበሩ ኢትዮጵያውያንና እሥራኤላውያን የቡድኑ አባሎች የሆነውን ሁሉ በዝርዝር ገለጸ::


ጄኔራል ዝሔራ ይህን ሲሰማ፣ በቁጣ ተቀጣጥሎ እሥራኤሎችን ለብቻ ወደ ጉን ወስዶ መጯጯህ ጀመሩ:: ምን እንደተባባሉ ባይታወቅም፤ ከሩቅ ሲታዩ ግን የሌሎችም ቁጣ ከእርሱ ያነሰ አልነበረም:: ከዚህ መጯጯህ በኋላ አጥፊው ወዲያው ወደአገሩ እንዲመለስ ተደርጎ ከቡድኑ ተለየ:: በተያዘው ፕሮግራም መሠረት፣ በጅጅጋ አውራጃ የአንድ ቀን የሥራ ጉብኝት በማድረግ፤ ከአውራጃ ገዥው (በኋላ የአገር ግዛት ሚኒስትር) ከፊታውራሪ ደምሴ ተፈራ ጋር የግማሽ ቀን ቆይታ አድርገው ሥራቸውን አጠናቀው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ:: አዲስ አበባ እንደተመለሱ፣ አቶ ዘመነ ከደጃዝማች ክፍሌ ጋር የነበረውን ቁጣና ብስጭት ለአለቃው ለሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ሪፖርት አደረገ:: ወርቅነህ ለደጃዝማች ክፍሌ ቁጣ ትኩረት አልሰጠውም:: በበኩሉ እርሱም ተቆጥቶ፣ «የምንናገረው እነዚህ ሰዎች የመጡበትን ፓስፖርት ነው:: ስለሌላ ታሪክ ማውራት አንችልም!» በማለት ይህንን ጉዳይ በዚህ ዘግተው ወደ ቀጣይ ሥራ እንዲተላለፉ ፍላጎቱ መሆኑን ገለጸለት::[16] የደጃዝማች ክፍሌ ቁጣ ኋላ ያስከተለውን መዘዝ ማናቸውም አስቀድመው ለመገመት ሳይችሉ ስለቀሩ ጉዳዩ በለሆሰስ ታለፈ::

ቀጣዩ የጉጃም ክፍለ አገር ጉብኝት በተያዘው ፕሮግራም መሠረት ተከናወነ:: በጉብኝቱ ቀን ቡድኑ ደብረማርቆስ አየር ማረፊያ ሲደርስ፤ እንደራሴው ደጃዝማች ሰብስቤ ሽብሩ ሌሎች ሹማምንትን ጨምረው ተቀብለዋቸው ወደ ጽሕፈት ቤታቸው አመሩና፤ የተለመደው ጥያቄና መልስ ተጀምሮ አስተዳደሩ የሚመራበትን እቅድ ለማየት ጠየቀ:: መልሱም ምንም ዓይነት ዕቅድ ወይም ፕሮግራም የለም:: የፕሮግራም መኖር ለምን ይጠቅማል? ፕሮግራም ቢወጣ ተከትሎ ለመሥራት አይቻልም:: ይኸው ዛሬ እናንተ ስለመጣችሁ ጊዜው በናንተ አለቀ:: ነገም እንደዚሁ አንዱ ይመጣል እንደዚሁ ባልታሰበ ጉዳይ ቀኑ ያልፋል:: ስለዚህ ምን ፕሮግራም ማውጣት ያስፈልጋል?" በማለት አስተዳደሩ ፕሮግራም ስላልነበረው ውይይቱ በአጭር ጊዜ ተጠናቀቀ:: በጉብኝቱ በእርግጥም የጉጃም ጠቅላይ ግዛት አስተዳደር በጣም ኋላ ቀር መሆኑ ግልጽ ሆነ:: የቡድኑ አባላትም ከጉጃም ጉብኝት በኋላ በፕሮግራሙ መሠረት ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ::

---

[16] ዝኒ ከማሁ

**የሥልጠና ዕቅዱ ያስከተለው መዘዝ**



አፈ ንጉሥ እሸቴ ገዳ

የገኸዎች ሥልጠና የዝግጅት ሒደት ወደ መጠናቀቁ ደረጃ ሲደርስ፤ በተግባራዊነቱ ላይ ችግር መከሰት ጀመረ:: በቅድሚያ በገኸዎች ሥልጠና የጃንሆይ ፈቃድ የተለወጠ መሆኑ ታወቀ:: ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ክርክሩን ትቶ በአውራጃ ገኸዎች ሥልጠና ላይ ትኩረት አድርጎ ያንን ለማስፈቀድ ጥረት ጀመረ:: ሁኔታው በዚህ እንዳለ፣ በሰባት ሰዓቱ የራዲዮ ፕሮግራም ጊዜ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ በሰጡት የሹመት ዝርዝር አፈንጉሥ እሸቴ ገዳ የፀጥታ መሥሪያ ቤት ምክትል ሚኒስትር ሆነው መሾማቸው ተነገረ:: ሹመቱ፣ በግርማዊ ጃንሆይና በወርቅነህ መኸል በነበረው ቀጥታ ግንኙነት፣ ሌላ ሦስተኛ ኃይል እንዲኖር ተደረገ ማለት ነው:: መልዕክቱ ለወርቅነህ ግልጽ ነበርና፣ በቀጥታ ለጃንሆይ ይላክ የነበረው ሁሉ ለአፈንጉሥ እሸቴ ገዳ እንዲቀርብ ሆኖ ሥራው ቀጠለ::

አፈንጉሥ እሸቴ ብልህ፣ አስተዋይና የነገር ሥልት የሚያውቁ በጣም ፈጣን አንባቢ ሰው ነበሩ:: ያም ሆኖ ግን፣ ከወርቅነህ የሥራ ፍጥነት ጋር ለመጓዝ አልቻሉም:: ለንጉሡ በሚቀርብ ነገር ላይ ጥንቃቄውም፣ ሥጋቱም ሁሉም ተደማምሮ ጃንሆይ የለመዱት የወርቅነህ ገበየሁ ሥራ ተቋረጠ:: በአዲሱ የሹመት ሥርዓት መሠረት የጀመሩት አሠራር ለአንድ ወር ያህል ከዘለቀ በኋላ፤ ከዕለታት አንድ ቀን ጥዋት ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ቀዝቅዞ የነበረው ሞራሉ ታድሶ አዲስ መመሪያ ሰጠ:: ከዚያን ቀን ጀምሮ፣ ከአፈንጉሥ ጋር የነበረው ግንኙነት ተቋርጦ እንደከዚህ ቀደሙ በቀጥታ ከንጉሡ ጋር ቀጠለ:: ሥራዎች በሙሉ እንደድሮው ለንጉሡ ይላካሉ:: የንጉሡ ውሳኔዎችም ወደታች ይወርዳሉ:: ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ይባስ ብሎ፣ አንድ ግቢ የነበረውን የፀጥታ መሥሪያ ቤት የክብር ዘበኛ መሐንዲሶችን አምጥቶ ከሁለት ከፍሎ አሳጠረው:: ሠራተኛውንም እንዲሁ ከሁለት ከፍሎ ደለደለ:: ስለዚህ አፈንጉሥ እሸቴ ገዳ አለቃ ሳይሆኑ አለቃ መስለው እንዲቀመጡ ተደርጎ ቀረ:: በኋላ እንደተወራው፣ የአፈንጉሥ እሸቴ ገዳ ሹመት የደጃዝማች ክፍሌ ቁጣ፣ እነ ራስ



አፈ ንጉሥ እሸቴ ገዳ

እንዳርጋቸውን ጨምሮ፣ የአገረ ገዥዎችና የእንደራሴዎች ዕድማ በወርቅነህ ላይ ያስከተለው ውጤት ሆኖ ተገኘ። ከጃንሆይ የቅርብ ሰዎች የተሰማው ደግሞ እነልዕልት ተናኘ ወርቅ፣ ጃንሆይም ጭምር ከጠቅላይ ገዢዎች ጋር ሥልጣና እንዲገቡ በገዢዎች ተጠይቋል የሚል ወሬ መናፈስ ነበር። ይህም ሊሰጥ የነበረው ሥልጣና እንዲቋረጥ ምክንያት ሆነ[17]። ይህን በዚሁ ላቁምና የሌ/ኮሎኔል ወርቅነህና የእኔን ቅርበት በአጭሩ እገልጻለሁ።

## ስለመፈንቅለ መንግሥቱ ጥንስስ ፍንጭ ማግኘቴ

የሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ በፀጥታ መሥሪያ ቤቱ ኃላፊነት ሥራውን ሲቀጥል በተለያዩ ጊዜያት የማሻሻያ ሐሣቦችን ለንጉሡ እያቀረበ ለማስወሰን ይተጋ እንደ ነበር ከዚህ በፊት ገልጫለሁ። ይህንንኑ ተግባር ከመቀጠሉ ባሻገር በተጓዳኝ የመንግሥት ሥርዓት ለውጥ በማካሔድ ለማሣካት ያሰበ መሆኑን ምልክቶች ለማየት ይቻላል። እኔ ይህንን ሐሣቡን ሆነ ሌሎቹን የተረዳሁት ከእርሱ ጋር የቀረበ የሥራ ግንኙነት ለመፍጠር ዕድል በማግኘቴ ነበር። ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ የነበረበትን ከፍተኛ የሥራ ጫና ለማቃለል፣ ለረጅም ጊዜ በልዩ ረዳትነት ያግዙት የነበሩት አቶ ዘመነ ካሡኝ (በኋላ አምባሳደር) እና አቶ ገላጋይ ዘውዴ (በኋላ በአሜሪካ የኢትዮጵያ የቡና ገበያ ወኪል) ነበሩ። ሁለቱ ረዳቶች ለነገረ መረጃ (ኢንተለጀንስ) ትምህርትና ሥልጠና ከሌሎች ሠልጣኞች ጋር ወደ ዩጎዝላቪያ ሲሔዱ፤ ከሥራ መደቤ ጋር ግንኙነት ባይኖረውም፣ በሁለቱ ልዩ ረዳቶች መሔድ ምክንያት የተፈጠረውን የሥራ ጫና ለማቃለል ቀደም ብሎ አደርግ ከነበረው እገዛ በላይ እንዳደርግ ወደ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ቢሮ ስጠራ፤ እየሔድኩ ዐቅሜ የቻለውን ያህል ከሥራ ሰዓት ውጭ ጠዋት ከአሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል ጀምሮ እስከ ሦስት ሰዓት፣ ከሰዓት በኋላ ደግሞ ከአሥራ አንድ ሰዓት እስከ ምሽቱ ሁለት እና ሦስት ሰዓት ድረስ ከዚያም ባለፈ ከሁለት በአንዱ ቢሮ በመገኘት አግዝ ነበር።

መተጋገዙ መልካም ቢሆንም ወደ ሥራ ጧት አንድ ሰዓት አካባቢ መግባትና ማታ በሦስት ሰዓት መውጣት ከቤተሰቤ ስለለየኝ ቅሬታዬን ለመግለጽ በአንድ ወቅት ለሁለት ቀናት ሳንገናኝ ቆየን። በሦስተኛው ቀን በሥራ መውጫ ሰዓት ስወጣ፤ ዘበኞች ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ 'ሳያገኝኝ እንዳይሔድ ወደኔ ይምጣ' ብለዋል ብለው እንዳልወጣ በሩን ዘጉብኝ። ፊቴን አጥቁሬ እያጉመጎምኩ ቢሮው ስገባ በሁለት እጆቹ ራሱን ይዞ ቀና ብሎ ካዬኝ በኋላ "አታፍርም? አታዝንም? በቀን ስድስት ሰዓት ተሠርቶ ነው ይች አገር አገር የምትሆነው?" ብሎ አዝኖ አንገቱን አቀርቅሮ ቆየና በል ይሔን ሥራ ብሎ ሥራ ሰጠኝ። በዚያን ጊዜ የሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት፣ «ጠዋት» ከሦስት እስከ ስድስት «ከሰዓት» ከዘጠኝ እስከ አሥራ ሁለት ሰዓት ነበር። ከሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ጋር እንዲህ እየሠራን ብዙ መገናኘቱና መቀራረቡ እየጠበቀ በመምጣቱ በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም.

[17] ዝኒ ከማሁ

የሁለተኛው ግማሽ የመጀመሪያ ወራትና በ፲፱፻፶ ዓ.ም. የመጀመሪያዎቹ ሦስት ወራት ውስጥ የበለጠ ቅርበት አዳበርን። ከዚያም አልፎ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ወዳንዳንድ ቦታዎች መሔድ ሲፈልግ በራሱ መኪና መሔዱን ትቶ፣ በተደጋጋሚ በእኔ መኪና እንድንሔድ እየጠየቀኝ፣ እኔም ፈቃደኛ ሆኜ እንሔድ ነበር። በዚህ አጋጣሚም ነበር አንድ ውስጥ ለውስጥ የሚሔድ እንቅስቃሴ ከሁኔታው እንዳለ የሚያደርጉኝን ክስተቶች ማስተዋልና መጠርጠር የጀመርኩት።

ከገጠመኞቼ አንዱን እዚህ ጋር ልጥቀስ። አንድ ቀን ከመኪናዬ ፊት ለፊት ካለው ፓናል ላይ የበኸር ልጄን የጸዳለ ብርሃኑን የሕፃንነት ፎቶግራፍ ለጥፌ ስለነበር ስንሔድ ፓናሉን በጣቶቹ መታ መታ እያደረገ ቆየና «ብርሃኑ፣ በአንዳንድ ነገር ደህና አቋም ያለህ ትመስላለህ። በሌላ በኩል ደግሞ በልጅ ታሥረህ ስለልጅ የምታስብ ትመስላለህ፤ ሁለት የማይገናኙ ሁኔታዎች እንደያዝክ አያለሁ» አለኝና ዝም አለ። እኔም መልስ ሳልሰጥ እንደተኮራረፈ ሰው በዝምታ ተዘጋግተን መንገዳችንን ቀጠልን። የልጄ ፎቶግራፍ ከመኪናዬ ፓናል ላይ መለጠፉ ቅር ያሰኘው ችግርን ለመቀበል በግንባር የማያሰልፍ አስናፊ ነገር አለብህ ማለቱ እንደሆነ ገመትኩ። የበለጠ እየተቀራረብን ስንሔድ ደግሞ አንዳንድ ከፍ ያለ ምሥጢር ያላቸው ሰነዶች ወይም ለንጉሡ የሚቀርቡ ጹሑፎችን ይሰጠኝና አሳጥሬ እንዳቀርብለት ወይም አንብቤ ሐሳቡን በቃል እንድገልጽ ይጠይቀኝ ነበር። እንድመለከታቸው የሚሰጠኝ ደብዳቤዎችና ሰነዶች ይዘት ግን ዕድሜና ልምድ ላላገዘው እንደኔ ላለ ሰው አዕምሮ በጣም የሚያስጨንቁና ለመሸከም ከዐቅሜ በላይ የሆኑ ጉዳዮችን የሚይዙ ስለነበር ለመራቅ እሞክራለሁ። እሱ ግን በነገሩ እንድጠነክርና እንድበስል የሚያደርገው ነው መሰለኝ፣ ብሸሽም በተደጋጋሚ እየጠራ ይሰጠኝ ነበር።

ከሚሰጠኝና አዕምሮዬን በጣም ያስጨነቁኝ ከነበሩት መካከል ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋሪያት መፈንቅለ መንግሥት ለማድረግ ማሤራቸውንና ዕቅድ ማውጣታቸውን፣ የጣሊያን ኤምባሲ በንጉሡ የዘውድ በዓል ዕለት በመናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ሦስት ሕፃናት ጊዜ ጠብቆ የሚፈነዳ ቦምብ ያለበት አበባ በቅርጫት ለንጉሡ እንዲያበረክቱና ፈንድቶ እንዲገላቸው የተጠነሰሰ ሤራና የመሳሰሉ ጉዳዮች የሚዘረዝሩ ይገኙባቸዋል። እነዚህንና ሌላም በርከት ያሉ ሰነዶችን ሳልወድ ሳይ፣ የተባለውም ሳይሆን መቅረቱን እየቆየሁ ስረዳ፣ ቀደም ብሎ እንደሠጋሁት ብዙ የሚያስፈራና የሚያስጨንቅ ነገር እንዳልሆነ፣ ሌሎች ያዩትንና እነሱ የሰሙትንና ያወቁትን እኔ ባውቅ ምን ያስጨንቃል? እነሱ ከኔ የተሻለ ምን አላቸውና ነው? በማለት መደፋፈር ጀመርኩ። በተለይ በሌ/ኮሎኔል ወርቅነህና በእኔ መኸል የነበረው የዕድሜ ልዩነት አምስት ዓመት እንደማይሆን ሳስብ፣ ከአምስት ዓመት ባልበጠ የዕድሜ ልዩነት እሱ ያንን ያህል መሸከም ሲችል፣ እኔ ይህ እንዴት ይከብደኛል? በሚል ራሴን የማጽናናት ነገር እየጠነከረ መጣና ፍርሐቱ ለቆኝ የሚጠይቀኝን በይሉኝታና በፈቃደኝነት እፈፅም ጀመር።

አንድ ቀን ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህና እኔ በኔ መኪና ከልዩ ካቢኔ ጽሕፈት ቤቱ ተነሥተን በመናገሻ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ወደ ጕጃም በሚወስደው ቀድሞ መስፍን ሐረር አሁን በላይ ዘለቀ በተባለው መንገድ ስንጓዝ፤ አዲሱ ገበያ ከተሠራበት ወረድ ብሎ፣ አንድ ዛፍ የበዛበትን ትልቅ ግቢ (አሁን ሸገር መናፈሻ የሆነው) አሳየኝና «እሱን እንድትከራየው» አለኝ:: «እንዴ! እኔ አስተዳደር ውስጥ አይደለሁ እንዴት ነው የምከራየው» ብዬ በውስጤ እያብሰለሰልኩ «ምን ሊሆን?» ብለው፣ «ለአንዳንድ ጉዳይ እንፈልገዋለን:: ልብ አድርግ ወደፊት የምነግርህ ብርቱ ነገር አለ:: ከዚህ ቀጥለህ የምትገናኛቸው ሰዎች አሉ:: የምንሰጠው ሽፋን ከውጭ አገር ለሚመጡ ሰዎች የአጭር ጊዜ የነገረ መረጃ ትምህርትና ሥልጠና መስጫ የሚል ይሆናል፤ ተጠንቀቅ ራስህን ቿብቅ» አለኝ::[18]

በታውን አሳይቶኝ «ተጠንቀቅ ራስህን ቿብቅ» ካለኝ በኋላ ተመልሰን ስንሔድ፤ መንገድ ላይ «ቀስ በልና ከኋላ የምትመጣዋን መኪና ሳትዞር በመስታወቱ እያት» አለኝ:: ከኋላ ያለውን በሚያሳየው መስታወት አየኋት:: «እንዴት እንደምትከታተለን ለማወቅ ከፈለግህ አቅጣጫህን ለውጠህ ሒድ፤ ትከተለናለች» አለኝ:: ከኋላ በሩቅ ትከተለን ነበር:: መንገዴን እየለዋወጥኩ ወዲያና ወዲህ ስዛወር ያቺ መኪና አሁንም ከሩቅ እኛን ተከትላ ትመጣ ነበር:: አቅጣጫዬን እየለዋወጥኩ ብሔድም መከተሏን አልተወችም:: «ምንድን ነው ነገሩ?» አልኩት:: እሱም «የአቶ መኮንን ሀብተ ወልድ ሰዎች ናቸው» አለኝ:: ይኼ እንዴት ሊሆን ቻለ? ብዬ ነገሩ ገረመኝ:: እንዲህ ያለ ክትትል? የከፋፍለህ ግዛ ፈሊጥ መሆኑን ባውቅም፤ የሁለቱ ከፍተኛ የመንግሥት ሹሞችና ቀራቢዎች (አቶ መኮንን ሀብተ ወልድና ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ) አንዱ የሌላውን እንቅስቃሴ መከታተል ግርም እያለኝ ሔድ:: ከዚህ በኋላ ያለው ነገር ስለሁሉም ነገር አንተ ድረስበት ማለቱ ነው ብዬ ገመትኩ:: ግልጽ አድርጎ ባይነግረኝም፤ «ከአሁን ጀምሮ የዚህ ውስጥ ለውስጥ የሚሔድ እንቅስቃሴ ተካፋይ ሆነሃል» ማለት እንደሆነ ገባኝ::

በሌላ ቀን፣ የሻለቃ ወርቁ መኮንን (በኋላ ብ/ጄኔራል እኔን ከሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ጋር ደርቦ ወይም የመንግሥት አካል አድርጎ በመቁጠር ይሁን ወይም በሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ላይ ያለውን ቅሬታ በእጅ አዙር ለመንገር፣ «እንዲህ እንዳላችሁ የምትቀሩ እንዳይመስላችሁ:: ሁላችሁም ታገኟታላችሁ:: ወታደሩ እንኳንስ ጥይት የያዘ ዝናር የሚታጠቅበት፣ የሱሪውን ቀበቶ እንኳን አጥብቆ የሚይዝበት አንጀት አጥቶ፤ ሆድና ጀርባው ተጣብቆ እየታየ፤ በዝምታ መታለፉ ችግር እንደሚያስከትል ዕወቁ» ብሎ በዛቻና በሽሙጥ የነገረኝን በመንገዳችን ላይ ለሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ አነሣሁለት:: ናቅ

---

[18] *ኋላ ላይ አቶ ወርቁ ተሰፋ እንደነገረኝ፤ እሱንም እስቲ ፩ የሚደርሱ አገራቸውን የሚወዱ ወጣቶች ፈልግ ብሎት ነበር:: ወደፊት እንደምጠቅሰው፤ ልክ እኔን እንደጠየቀኝ፣ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ መሣሪያ መተኮስ ትችልበታለህ? ብሎም ጠይቆት ነበር:: አቶ ወርቁ ተሰፋ እንዲመለምልለት የጠየቀው ፩ ሰዎች ከዚህ ቪላ ቤት ጋር ግንኙነት ሳይኖረው አይቀርም::*

በማድረግ፣ «አይ! እንዲያው ዝም ብሎ ነው። አንድ ነገር ቢመጣ አሁን እንደሚያወራው የሚቆም የለም። የኛ ሰው ጥንካሬ በወሬ ነው። በተግባር አያሳይም» በማለት ሁኔታውን ከመቃወም ይልቅ የመተባበር አዝማሚያ የሚመስል ሁኔታ ሲያሳይና እንዲያውም ጥንካሬ እንደሚጐል ያለውን ቅሬታ ሲገልጽ፤ ይኽ ሰውዬ ከመንገድ እየወጣ እንደሆነና ለዐመፅ እየተዘጋጀ መሆኑን፤ እኔም ቀስ ብየ እየተንሸራተትኩ ወደዚያው እየገባሁ መሆኔ ግልፅ ሆኖ ገባኝ። እንዲያ እያለም የሌ/ኮሎኔል ወርቅነህና የኔ መተማመን እየጠበቀ ሔደ።

እንዲሁ አንድ ቀን በጥቅምት ወር ፲፱፻፶ ዓ.ም. ከቀኑ ፲፩ ሰዓት ላይ፣ መኪናዬን ቤንዚን እንድሞላ በስልክ ነገረኝ። እኔም ነዳጅ ሞልቼ ልዩ ካቢኔ ቢሮው አቁሜ ስንሠራ አመሸን። ከምሽቱ አንድ ሰዓት ተኩል ሲሆን፣ ባንተ መኪና ወደ ቪላ ቬርዴ እንሒድ" አለኝ። "እሺ" ብዬ በመሔድ ቀጥታውን መንገድ ጨርሼ ወደ ቪላ ቬርዴ መግቢያ ልጠመዝዝ ስል፤ "እንዲያውም ግድ የለም ቀጥታውን መንገድ ይዘህ ትንሽ ሒድ" ብሎኝ መሔድ እንደጀመርን መንገዱን ወደ ደብረ ዘይት መንገድ እንዳቃና አዘዘኝ። ቀጠል በማድረግም፣ «ምን መሣሪያ አለህ?» አለኝ። «ትንሽ ሽጉጥ አለችኝ» አልኩትና ከኪሴ አውጥቼ አሳየሁት። ሽጉጤ በጣም ትንሽ አውቶማቲክ ስለነበረች በማናናቅ፤ «በል እሱን ተወው» አለና፣ የእሱን ኡዚ ከሰነድ መያዣ ቦርሳው አውጥቶ «ያዝ!» አለኝ፡ ተቀብየ ያዝኩ። ቀጠል አድርጐ፣ «ለመሆኑ አተኲኮስ ትችላለህ?» ሲል ጠየቀኝ። እኔም በማሽሙዋጠጥ «እሱንማ በኮሎኔል እምሩ ወንዴ ሠርግ ጊዜ ሆለታ ላይ በነበረው የተኩስ ውድድር ተያይተን የለም ወይ?» አልኩት[19]። «አ! አዎ! አዎ! እውነትህን ነው፤ ምንም አትል» አለና «ወደ ነፋስ ስልክ ቀጥል» አለኝ። ደረስን። «ትንሽ ሔደት በል»፣ አለኝ፤ አቃቂ ደረስን። «አቁም እስክልህ ድረስ ቀጥል» አለኝ። ደብረዘይት ደረስን። በራስ ሆቴል አጠገብ አድርጌ ወደ ባሕሩ እንድሔድ ነገረኝ። የምሔድበት ምክንያት ስላልተገለጸልኝ፤ ውስጤ በብዙ የሐሳብ ማዕበል እየተናወጠ ከባሕሩ ዳር ደረስን። ከዚያ «መኪናዋን ከመንገዱ አውጥተህ አቁማት» አለኝና፤ ፈጠን ብሎ ከመኪናዋ ወረደ።

ያለ ጊዜ ባሕር ጥግ ሲቆሙ፣ «ሰይጣን ይማታል» ስለሚባል ሰይጣን ቢመታንስ ብዬም ሠግቼ ነበር። ቦታው በአልጋ ወራሽ ማረፊያ ቤት በምዕራብ በር ትይዩ ከአጥር ውጭ ነበር። ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ስለሆነ፤ ኡዚውን አቀባብሎ ሰጠኝና፤ "እኔ ወደዚያ ቤት እሔዳለሁ። ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ከአምስት ደቂቃ ሲሆን፤ የዚያ ቤት የውጭ መብራት ይበራል። በበቆሎው መካከል አልፌ በረንዳው ላይ ስደርስ አልጋወራሽ ብቻ ወጥተው የተቀበሉኝ እንደሆነ፣ የምቆየው ለሩብ ሰዓት ብቻ ነው። ነገር ግን፣ ከሳቸው ጋር ሌላ ሰው ተጨምሮ የወጣ እንደሆን፣ ብትችል ነጥለህ ካልሆነም ደርበህ እንድትመታን። ይህ የመጨረሻ ቁርጠኛ ትእዛዝ ነው። እጄን

---

[19] የኮሎኔል እምሩ ወንዴ ሰርግ ላይ በግብዣው መኻል የዒላማ ተኩስ ሲደረግ፤ ያተኲኩሴን ሁኔታ አስመስክሬ ስለነበር ነው።

እንዳታስይዘው፤ የምቆየው ቢበዛ ሩብ ሰዓት ነውና ነቅተህ ጠብቅ» ብሎኝ ሔደ:: ጾ እሺ» ብዬ፣ ከዚያች ከእኔ ከተለየባት ደቂቃ ጀምሮ ሦስት ሰዓት ከአምስት ደቂቃ ሆኖ በጋሮ በኩል እደጃፍ ላይ እስቲቆም ድረስ ምን ያጋጥም ይሆን ብዬ በመሥጋት ስጨነቅ ቆየሁ:: በዚህ ዓይነት ጭንቀት ጣቴን ከኡዚው ምላጭ ላይ አድርጌ ስጠብቅ፤ በተባለው ሰዓት አልጋ ወራሽ ብቻ ብቅ ብለው ተቀብለው ይዘውት ገቡና እፎይታ ተሰማኝ::

ከዚህ በኋላ እዚያው ሆኜ ስጠብቀው ቆየሁ:: ነገር ግን እመለስበታለሁ ያለኝ ጊዜ ደግሞ ለሩብ ሰዓት እያለፈ በመሔዱ ሌላ ጥርጣሬና ሥጋት ያዘኝ:: ወደዚያ እንዳልገባ አላስፈላጊ ችግር እንዳልፈጥር ሠጋሁ:: ዝም እንዳልል ደግሞ የተሰጠኝ ጊዜ አለፈ:: «እስቲ አምስት ደቂቃ ልጠብቅ፤ ሌላ አምስት ደቂቃ ልጠብቅ፤ እንደገና ሌላ አምስት ደቂቃ ልጠብቅ» እያልኩ ሦስት ጊዜ አምስት አምስት ደቂቃዎችን በመጠበቅ ልቤ ተንጠልጥላ እንዳሳለፍኩ፤ ግማሽ ሰዓት ሆነ:: በዚህ ጊዜ መሸበር ጀመርኩ:: እወደው፣ እሳሳለትና አከብረው ነበር። «ምን ላድርግ» ብዬ ተጨነቅሁ:: «እሱ ችግር ላይ ወድቆ እኔ ወደ ቤቴ አልመለስም፣ እንግዲህ የመጣ ይምጣ» ብዬ በሕይወቴ ቆርጬ ወደ ገባበት ቤት ለመሔድ ልነሳ ስል ፴፭ኛው ደቂቃ ላይ ሁለቱም ብቅ አሉና፤ ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ በግሥጋሤ ወደ እኔ መጣ:: ነፍሴ ከሥጋዬ ጋር ተገናኘ ች:: ወደታች የወረደ መስሎኝ የነበረው ፊቴና ጆሮዬም አሁን መሰብሰቡ ታወቀኝ::

ይህ ከሆነ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ ጉዞ ላይ ሳለን፤ እያጉተመተመ «አይረቡም! ከንቱ ነው» ይላል:: ቆይቶ ደግሞ «እንዲያው ነው አይረቡም! ከንቱ ነው» ይላል:: ግን ይህን የሚልበትን ምክንያት አይነግረኝም። በምንም ዓይነት አባታቸውን አይተኩም!» እያለ ራሱ ለራሱ በማጉተምተም ተናገረ። አኸ! አባታቸውን አይተኩም የምትለዋን ቃል ቀርቀብ አደረግሁ:: አሁን ገባኝ። አሁን ዐፄ ኃይለ ሥላሴን ከሥልጣን አንስቶ አልጋ ወራሹን ለመተካት እንደሆነ እሱ እንደፈለገው እኔው ድሔ ደረስኩበት:: ነገሩን ባይገልጽልኝም እስከዚያ ድረስ የሔድንበት፣ ሕይወትን እስከመክፈል ድረስ የቆረጥንበት፣ ያን ሁሉ ችግር ያየንበት ጉዳይ እንደተጠበቀው ሆኖ እንዳላገኘው ገባኝ:: ይህን ሁሉ ሆኖ ግን ግልጽ አድርጎ ስላልነገረኝ ከፋኝ። ቀደም ብሎ የልጄን ፎቶግራፍ ከፊቴ እየቆረቆረ ምን ያደርጋል? የአንተ ዕምነት በዚህ ነው» እያለ ፎቶግራፉን የነካው ሞትን ለመቀበል የተዘጋጀህ አይደለህም ማለቱ ነው ብዬ የገመትኩት በዚህ ግዳጅ ግምቴ ትክክል እንደሆነ አረጋገጥኩ:: ምክንያቱም እዚያ ድረስ የሔድንበትና የደከምንበት ነገር ጉዳዩ ስላልተገለጸልኝ፤ ሁለት ነገሮች ሊሆኑ እንደሚችሉ አሰብሁ:: አንዱ አልጋወራሹ እንዳይነግሡ ንጉሡ የሥልጣኑን ውርስ ለሌላ መስጠት ይፈልጋሉ» የሚል ሐሜት በከተማው በሠፊው ይወራ ስለነበር፤ ይሄን በተመለከተ ምናልባት ተነጋግረው ይሆናል አሊያም ደግሞ የመንግሥት ለውጥ ሙከራ ይሆናል ብዬ ስላሰብኩ ነው::

በቀጥታ አልነግር እንዳለኝ ስለገባኝ በዘዋራ መንገድ እያነሳሁ ፍንጭ ለማግኘት መሞከር ጀመርኩ። በመኸሉ የወቅቱ ሹክሹክታ የሆነውን የክብር ዘበኛ መኮንኖችን ማጉረምረም ጣልቃ አግብቼ ሳነሣ፤ ትንሽ ፍንጭ የሚሆነኝ ነገር ማግኘት ጀመርኩ። «ሰውየው!» አለ ንጉሡን ለማለት «ይሉኝታ የሌላቸው፣ ራሳቸውን ብቻ የሚወዱ፣ ኢትዮጵያ እንዳለች ወድማ እሳቸው ብቻቸውን የሚቀሩ ቢሆን እንኳን ግድ የሌላቸው ናቸው።» የሚል የመረረ ቃል ከአንደበቱ ወጣ። ይህን ሲል እጁ የመኪናውን መሪ ሊለቅ ትንሽ ነበር የቀረው። የደነገጥኩትም ንጉሡ ለሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ያላቸው አመኔታ፣ ከበሬታ እና ፍቅር ምን ያህል እንደሆነ ከማያቸው ሰነዶች፣ ከባለሥልጣኖችና ከሕዝብ ይወራ ከነበረው ጋር አገናዝቤ ነው። በአንጻሩ ደግሞ፣ እሱ ንጉሡን የሚጠላ፣ ከሥልጣን ማግለያ ቀን የሚጠብቅ መሆኑ ሲገባኝ ለምን አልደናገጥ። እሱም ነገሩ እንደከበደኝ ከሁኔታዬ የተረዳ መሰለኝ። ያኔ እኔ በዕድሜ ፳፱ ዓመት ነበርኩ። የሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ዕድሜ ደግሞ ፴፬ አካባቢ ነበር። እኔ ነገሩ የከበደኝ መሆኑን ከአንዳንድ ሁኔታዎቼ ሲያይ አርእስቱን በመለወጥ የክብር ዘበኛ መኮንኖችን ጥያቄ አንሥቶ ችግሩ ወርቁ እንዳለህ ነው። ንጉሡ እንደዚህ ያሉ ሰው ስለሆኑ፤ ለጦሩ ደመወዝ እንዲጨመርለት ብለን ብንጠይቅ፤ ግንዘብ የለም፣ በጀት የለም" እያሉ፣ ሆድና ጀርባው የተጣበቀ ወታደር ወጭ ወራጅ ከሚተላለፍበት ከቤተ መንግሥት በራፍ ዘብ ሲያቆሙ አያፍሩም" በማለት ቅሬታውን በንዴትና በማማረር ገለጸልኝ። ቀደም ብዬ ያላወቅሁትና ያልጠበቅኩት ከንጉሡ ጋር የነበረው ፍቅር ተሟጦ አልቆ ለለውጥ እንደተነሳ ተረዳሁ። የሥርዓቱ ደጋፊ ነው ብዬ ፈርቼው የነበረውን አጠራልኝ። የተፈለገውም በዚህ ዓይነት እንድደርስበት መሆኑን ሳይነገረኝ ዐወቅሁ። ዐላማውን ብወደውም፤ ሳልደራጅ ቀስ እያለ ወደዚያው ያስገባኝ መሆኑን በዚሁ ዕለት በሚገባ ተገነዘብኩ። እንግዲህ ሕይወቴም ሞቴም ከሱና ካድማው ጋር የተያያዘ መሆኑን ዐውቄና ተቀብዬ፤ እያንዳንዷን ቀን በንቃትና በትጋት እከታተላት ጀመር።

## የመግለጫ መስጠት መርኃ ግብር

ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ አርቆ የሚያይ፣ ሠርቶ የማይደክም፣ የማይጠግብ፣ የማይሰለች፣ ተስፋ የማይቆርጥ፣ ብርቱ ሰው ነበር። እንዲህ ያለ በመሆኑም፣ በፀጥታና በልዩ ካቢኔ ተሰጥቶት በነበረው የሥራ ኃላፊነት የአገሪቱ የአመራር አባላት የሚፈጽሟቸው ልዩ ልዩ የሥራ በደሎች እየበረከቱ ሲመጡ፤ ከፍ ያለ የአገር ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት ማረም የሚያስችል አሠራር እንዲሰፍን በመጨረሻ የሞከረው፤ የመግለጫ መስጠት ሥልት በማስጀመር ነበር። ይህ ሥልት ንጉሡ፣ አልጋ ወራሹና ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተገኙበት የሚከናወን ነበር። ተሳታፊዎቹም ከባለሥልጣኖች ሚኒስትሮችና አንዳንድ ምክትል ሚኒስትሮች፣ እንዲሁም ከፍተኛ የጦር ኃይል አዛዦች ነበሩ። በሠለጠኑትና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ተከትለው በሚያስተዳድሩ አገር መሪዎች፣ አሜሪካ እንግሊዝ... ወዘተ. በሳምንት ቢያንስ ሁለት ቀናት መሪዎቹ ከፍተኛ የመንግሥቱ ባለሥልጣናትና የፀጥታው መሥሪያ ቤት ኃላፊዎች የዕለቱን ሥራቸውን ከመጀመራቸው በፊት ጠዋት "ብሪፊንግ ወይም ሲቺዌሽን ሩም" ተገኝተው በድንገተኛና ትኩረት በሚሹ ጉዳዮች ለአጭር ጊዜ ያህል የፀጥታው ጉዳይ ከሚመለከተው ባለሥልጣን የሚቀርቡትን መግለጫዎች ሰምተው ወዲያውኑ ለጉዳዩ እልባት ሰጥተው የሚለያዩበት ሥርዓት አላቸው።

የሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ጥረትም የአገሪቱ ድንገተኛና ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ጊዜ ሳይወስዱ በጊዜ በባለሥልጣኖች ታይተው ቶሎ ውሳኔ እንዲያገኙ በማድረግ ፈጣን የችግር አፈታት ሥራና ትክክለኝነትን ለማስለመድ ነበር። እነዚህ ተሳታፊዎች በተገኙበት፣ በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት (አሁን የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከሆነው) ከጃንሆይ ቢሮ ቀጥሎ ባለ ሰፊ ክፍል፣ በሳምንት ሁለት ቀን (ማክሰኞ እና ሐሙስ) ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ጀምሮ፣ በሕዝብ ፀጥታ መምሪያ የልዩ ልዩ ክፍል ኃላፊዎች፣ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ወቅታዊ ሁኔታዎች ላይ መግለጫዎች እንዲሰጡ፤ እንዲሁም አንዳንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሥራ እየተጐተተ በአገርና በሕዝብ ላይ እየደረሰ ስላለው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የመከላከያ፣ የፍትሕ፣ የአስተዳደርና የማኅበራዊ ጉዳይ ቀውሶች ለንጉሡ በሹክሹክታና በጓሮ በር እየተነገሩ ከሚታለፉ፤ በዚህ መግለጫ መስጫ መድረክ በግልጽ እየተነሡና በስብሰባው ተካፋዮች ውይይት ተደርጐባቸው መፍትሔ እንዲያገኙ ታስቦ የተሠራ ዘዴ ነበር። በዚህ መሠረት መግለጫውን እያዘጋጁ የሚያቀርቡት የመሥሪያ ቤቱ አባሎች፣ በወቅታዊ ሁኔታዎች በቂ ክትትል ያደረጉና ዕውቀቱም ያላቸው ከመሆናቸው በተጨማሪ፤ ለኢትዮጵያ ዕድገት፣ ብልፅግና፣ በጐ ምኞትና ብርቱ ፍላጐት የነበራቸው ሰዎች ነበሩ። ዝርዝራቸውም ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተው ነው።

[illegible]

ለ[illegible]

**አዲስ አበባ ።**

ዘርዘሩ በቃል እንደተነገረዎ መሠረት ከ[illegible] 18 ቀን 1952 ዓ.ም ጀምሮ [illegible] ከዚህ ጋር አያይዤ [illegible] ።

ከሠላምታ ጋር ።

[illegible]

*በመረጃ መስጠት እንድሳተፍ የታዘዝኩበት፤*
*የእጅ ጽሑፉና ፊርማው የኮሌኔል ወርቅነህ ነው።*

1. [illegible] ።

[illegible] ።

/ [illegible] /

---

2. [illegible] ።

[illegible] ።

/ [illegible] /

---

3. [illegible] ።

[illegible] ።

/ [illegible] /

---

4. [illegible] ።

[illegible]

/ [illegible]

[illegible] ።

እነዚህ መግለጫ ሰጭዎች መግለጫቸውን የአገር ውስጥና የውጭ አገር በሚል በሁለት ዋና ዋና ዘርፎች ከፍለው እያዘጋጁ ያቀርቡ ነበር። በነዚህ ርዕሶች ሥር በወቅቱ የመንግሥቱን አስተዳደር ወጥረው ይዘው ከነበሩት ዋና ዋና ችግሮች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

፩ኛ የአገር ውስጥ ጉዳይን በሚመለከት የተካተቱት የውስጥ ችግሮች በርካታ ነበሩ። እነዚህም የአስተዳደር፣ የፍርድና የኢኮኖሚ (በተለይ የሥራ ዕድል መጥበብ)፣ ሥራና ሠራተኛ አለማገናኘት (የተማሩትን በተገቢው የሥራ መስክ አለማሠማራት)፣ የአገሪቱ ሀብት በጥቂት የውጭ አገር ተወላጅ ነጋዴ፣ በባላባቶችና መኳንንት እጅ ተጨብጦ መያዝ)፣ ማኅበራዊ ዕድገት (በትምህርት፣ በጤና፣ በባህል) ያለው እንቅስቃሴ በጣም ውስን መሆን፣ ለጦር አደረጃጀትና ለደመወዝ ድልድል ተገቢውን ትኩረት አለመስጠት፣ በአንዳንድ ጠቅላይ ግዛቶች የፀጥታ መታወክ ... ወዘተ. እየተዳመረና እየተወሳሰበ መጥቶ አስተዳደሩን ውጥረት ውስጥ ከቶት ነበር። ለነዚህ ውስብስብ ችግሮች መነሻ ናቸው የተባሉት ምክንያቶች ደግሞ:-

ሀ/ ለከፍተኛ ትምህርት ውጭ አገር ሔደው የተመለሱ ወጣት ምሑራን ቁጥር በየጊዜው መጨመርና የዘመናዊነት መንፈስ መሠራጨት፣

ለ/ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ያስተምሩ የነበሩ መምህራን በተለይ የታሪክ መምህሩ በ፲፯ኛውና በ፲፰ኛው ክፍለ ዘመናት አውሮፓን የናጣት የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የፖለቲካ ጉዳይ አዲሱን የመቀበልና አሮጌውን የመንቀፍ፣ የለውጥ ጥያቄ አንሥተው ሲያስተምሩ፣ የእኛም ወጣቶች "ላሰው ብሎ ሲያማ ለኔ ብለህ ስማ" እንደተባለው የዚህ ዓይነቱ የለውጥ ጥያቄ በኢትዮጵያም ወቅታዊ ጥያቄ እየሆነና በወጣቶች ኅሊና እያቆጠቆጠ መምጣት አንዱ ነበር። እንዲሁም፣ የወቅታዊ ታሪክ (ኮንቴምፖራሪ ሂስትሪ) መምህር ከላይ በተጠቀሱት ዘመናት በአውሮፓ የነበረውን ሁኔታ ከኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ ጋር በማወዳደር እያነሡ ሲያስተምሩ የሚያነሱዋቸው የማነጻጸሪያ ሐሳቦች እንዲሁም የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥትና ሕግ የተባለውን ትምህርት ከሚያስተምሩት አቶ በረከተአብ ሀብተ ሥላሴ (በኋላ ዶክተር በኤርትራ የኘሬዘደንት ኢሳይያስ የሕግ አማካሪ የነበሩ) እና ዶክተር ፍሬዘር የተባሉ የሕዝብ አስተዳደር መምህር የሚያቀርቧቸው ምሳሌዎች የመማር ዕድሉ ባጋጠማቸው ወጣቶች ዘንድ ከፍተኛ የለውጥ ስሜት ማሳደር ሌላው ችግር ነበር።[20]

ሐ/ አንዳንድ የአፍሪካ አገሮች የነፃነት ታጋዮች በአዲስ አበባ ከተማ በመገኘት በየታላላቅ አዳራሾች በስብሰባ ያነሡት የነበረው ከጭቆና ተላቆ ነፃ የመውጣት የፖለቲካ ጥያቄ ለወጣቱ የሰጠው የንቃተ ኅሊናና ግንዛቤ ማደግ እንደዚሁ ያስከተለው ተጽዕኖም ነበር።

[20] በጊዜው የዩኒቨርስቲ ኮሌጅ የኤክስቴንሽን ተማሪ ስለነበርኩ አንዳንድ ኮርሶችን ስከታተል በተማሪው ዘንድ የሚፈጠረውን ስሜት እኔም አስታውሰዋለሁ።


መ/ ከብሔራዊ ቤተ መጻሕፍትና መዛግብት፣ ከአሜሪካና ከመስኮብ መጻሕፍት ቤቶች ያሉ መጻሕፍትን በማንበብ በሚገኘው ዕውቀት አማካኝነት በሚሠራጭ የውጭው ዓለም የፖለቲካ፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ዕድገት አራማጆች ታሪክ ስሜት ለለውጥ ቀስቃሽና አነቃቂ ሁኔታ ቀስ በቀስ ከምሑራኑ አልፎ ወደ ተራው ሕዝብም እየሠረጸ መምጣት የበኩሉን አስተዋፅኦ አድርጓል።

ሠ/ በዚያን ጊዜ የምዕራቡ ዓለም በሥልጣኔ እየገፋ በመሔድ፤ የብዙ ኢትዮጵያውያን የመግዛት ዐቅም የሚደርስባቸው በባትሪ የሚሠሩ ትንንሽ ሬዲዮኖች ሠርቶ ለገበያ በማቅረብ፤ ሕዝቡ እየገዛ በዓለም በየዕለቱ የሚፈጸሙትን ድርጊቶች በተለያዩ ቋንቋዎች ዜና እየሰማ ላልሰማው በማሰማት ወሬው ለሕዝብ በሥፋት እየተዳረሰ ትችት በማካሄድ ንቃተ ኅሊናውን እያሳደገና እያሠፋ መምጣትም ተጨማሪው ችግር ነበር።

ረ/ ወጣቱ የውጭ አገሮችን የአስተዳደር ሥርዓት ከኢትዮጵያ አስተዳደር ሥርዓት ጋር በማነጻጸር ኋላ ቀርነቱ እየቆጨው ለአስተዳደር ለውጥ በኃላፊነት ተነሣሥቷል። በሌላ ጎኑ ደግሞ፣ በወቅቱ ለአመራሩ ሳጋና ማገር የነበሩት የመንግሥት ባለሥልጣኖች ከአመራሩ ቀለበት ውስጥ የገቡት፤ ብዙዎቹ ቀደም ሲል በዋሉት ውለታና በዘር ሐረጋቸው በጥቅሉ ተገምግመው እንጂ ውለታቸው ከችሎታቸው ጋር ተመዛዝኖና በሕዝብ ዘንድ የሚኖራቸው ተቀባይነት ታምኖ አልነበረም። እነዚህ ባለሥልጣኖች አብዛኞቹ ከዘመናዊ አስተሳሰብ፣ ከዓለም ወቅታዊ ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዕድገት ጋር ያልተገናኙ፤ የተገናኙ እንኳ ቢኖሩ ከመንግሥት ሳይታዘዝ ቢሠሩ በአፈንጋጭነት የሚጠመዱ ነበሩ። በዚህ ምክንያት ዘመናዊውን የአመራር ሥርዓት ተቀብሎ ለአገርና ለሕዝብ ዕድገት ከመሥራት ይልቅ፣ በጊዜው በነበረው ልማዳዊ አስተዳደር የተተበተበው ከዘመናዊ ዕውቀትና አዲስ የሥራ ሥልት ይዘው ከተነሡ የአገር ዕድገት አራማጅ ወገኖች ጋር የጎላ ልዩነትና ቅራኔ መፈጠሩም ሌላው ችግር ነበር። ቅራኔው የተፈጠረው ለአገር ውለታ ለዋለ የውለታው ዋጋ ለምን ተከፈለ በማለት ሳይሆን፤ ውለታውን ያለ ችሎታው በሕዝብ አመራር ላይ አውሎ ሕዝብን ከመበደል፣ ሕዝብ በማይበድል ሥራ ላይ በመመደብ ቢከፈል አይሻልም ወይ በሚል ነበር። ጥቂት የአመራር ክፍሉ አባሎች በዚህ ቀና መንፈስ ሊሠሩ ሲፈልጉ፤ የልማዳዊው አመራር ደጋፊዎች የሚጋርጡዋቸው ችግሮች ጐልተው ወጡ። ይህንንም መንግሥት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ቀስ በቀስ ከችግሮቹ የሚያወጣ ሥልት ቀይሶ መለወጥ ሲቻል እስከ ህልፈታቸው ድረስ በሕዝብ ትከሻ ላይ ጭኖ ማኖሩ ዓይነተኛው የችግር ምንጭ ነበር። ይህን ቅራኔ ዝም ብሎ ማየት ኅሊናው ሊቀበለው ያልቻለውን ወጣቱን በለውጥ ፍላጎት ነውጥ ውስጥ ከተተው። ቁጭቱና በታሪክ ፊትም ተጠያቂ እንደሚያደርገው እየተሰማው ሲሔድ ኃላፊነቱን በቀላሉ እንዲያይ አላደረገውም። በአጠቃላይ ሁኔታው ይህን ችግር ለማስወገድ አንድ የለውጥ

ኃይል ቢነሣ ሙከራው ያለአንዳች ችግር ስኬታማ እንደሚሆን የዘመናዊ አስተሳሰብ አራማጅ የነበሩ ሁሉ የሚያምኑበት ሆኖ ይታይ ነበር።

፪ኛ የውጭ ሁኔታን በተመለከተ በዚያን ወቅት ኢትዮጵያ ባገር ውስጥ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በውጭ ጉዳይዋም ከፍተኛ የፖለቲካ ውጥረትና ተጽዕኖ ውስጥ ገብታ ነበር። ከውጥረቶቹ መካከል ጎላ ብለው ይታዩ ከነበሩት አንዱ የሱማሌ ነፃነት ነው። በ፲፱፻፶ዎቹ ዓመታት በቅኝ ገዢዎች ሥር የነበሩት ብዙ የአፍሪካ አገሮች ነፃነታቸውን እየተቀዳጁ መጥተው ነበር። በመሆኑም በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ያወጣው «ቤቪን ዲክላሬሽን ኦን ግሬተር ሶማሊያ» ተብሎ በሚታወቀው ሰነድ፤ በሦስት ቅኝ ገዢዎች ሥር የነበሩት የሱማሌኛ ቋንቋ ተናጋሪ አገሮችን አጋዴንንም በማጠቃለል «ታላቋ ሱማሌ» የተባለ መንግሥት ለማቋቋም የተጠነሰሰው ሐሳብ ኢትዮጵያን ከሚያሳስቧት ጉዳዮች አንዱ ነበር።




*የእንግሊዝ መንግሥት የታላቋ ሱማሌን መንግሥት ለማቋቋም የከለለውን ስፍራ የሚያሳይ ካርታ*

ሌላው ደግሞ፣ የሃይማኖትና የፖለቲካ ተፅዕኖ ነበር። ይኸውም ኢትዮጵያን ከአካባቢው አገሮች ለየት አድርጎ የሚያሳያት የክርስትናና የእስልምና (ሙስሊም) እምነት ተከታይ ሕዝቦች የሚኖሩባት አገር ሆና ሳለ፤ የመንግሥቷ የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ መሆን፤ በቅርብና በሩቅ የሚገኙ የእስልምና እምነት ተከታይ




የእንግሊዝ መንግሥት የታላቋ ሱማሌን መንግሥት ለማቋቋም የከለለውን ስፍራ የሚያሳይ ካርታ

መንግሥታት አይወዱትም ነበር። በመሆኑም በዐፄ ልብነ ድንግል፣ ቀጥሎም በዐፄ ዮሐንስ ፬ኛ ዘመነ መንግሥት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የእስልምና (ሙስሊም) እምነት ተከታይ ለማድረግ ተነስቶ የከሰመው እንቅስቃሴ፣ በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በ፲፱፻፷ዎቹ እንደገና በሌላ ዘዴ ማቆጥቆጥ ይታይ ስለነበር፤ እሱም አንድ ዐቢይ የፖለቲካ ችግር ተደርጐ ተወስዷል። ከዚህ ጋር በተያያዘም የእሥራኤል ወዳጅነት ተጨማሪ ችግር መሆኑ አልቀረም። የዐረብ አገሮች ከእሥራኤል ጋር ባላቸው ጠብ ምክንያት፣ «ኢትዮጵያ የእሥራኤል ወዳጅ ናት በማለት» የጠላቴ ወዳጅ ጠላቴ ነው በሚለው ፍልስፍና መሠረት እንደ ጠላት ያይዋት ነበር። ኢትዮጵያ በጂኦግራፊ አቀማመጧ በአብዛኛው በሙስሊም አገሮች የተከበበች ሆና በክርስቲያን ደሴትነት መታወቋና የመንግሥቷም ዓርማ «ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ» በሚል ቅጽል መታወቁ የእስልምና እምነት ተከታይ በሆኑ አገሮች ዛቻና ጥላቻ ተራ ገብታ የምትታይ ነበረች።

በዘመኑ ከነበሩት ነዋሪ ችግሮች መካከል የዓባይ ወንዝ መዘዝም ትኩረት የሚነፈገው አልነበረም። በዓባይ ወንዝ ተጠቃሚ የሆኑትና ካለዓባይ ወንዝ ሕልውናቸው ችግር ላይ የሚወድቀው ሱዳንና ግብፅ ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊና በጦር አደረጃጀቷ ከጠነከረች የዓባይ ወንዝ ተጠቃሚነታችንን ልትጋራ ትዳፈራለች በሚል ሥጋት ኢትዮጵያን ለማዳከም በስውርና ገሐድ የጦርና የሥነ ልቦና ዘመቻ ያካሒዱ ነበር። ይኸውም ለኢትዮጵያ ከእስክንድሪያ የሚላኩት ሊቃነ ጳጳሳት፣ ሕዝቡ ጠንክሮ እንዳይሠራና እንዳይበለጽግ ስለአጽዋማትና በዓላት አብዝቶ በማስተማር (በመስበክ) ማስነፍና መንግሥታቱም ተደጋጋሚ የድንበር ጥሰት መፈፀማቸው ማሣያ ነበር። በመተማና በሁመራ ገበሬዎች ላይ ማቋረጫ የሌለው ችግር መፍጠሩ ... ወዘተ. በዘመኑ አገሪቱን ወጥረው ከያዟት ዓበይት ችግሮች መካከል ነበሩ። በእሥራኤልና በዐረቦች መካከል በየጊዜው ይቀሰቀስ በነበረው ጠብ ምክንያት የስዌዝ ቦይ (ካናል) አልፎ፣ አልፎ የጦር ቀጠና ውስጥ እየገባ ስለሚዘጋ በኢትዮጵያ የገቢና የወጪ ንግድ እንቅስቃሴ ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩም ሌላ ችግር ነበር።

ከላይ እንደተገለጸው መግለጫ የመስጠቱ ዐላማ በአገሪቱ ላይ የተጋረጡትን አስቸኳይና ጊዜ የማይሰጡ ችግሮችን ለይቶ በማውጣት በፍጥነት ለማስወገድ ጥረት የማያደርጉ ባለሥልጣኖችን ድክመት ፊት ለፊት አውጥቶ እያሳየ፤ አሠራራቸውን እንዲያሻሽሉ ለማንቃት ነበር። በዚህ ገለጻ ግንዛቤ አግኝተው ሥራቸውን የማያሻሽሉ ሆነው በሚገኙ ባለሥልጣኖች ላይ ደግሞ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ እንዲችሉ ሁኔታዎችን የሚያመቻች ነበር። በአስቸኳይ መሻሻል ከነበሩባቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱና ዋነኛ የሆነውን «እሺ ነገ» የተባለውን የወቅቱን የሥራ መጕተቻና የቀጠሮ ማብዣ ልማድ ማስወገድና ተፈላጊውን ተግባር ከሥር ከሥር እየተከታተሉ እንዲከናወኑ ማድረግንም ያካትት ነበር። ይህም ወቅቱ ከሚጠይቀው ፍጥነት ጋር እርምጃቸውን ጠብቀው መራመድ በሚያቅታቸው ምትክ

ፍጥነታቸውን ከወቅቱ ሒደት ጋር ማገናኘት በሚችሉ፣ በአፍላ ጉልበት በሚሠሩ የተማሩ ወጣቶች ለመተካት መንገድ ይከፍታል የሚል ዕምነት ያስያዘ ነበር:: የተማሩ ወጣቶች የኃላፊነቱን ቦታ እየተረከቡ ከሔዱ፤ ለአገራቸው የሚመኙትን ዕድገት ለማስገኘት አስፈላጊው መሣሪያ እጃቸው ውስጥ ስለሚሆን፣ የመፈንቅለ መንግሥት ሐሳባቸውን ትተው አገሪቱን ቀስ በቀስ ወደ ማሳደጉ ሊያተኩሩ ይችላሉ የሚል የሩቅ ጊዜ ዓላማም የያዘ ነበር::

የሌ/ኮሎኔሉ ሥልት ረቀቅ ያለና ለተቃውሞ ያልተጋለጠ ነበር ቢባልም፤ ይህ ዕቅድ እንደሌሎች መልካም ዕቅዶች ሁሉ እያደረ መሰናክሎች እየገጠሙት ቆይቶ የተጠበቀውን ውጤት ሳያስገኝ ተቋረጠ:: ለግርማዊ ጃንሆይና ለባለሥልጣኖቹ የነበረው መግለጫ የመስጠቱ መርሐ ግብር ቢቋረጥም የመግለጫ መስጠቱ ሒደት አፈ ንጉሥ እሸቴ ገዳ ባሉበት ለፀጥታ መምሪያው ሠራተኞች ረቡዕና ዓርብ፣ በሳምንት ሁለት ቀን ይሰጥ ስለነበር፤ ሠራተኛውን በአገር ውስጥ፣ በዓለም አቀፍና በጠቅላላው ኢትዮጵያን በሚያሳስቡ ጉዳዮች ሁሉ ሁለንተናዊ ዕውቀት በማስጨበጥ ንቃተ ኅሊናውን ከፍ ያደረገ ነበር::

ይሰጡ ከነበሩት መግለጫዎች ውስጥ ለምሳሌ በግንቦት ወር ፲፱፻፺፪ ዓ.ም. ከቀረቡት ሁለቱን ለአብነት እንደሚከተለው አቀርባለሁ:: ድርቅ በትግራይና በወሎ ያደረሰውን ችግር አጥንቶ የሚመጣ በአፈንጉሥ እሸቴ ገዳ የሚመራ ቡድን ወደ ቦታው ሒዶ አጥንቶ ያቀረበውን ሪፖርት አፈ ንጉሥና ሌ/ኮሎኔል ወረቅነህ ተነጋግረው አስቸኳይ ውሳኔ ለመስጠት እንዲረዳ እኔ (የክፍሌ የሥራ ድርሻ ባይሆንም፣ ለአቀራረቡ ሲባል) የመልእክተኞቹን የጥናት ሪፖርት አጥንቼ መግለጫውን እንዳቀርብ ታዘዝኩ:: በዚህም መሠረት ገለጻውን ስሰጥ በትግራይና በወሎ ጠቅላይ ግዛቶች የደረሰው ድርቅ ስላስከተለው ችግር ሳትት በችግሩ ምክንያት «የተራቡ ሕፃናት የእናቶቻቸውን የደረቀ ጡት ሲገጠግጡ ከእናታቸው ደረት እንደቅጠል የሚረግፉት ሕፃናት ቁጥር ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ ነው» የሚል ቃል ተጠቀምኩ:: በዚህ ጊዜ ጃንሆይ ተቆጥተው ካባቸውን ወንጨፍ አድርገው «ሌላ ቃል አጥተህ ነው? እንዲህ ብለህ የምታቀርበው?» በማለት ገሰጹኝ:: ደንገጥ ብዬ ጥቂት ከቆየሁ በኋላ አንሰራርቼ መግለጫ መስጠቱን በመቀጠል «ረሀብተኛው የሞተው ሞቶ፣ የቀረው በየአቅራቢያው ወዳሉ ከተሞችና ወደ አዲስ አበባም ጭምር ዘልቆ ሊያጥለቀልቅ ስለሚችል አስቸኳይ መፍትሔ ሊፈለግለት ይገባል» አልኩ:: ራስ አንዳርጋቸው መሳይ (በወቅቱ የአገር ግዛት ሚኒስትር) ተነሥተው፣ "የወርቅነህ ሰዎች የኔን ሥራ ካላነሡ የሚናገሩት ሁሉ የማይደመጥላቸው ስለሚመስላቸው በዚህ ሁኔታ አቀረቡት እንጂ፤ ነገሩ ከእውነት የራቀ ነው» ብለው የመግለጫውን እውነታ አስተባበሉ:: ጃንሆይ «አይ! ዝም በልና ተቀመጥ» ቢሉም "የለም! እናገራለሁ!" ብለው ከጃንሆይ ጋር ክርክር ገጠሙ:: አፈ ንጉሥ እሸቴ ይህን እየሰሙ ዝም አሉ:: እኔ ከዚያ የመጣውን የመረጃ ሪፖርት ይዤ ስለነበር ለጃንሆይ ለማሳየት ወደሳቸው ልሔድ ስል «ግዴለም! ተረድተነዋል!» አሉ:: ነገሩም በዚሁ ቆመ::

በበኩሌ ያንን መግለጫ የሰጠሁት በጋለ መንፈስና በዕምነት ተመሥርቼ የሥራ ግዳጄን ለመወጣት ብቻ ሳይሆን፤ የወጣቱን ስሜት እንደተወጣሁ እየቆጠርሁ ነበር። መግለጫ መስጠቴ እንዳበቃ፤ ጄኔራል መንግሥቱ ጃንሆይን አጅበው ቢሮ ካደረሱ በኋላ ተመልሰው መጥተው፤ ራሴንና ትከሻዬን እያሻሹ «አንቺ እሳት ነሽ። በጣም ጥሩ አገላለጽ ነው» ብለው አደነቁኝ። ይሄን ጊዜ ደስ አለኝ፤ ተበረታታሁም። በዚህ መነሻ ከእርሳቸውም ጋር ቀረቤታችን ጠበቀ። ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህና ጄኔራል መንግሥቱ ባቀረብኩት መግለጫ እጅግ እንደተደሰቱ ባሳዩት የፊት ፈገግታ ይገለጽ ነበር። በአንጻሩ የንጉሡ ተግሣጽ፣ ንጉሡ በዘመነ መንግሥታቸው ሊደርስ ስለሚችል ችግር እውነቱን ተረድተው መፍትሔ ከመፈለግ እየተድበሰበሰ እሳቸው ሲወደሱ መኖርን የሚፈልጉ መሆናቸውን ከሚያሳይ በቀር፤ ምንም የሚጠቅመው ነገር አልነበረም። እንደተፈራው ችግሩ እውነት አሳሳቢና አስቸኳይ ስለነበር መግለጫው በተሰጠ በ፲፯ኛው ቀን ረሃብተኛው ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ከተማውን አጥለቀለቀው።

ሌላው ጉዳይ ስለኦጋዴን አሳሳቢነት የተሰጠው መግለጫ ነበር። ቀጥሎ ያቀረብኩት መግለጫ ኢትዮጵያ በምሥራቁ ክፍል፣ የኦጋዴን ወሰኗን ለማስጠበቅ በምታደርገው መከላከል ዙሪያዋን የከበቡት ሱማሌኛ ተናጋሪ አገሮች ጋር ግጭት ቢፈጠር፣ ወሰኗን ለማስከበር በምታደርገው መከላከል ችግር ፈጣሪዎች ከመንቀሳቀሳቸው በፊት የመከላከያ ቅድመ ዝግጅት ልታደርግ እንደሚገባ ነው። ጃንሆይ የመከላከያ ሚኒስትር ወደ ነበሩት ወደ ራስ አበበ አረጋይ ዞር ብለው፣ ከሁዋላ መቀመጫ ስለነበሩ «ይህ ልጃችሁ የሚላችሁን ሁሉ እስቲ ስሙ፤ እዚህ እደጃችሁ ድረስ መጥቶ መውጫ መግቢያ ሳያሳጣችሁ፣ ከአሁኑ አስቡበት እኮ ነው የሚለው» በማለት የአስቸኳይ ዝግጅቱ አስፈላጊነት በጃንሆይም ታምኖበት መመሪያ ያዘለ አስተያየት ሰጡ። ለዚህ መፍትሔ የሚሆን ጥናት በክብር ዘበኛና በጦር ሠራዊት በኩል ተጠንቶ እንዲቀርብ መመሪያ ተሰጠ። የሁለቱ የጦር ክፍል አዛዦች በስብሰባው ላይ ስለነበሩ ትእዛዙን ተቀብለው ሔዱ። ትዕዛዙ ማስታወሻ ቦርዱ ላይ ተመዘገበ።

በትእዛዙ መሠረት፣ ሁለቱ የጦር ክፍሎች በተሰጣቸው ጊዜ ውስጥ ጥናታቸውን አጠናቀው በስብሰባው ላይ ተገኙ። መጀመሪያ የክብር ዘበኛ ጦር ጥናታዊ ሪፖርት እንዲሰማ ታዝዞ ቀረበ። የጥናቱ ፍሬ ነገርም በዚህ አጭር ጊዜ አዲስ ሠራዊት መልምሎና አሠልጥኖ ብቁ ተዋጊ ኃይል ማፍራት አስተማማኝ ስለማይሆን፣ ከኢኮኖሚ አቅማችን ውስንነትና ከጊዜው ማጠር የተነሣ ከታሰበው ግብ ለማድረስ አጭርና ፈጣኑ መንገድ፣ ያለውን ሠራዊት በኮማንዶ ሥልት አሠልጥኖ በአንድ ግንባር ተዋግቶ ሲጨርስ ወዲያውኑ ወደሌላ የውጊያ ግንባር በፈጣን ማጓጓዣ ወስዶ እንዲዋጋ ተወርዋሪ ጦር ማዘጋጀቱ ይመረጣል የሚል ነበር።

ይህ መግለጫ እንደተሰማ ጄኔራል ነጋ ኃይለ ሥላሴ የመከላከያ ሚኒስቴር ሚንስትር ደኤታ (ቺፍ ኦፍ ስታፍ) እጃቸውን አንስተው አስተያየት ለመስጠት ጠየቁና ሲፈቀድላቸው፤ «ይህ ትልቅ የአገር ጉዳይ ነው። ላይ ላዩን የምንነጋገርበት

ጉዳይ አይደለም። ጥሩ ውሳኔ ላይ ለመድረስ የቀደመ የጦር ታሪካችን እንዴት ነበር? ብሎ ወደኋላ ማየት ያስፈልጋል። መነሻችን ነውና። በማይጨው ጦርነት ድል የሆነው በሠራዊት ማነስ ወይም በመሣሪያ እጥረት ሳይሆን፤ በአመራር ችግር ነው።» ሲሉ ጃንሆይ በዚህ አባባል በመበሳጨት ካባቸውን በኃይል አወናጭፈው ስብሰባውን ጥለው ወጡ። በዚህ ምክንያት የጦር ሠራዊት የጥናት ሪፖርት ሳይሰማና በዚህ ብርቱ የአገር ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሳይሰጥ ስብሰባው ተቋረጠ። መግለጫው ላይ ተመስርቶ ኢትዮጵያ ራሷን ለመከላከል እንድትችል የሚረዳትን ዝግጅት ባለማድረጓ በ፲፱፻፶፪ ዓ.ም. ሱማሌ ኢትዮጵያን ለመውረር ተነሥታ መኸል ሐረር ድረስ በቀላሉ ዘልቃ እንድትገባ ክፍተቱ ረዳት።

በሱማሌ ጉዳይ ላይ ያስፈልጋል የተባለው ዝግጅት በሚደርስበት ውሳኔ መሠረት ሳይካሔድ፤ እንግሊዝ ሳይታሰብ በድንገት ለቅኝ ግዛቷ ነፃነት ሰጠች። ቀደም ብሎ በተባበሩት መንግሥታት የሞግዚት አስተዳደር ስር የነበረችው የጣሊያን ሱማሌ ላንድ መጀመሪያ ነፃነቷን እንድታገኝ የነፃ መውጫ ቀኗን የመንግሥታቱ ኅብረት ወስኖ ነበር። በዚህ ግንዛቤ መሠረት የጣሊያን ሱማሌ በመንግሥታቱ በተያዘው ዕቅድ መሠረት ነፃ ወጥታ ሌሎች ይከተላሉ ተብሎ ሲጠበቅ እንግሊዝ የወሰደችው ዕርምጃ የተጠበቀውን ቅደም ተከተል አለዋወጠው። ይህ ጉዳይ የታወቀው ሁል ጊዜ እንደማደርገው ቴሌክሱን ለማንበብ በገባሁበት አንድ ቀን ጠዋት ስለሁኔታው ሮይተር የዘገበውን በማንበቤ ነበር። ስለዚህ ወዲያው ለአንድ ሩብ ጉዳይ ለሌ/ኮሌኔል ወርቅነህ ደውዬ ነግሬው ነበር። በአጋጣሚ ቀኑ መግለጫ መስጫ በመሆኑ ስለጉዳዩ ገለጻ ስሰጥበት ከተገኙ ባለሥልጣናት ጠቅላይ ሚኒስቴር አክሊሉ ሀብተ ወልድ፣ ውጪ ጉዳይ ሚኒስቴሩ ይልማ ዴሬሳና የማስታወቂያ ሚኒስትሩ አቶ አምደ ሚካኤል ደሣለኝ በወቅቱ በነበረው ግንዛቤ መሠረት ያልጠበቁት በመሆኑ ለማመንና ለመቀበል ከብዷቸው እንደነበር አስታውሳለሁ። በተለይ አቶ አክሊሉ ለጃንሆይ "ይሄ ሊሆን አይችልም" እስከማለት ደረሰው ነበር። እኔ የቴሌክሱን መልዕክት ይዤ ስለነበር ማስረጃውን ለመካድ የማይቻል ሆነ። ይሄ ሁኔታ የንጉሡን ትኩረት ሲያስገኝልኝ እነ አቶ አክሊሉና መኳንንቱ ግን ተዘጋጅተው የመጡበት ጉዳይ ባለመሆኑ አስከፍቷቸዋል።

ሱማሌ ነፃ ከወጣችበት ዕለት ከጥቂት ሳምንት በኋላ ጣሊያን ሱማሌላንድ በመንግሥታቱ ኅብረት በተያዘው ቀን መሠረት ነፃነቷ ሲታወጅ ኢትዮጵያን ወክሎ የሚገኝ ልዑክ ሲላክ እኔም አንዱ አባል ሆኜ ተልከን በበዓሉ ላይ ተካፍለናል።



*የኢትዮጵያን ምሥራቅ ክፍል (ኦጋዴን) የሚያጠቃልል የሱማሊኛ ተናጋሪ አገሮች መንግሥት መመሥረት ጅማሮን የሚገልፅ በክፍት ሰማያዊ መደብ ጨርቅ ላይ ባለ አምስት ጦር ኮከብ ሰንደቅ ዓላማ ሲሰቀልና ሲውለበለብ ዓይናችንን አፍጥጠን ስንመለከት*

*በስዕሉ ከግራ ወደቀኝ የመጀመሪያው ጥቁር ሙሉ ልብስ እና ጥቁር መነጽር ያደረገው የዚህ ታሪክ ጸሐፊ ከፀጥታ መሥሪያ ቤት፣ ሐጂ አብዱላሂ ሙሜ ጥቁር ሙሉ ልብስ እና ኮፊያ የለበሱት የገንዘብ ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትር፣ አቶ ጌታቸው መካሻ (በኋላ ዶክተር አምባሳደር) ከፕሮፖጋንዳ መሥሪያ ቤት (ማስታወቂያ ክፍል) ከሐጂ አብዱላሂ በኋላ ጥቁር መነጽር ያደረጉትና ፊታቸው ብቻ የሚታየው፣ ግራጫ ሙሉ ልብስ የለበሱትና ከሐጂ አብዱላሒ ቀጥሎ ሦስተኛው ብላታ ዳዊት ዕቁበ እግዚ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ደኤታ የመልክተኞቹ መሪ ናቸው።*

*አቶ ፍጡር አብርሃም በሞቃዲሾ የኢትዮጵያ መንግሥት ቆንስላ ጀኔራል፣ በቀኝ ዳር ነጭ የለበሱትና ከብላታ ዳዊት ዕቁባ እግዚ ቀጥሎ ያሉት፣ አቶ ተክለሃይማኖት ተድላ ምክትል ቆንስላ ከኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ከቀኝ ወደ ግራ አራተኛው ናቸው።*

የመግለጫ መስጠቱ ጉዳይ በዚህ ሁኔታ እየቀጠለ ሲሔድ፤ ለአንዳንድ ጉዳዮች እዚያው ላይ ትእዛዝና ውሳኔ ይሰጥባቸው ነበር። ትእዛዞቹ በመግለጫ መስጫው መድረክ ግራና ቀኝ ባሉ ሰሌዳዎች ላይ ተመዝግበው ይቀመጣሉ። የመግለጫ መስጫው ቢሮ ቁልፍ በእኔ እጅ ተቀምጦ በሰሌዳው ላይ የተጻፈው ትእዛዝም ሳይጠፋ ለሚቀጥለው መግለጫ ቀን ይደርስ ነበር። ስለዚህ በሚቀጥለው የመግለጫ ቀን ያ ባለፈው ጊዜ የተሰጠው ትዕዛዝ ወይም መመሪያ ከምን እንደደረሰ፣ ምን እርምጃ እንደተወሰደ፣ ምን መፍትሄ እንደተገኘለት ጉዳዩ የሚመለከተው ባለሥልጣን የማስረዳት ግዴታ ነበረበት። የዚህ ዓይነቱ አሠራር ጉዳዩ የሚመለከተውን ባለሥልጣን (መሥሪያ ቤት) ወለም ዘለም የማያስብል በመሆኑ፤ በጓሮ በር ገብቶ በቃላት ድርደራና እየተቅለሰለሱ ተናግሮ ከሐቁ መውጣትን አስቀረ። ይህ ያስከፋቸውና ጥቅማቸው የጐደለባቸው ባለሥልጣኖች፣ «ብለው! ብለው ጃንሆይ በልጆች ይመከሩ ጀመር» እያሉ በየቦታው አጣጥለው በማስወራት መግለጫ መስጠቱ እንዲቋረጥ አስደረጉ። ለማንኛውም ሌ/ኮሎኔል ወርቅነህ ይህ ሁሉ ሳያበሳጨውና ተስፋ ሳያስቆርጠው



የኢትዮጵያን ምሥራቅ ክፍል (ኡጋዴን) የሚያጠቃልል የሱማሊኛ ተናጋሪ አገሮች መንግሥት
መመሥረት ጅማሮን የሚገልፅ በክፍት ሰማያዊ መደብ ጨርቅ ላይ ባለ አምስት ጦር ኮከብ ሰንደቅ ዓላማ
ሲሰቀልና ሲውለበለብ ዓይናችንን አፍጥጠን ስንመለከት

ከዓላማው ሳያዛንፈው አንዱ ዕቅድ ሲደናቀፍ ሌላ ዕቅድ በማውጣት ለአገሩ ዕድገትና ለወገኑ ኑሮ መሻሻል የነበረው ጥረት ምን ያህል እንደነበር ያሣያል።

ከዚህ በላይ በአጭር በአጭሩ የጠቀስኳቸው ነጥቦች፣ ወጣቱ አገሩ እንደጥንታዊ ባለታሪክነቷ ቀድማ በመገኘት ፈንታ በቅርብ ከቅኝ ገዢዎቻቸው ነፃ ከወጡት አገሮች ጋር እንኳን ስትነጻጸር በማናቸውም ረገድ ፍጹም ኋላ ቀር ሆና መገኘቷ፤ ከፍተኛ ቁጭት አሳድሮበት ስላሳየው ሰላም የለሽ መታሸት እንዲሁም፣ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ ለመከላከል ሲሉ አንዳንድ አገርና ወገን ወዳዶችና ተቆርቋሪ ባለሥልጣኖች ያደርጉ የነበረውን ጥረት ለመፈንጠቅ ይረዳሉ ብዬ ካመንኩባቸው፣ ለጃንሆይ ከቀረቡ የሥርዓት ለውጥ ማስታወሻዎች ሳቀርብ፤ እኔ የማላውቃቸው እና ያልደረስኩባቸው ለጃንሆይ የቀረቡ ሌሎች የሥርዓት ለውጥ ማስታወሻዎች እንደሚኖሩ ሳልጠራጠር ነው። እነዚህና ሌሎች ጥረቶች ሁሉ ተደርገው ውጤት አልባ በመሆናቸው፤ የተማረው ወጣት ትውልድ ለአገሩ የሚያስፈልገውን ለውጥ እሱ በመሰለው መንገድ ለማምጣት ሲል የሔደበትን መንገድ ትንሽ ዘርዘር ባለ መልክ መመልከት አስፈላጊ ይሆናል። ይህም የአገሪቱ ወጣቶች በተሳተፉባቸው የትግል ዘርፎች ግንባር ቀደም የነበረው ገርማሜ ንዋይ የጎላ ሚና ያሳየበት የትግል ዘርፍ ይሆናል።